# ኦሪት ዘሌዋውያን

## ምዕራፍ ፩

### ስለሚቃጠል መሥዋዕት

፩እግዚአብሔርም ከምስክሩ ድንኳን ውስጥ
ሙሴን ጠርቶ እንዲህ ሲል ተናገረው:- ፪“ለእ
ስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው:- ከእ
ናንተ ለእግዚአብሔር መባ የሚያቀርብ ሰው
ቢኖር መባችሁን ከእንስሳ ወገን ከላሞች ወይም
ከበጎች ታቀርባላችሁ።
፫“መባውም የሚቃጠል መሥዋዕት ከላሞች
መንጋ ቢሆን፥ ነውር የሌለበትን ተባቱን ያቀ
ርባል፤ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት እንዲ
ኖረው በምስክሩ ድንኳን ደጃፍ ፊት ያቀርበ
ዋል። ፬ተቀባይነት ይኖረው ዘንድ ስለ እርሱም
ያስተሰርይለት ዘንድ እጁን በሚቃጠለው መሥ
ዋዕት ራስ ላይ ይጭናል። ፭በሬውንም በእግ
ዚአብሔር ፊት ያርደዋል፤ የአሮንም ልጆች
ካህናቱ ደሙን ያቀርባሉ፤ ደሙንም በምስ
ክሩ ድንኳን ደጃፍ ፊት ባለው በመሠዊያው
ላይ በዙሪያው ይረጩታል። ፮የሚቃጠለውንም
መሥዋዕት ይገፍፈዋል፤ በየብልቱም ይቈርጠ
ዋል። ፯የካህኑም የአሮን ልጆች በመሠዊያው
ላይ እሳት ያነድዳሉ፤ በእሳቱም ላይ ዕንጨት
ይረበርባሉ፤ ፰የአሮንም ልጆች ካህናቱ የተቈ
ረጡትን ብልቶች፥ ራሱንም፥ ስቡንም በመ
ሠዊያው ላይ በእሳቱ ላይ ባለው በዕንጨቱ
ላይ ይረበርቡታል። ፱የሆድ ዕቃውንና እግሮቹን
ግን በውኃ ያጥባሉ፤ ካህኑም ሁሉን የሚቃጠል
መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ በጎ መዓዛ እን
ዲሆን በመሠዊያው ላይ ያቀርበዋል።
፲“ነገር ግን ለእግዚአብሔር የሚቀርበው
መባ ከበጎች ወይም ከፍየሎች ቢሆን፥ ለሚ
ቃጠል መሥዋዕት ነውር የሌለበትን ተባቱን፥
የፊት እግሮቹንና ራሱን ጨምሮ[፩] ያቀርበዋል።
፲፩ [፪]በመሠዊያውም አጠገብ በመስዕ በኩል በእ
ግዚአብሔር ፊት ያርዱታል፤ የአሮንም ልጆች
ካህናቱ ደሙን በመሠዊያው ላይ በዙሪያው
ይረጩታል። ፲፪በየብልቱም ራሱን፥ ስቡንም
ይቈርጡታል፤ ካህናቱም በመሠዊያው ላይ በእ
ሳቱ ላይ ባለው በዕንጨቱ ላይ ይረበርቡታል፤
፲፫የሆድ ዕቃውንና እግሮቹን ግን በውኃ ያጥቡ
ታል። ካህኑም ሁሉን በመሠዊያው ላይ ለቍ
ርባን ያቀርበዋል፤ የሚቃጠል መሥዋዕት በእ
ግዚአብሔር ዘንድ በጎ መዓዛ ያለው ቍርባን
ነው።
፲፬“ለእግዚአብሔርም የሚያቀርበው ቍርባን
የሚቃጠል መሥዋዕት ከዎፎች ቢሆን፥ ቍር
ባኑን ከዋኖስ ወይም ከርግብ ያቀርባል። ፲፭ካህ
ኑም ወደ መሠዊያው ያቀርበዋል፤ አንገቱንም
ይቈርጠዋል፥ በመሠዊያውም ላይ ያኖረዋል።
ደሙንም በመሠዊያው አጠገብ ያንጠፈጥፈ
ዋል፤ ፲፮የሆድ ዕቃውንም ከላባዎች ጋር ለይቶ
በመሠዊያው አጠገብ በምሥራቅ በኩል በአ
መዱ ስፍራ ይጥለዋል፤ ፲፯ከክንፎቹም ይሰብረ
ዋል፤ ነገር ግን አይለየውም። ካህኑም በመሠዊ
ያው ላይ በእሳቱ ላይ ባለው በዕንጨቱ ላይ ያኖ
ረዋል፤ መሥዋዕቱ ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ
ያለው ቍርባን ነው።

## ምዕራፍ ፪

### የእህል ቍርባን

፩“ማናቸውም ሰው ቍርባን ለእግዚአብሔር
መሥዋዕት እንዲሆን ቢያቀርብ፥ ቍርባኑ ከመ
ልካም ስንዴ ዱቄት ይሁን፤ ዘይትም ያፈስስ
በታል፤ ነጭ ዕጣንም ይጨምርበታል፤ ይህም
መሥዋዕት ነው። ፪ወደ ካህኑ ወደ አሮን ልጆች

፩ “የፊት እግሮቹንና ራሱን ጨምሮ” የሚለው በግእዝና በዕብ. የለም።
፪ ግሪክ ሰባ. ሊ. “በራሱም ላይ እጁን ይጭናል” የሚል ይጨምራል።

ያመጣዋል፤ ከመልካም ስንዴ ዱቄቱና ከዘይ
ቱም አንድ እፍኝ ሙሉና ነጩንም ዕጣን ሁሉ
ወስዶ ካህኑ የእሳት ቍርባን ለእግዚአብሔር
በጎ መዓዛ እንዲሆን ለመታሰቢያ በመሠዊያው
ላይ ያቃጥለዋል። ፫ከመሥዋዕቱም የተረፈው
ለአሮንና ለልጆቹ ይሆናል፤ ይህም ከእግዚአብ
ሔር መሥዋዕት የተረፈ ቅዱስ ቅዱሳን ነው።
፬“በእቶን የተጋገረውን ቍርባን ስታቀርብ፥ በዘ
ይት የተለወሰ የመልካም ስንዴ ዱቄት፥ የቂጣ
እንጎቻ ወይም በዘይት የተቀባ ስስ ቂጣ ይሁን።
፭ቍርባንህም በምጣድ የተጋገረ ቍርባን ቢሆን፥
በዘይት የተለወሰ የመልካም ስንዴ ዱቄት ቂጣ
ይሁን። ፮ቈርስህም ዘይት ታፈስስበታለህ፤ የእግዚ
አብሔር መሥዋዕት ነው። ፯ቍርባንህም በመቀቀያ
የበሰለ ቍርባን ቢሆን፥ ዘይት የገባበት ከመልካም
ስንዴ ዱቄት የተደረገ ይሁን። ፰ከዚህም ያደረግኸ
ውን መሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር ታመጣለህ፤
ወደ ካህኑም ታቀርበዋለህ፤ ካህኑም ወደ መሠዊ
ያው ያቀርበዋል። ፱ካህኑም ከቍርባኑ መታሰቢያ
ውን ይወስዳል፤ በመሠዊያውም ላይ ይጨምረ
ዋል። ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ ያለው የሚቃጠል
ቍርባን ነው። ፲ከመሥዋዕቱም የተረፈው ለአሮንና
ለልጆቹ ይሆናል፤ ይህም ከእግዚአብሔር መሥዋ
ዕት የተረፈ ቅዱስ ቅዱሳን ነው።
፲፩“ለእግዚአብሔር የምታቀርቡት የእህል
ቍርባን ሁሉ እርሾ አይሁንበት፤ እርሾ ያለበት
ነገር፥ ማርም ለእግዚአብሔር ቍርባን ይሆን
ዘንድ አታቀርቡምና። ፲፪እነዚህንም ዐሥራት
አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር ታቀርባላችሁ፤
ነገር ግን ለእግዚአብሔር ለበጎ መዓዛ በመሠዊ
ያው ላይ አይቀርቡም። ፲፫የምታቀርቡት ቍር
ባን ሁሉ በጨው ይጣፈጣል፤ የአምላክህም
ቃል ኪዳን ጨው ከቍርባንህ አይጕደል፤ በቍ
ርባናችሁ ሁሉ ላይ ጨው ትጨምራላችሁ።
፲፬“ከመጀመሪያው እህልህ መሥዋዕት ለእግዚአ
ብሔር ብታቀርብ በእሳት የተጠበሰና የተፈተገ የእ
ህል እሸት ታቀርባለህ። ፲፭ዘይትም ታፈስስበታለህ፤
ዕጣንም ትጨምርበታለህ፤ የእህል ቍርባን ነው።
፲፮ካህኑም ከተፈተገው እህል፥ ከዘይቱም ወስዶ ከዕ
ጣኑ ጋር መታሰቢያውን ያቀርባል፤ ይህም ለእግዚ
አብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት ነው።

## ምዕራፍ ፫

### የደኅንነት መሥዋዕት

፩“ለእግዚአብሔር የሚቀርበው ቍርባን የደኅ
ንነት መሥዋዕት ቢሆን፥ ከላሞች መንጋ ተባት
ወይም እንስት ቢያቀርብ፥ ነውር የሌለበትን በእ
ግዚአብሔር ፊት ያቅርብ። ፪እጁንም ለቍርባን
በቀረበው ራስ ላይ ይጭናል፤ በምስክሩ ድን
ኳን ደጃፍ አጠገብ ያርደዋል፤ የአሮንም ልጆች
ካህናቱ ደሙን በሚቃጠለው መሥዋዕት፥ በመ
ሠዊያው ላይ በዙሪያው ይረጩታል። ፫ከደኅን
ነቱም መሥዋዕት ለእግዚአብሔር የእሳት ቍር
ባን አድርገው ያቀርባሉ፤ የሆድ ዕቃውንም
የሚሸፍነውን ስብ፥ በሆድ ዕቃውም ላይ ያለ
ውን ስብ ሁሉ፥ ፬ሁለቱንም ኵላሊቶች፥ በእ
ነርሱም ላይና በጎድኑ አጠገብ ያለውን ስብ፥
በጉበቱም ላይ ያለውን መረብ ከኵላሊቶቹ ጋር
ያመጣሉ። ፭የአሮንም ልጆች ከሚቃጠል መሥ
ዋዕት ጋር በመሠዊያው ላይ በእሳቱ ላይ ባለው
በዕንጨቱ ላይ ያቀርቡታል፤ የእሳት ቍርባን
ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ ነው።
፮“ለእግዚአብሔርም ለደኅንነት መሥዋዕት
የሚያቀርበው ቍርባኑ ከበጎች ተባት ወይም
እንስት ቢሆን፥ ነውር የሌለበትን ያቀርባል።
፯ለቍርባኑ የበግ ጠቦትን ቢያቀርብ በእግዚ
አብሔር ፊት ያቀርበዋል፤ ፰እጁንም ለቍር
ባን በቀረበው ራስ ላይ ይጭናል በምስክሩ
ድንኳን ደጃፍ ያርደዋል፤ ካህናቱም የአሮን
ልጆች ደሙን በመሠዊያው ላይ በዙሪያው ይረ
ጩታል። ፱ከደኅንነቱም መሥዋዕት ለእግዚአ
ብሔር የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጎ ያቀር
ባል፤ ስቡን፥ እስከ ጀርባውም ድረስ የተቈረጠ
ሙሉ ላቱን፥ የሆድ ዕቃውንም የሚሸፍነውን
ስብ፥ በሆድ ዕቃውም ላይ ያለውን ስብ ሁሉ፥
፲ሁለቱንም ኵላሊቶች፥ በእነርሱም ላይና በጎ
ድኑም አጠገብ ያለውን ስብ፥ በጉበቱም ላይ
ያለውን መረብ ከኵላሊቶቹ ጋር ይወስዳል።
፲፩ካህኑም በመሠዊያው ላይ ያቀርበዋል፤ በጎ
መዓዛ ያለው ለእግዚአብሔር የሚቃጠል መሥ
ዋዕት ነው።
፲፪“ቍርባኑም ፍየል ቢሆን በእግዚአብሔር
ፊት ያቀርበዋል፤ ፲፫እጁንም በራሱ ላይ ይጭ
ንበታል፤ በምስክሩ ድንኳን ደጃፍም ያርደ
ዋል፤ የአሮንም ልጆች ደሙን በመሠዊያው
ላይ በዙሪያው ይረጩታል። ፲፬ከእርሱም ለእ
ግዚአብሔር የእሳት ቍርባን አድርጎ ያቀርበ
ዋል፤ ሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ስብ፥ በሆድ
ዕቃውም ላይ ያለውን ስብ ሁሉ፥ ፲፭ሁለቱንም
ኵላሊቶች፥ በእነርሱም ላይና በጎድኑ አጠገብ
ያለውን ስብ፥ በጉበቱም ላይ ያለውን መረብ
ከኵላሊቶቹ ጋር ይወስዳል። ፲፮ካህኑም በመሠ
ዊያው ላይ ያቀርበዋል፤ ለእግዚአብሔር በጎ

መዓዛ ያለው የሚቃጠል መሥዋዕት ነው። ስቡ
ሁሉ ለእግዚአብሔር ነው። ፲፯ስብና ደም እንዳ
ትበሉ በምትኖሩበት ሁሉ ለልጅ ልጆቻችሁ የዘ
ለዓለም ሥርዐት ነው።”

## ምዕራፍ ፬

### የኀጢአት ማስተስረያ መሥዋዕት

፩እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ሲል ተና
ገረው፦ ፪“ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ
ንገራቸው፦ ማናቸውም ሰው ሳያውቅ በእግ
ዚአብሔር ፊት ኀጢአት ቢሠራ፥ እግዚአብ
ሔርም፦ አትሥሩ ካላቸው ትእዛዛት አንዲቱን
ቢተላለፍ፥ ፫የተቀባውም ሊቀ ካህናት በሕዝቡ
ላይ በደል እንዲቈጠርባቸው ኀጢአት ቢሠራ፥
ስለ ሠራው ስለ ኀጢአቱ ከመንጋው ነውር
የሌለበትን ወይፈን ለእግዚአብሔር ለኀጢአት
መሥዋዕት ያቀርበዋል። ፬ወይፈኑንም ወደ ምስ
ክሩ ድንኳን ደጃፍ በእግዚአብሔር ፊት ያመ
ጣዋል፤ እጁንም በወይፈኑ ራስ ላይ ይጭነ
ዋል፤ ወይፈኑንም በእግዚአብሔር ፊት ያር
ደዋል። ፭ተቀብቶ የተሾመው ካህን ከወይፈኑ
ደም በእጁ ወስዶ ወደ ምስክሩ ድንኳን ያመ
ጣዋል፤ ፮ካህኑም ጣቱን በደሙ ውስጥ ነክሮ
በእግዚአብሔር ፊት በመቅደሱ መጋረጃ ፊት
ደሙን ሰባት ጊዜ ይረጨዋል። ፯ካህኑም በምስ
ክሩ ድንኳን ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት ያለው
ጣፋጭ ዕጣን በሚታጠንበት መሠዊያ ቀንዶች
ላይ ከደሙ ያደርጋል፤ የወይፈኑንም ደም ሁሉ
በምስክሩ ድንኳን ደጅ ባለው ለሚቃጠል መሥ
ዋዕት በሚሆነው መሠዊያ በታች ያፈስሰዋል።
፰ለኀጢአትም መሥዋዕት ከሚታረደው ወይ
ፈን ስብን ሁሉ ይወስዳል፤ ሆድ ዕቃውንም
የሚሸፍነውን ስብ፥ በሆድ ዕቃውም ላይ ያለ
ውን ስብ ሁሉ፥ ፱ሁለቱንም ኵላሊቶች፥ በእ
ነርሱም ላይና በጎድኑ አጠገብ ያለውን ስብ፥
በጉበቱም ላይ ያለውን መረብ ከኵላሊቶች
ጋር፥ ፲ለደኅንነት መሥዋዕት ከታረደው ወይ
ፈን እንደ ተወሰደው ይወስዳል፤ ካህኑም ለሚ
ቃጠል መሥዋዕት በሚሆነው መሠዊያ ላይ
ያቀርበዋል። ፲፩የወይፈኑን ቍርበት፥ ሥጋው
ንም ሁሉ፥ ራሱንም፥ እግሮቹንም፥ ሆድ ዕቃ
ውንም፥ ፈርሱንም፤ ፲፪ወይፈኑን ሁሉ ከሰፈሩ
ወደ ውጭ አመድ ወደሚፈስስበት ወደ ንጹሕ
ስፍራ ይወስዱታል፤ በዕንጨትም ላይ በእሳት
ያቃጥሉታል፤ አመድ በሚፈስስበት ስፍራ ይቃ
ጠላል።

፲፫“የእስራኤል ማኅበር ሁሉ ቢስቱ፥ ነገሩም
ከማኅበሩ ዐይን ቢሸሸግ፥ እግዚአብሔርም አት
ሥሩ ካላቸው ትእዛዛት አንዲቱን ቢተላለፉ፤
፲፬ከዚህም በኋላ፥ የሠሩት ኀጢአት ቢታወቃቸ
ውና ንስሓ ቢገቡ ማኅበሩ ስለ ኀጢአት መሥ
ዋዕት ወይፈንን ያቀርባሉ፤ ወደ ምስክሩም ድን
ኳን ፊት ያመጡታል። ፲፭የማኅበሩም ሽማግ
ሌዎች እጆቻቸውን በወይፈኑ ራስ ላይ በእ
ግዚአብሔር ፊት ይጭናሉ፤ ወይፈኑንም በእ
ግዚአብሔር ፊት ያርዱታል። ፲፮የተቀባውም
ካህን ከወይፈኑ ደም ወደ ምስክሩ ድንኳን ያመ
ጣል፤ ፲፯ካህኑም ጣቱን በደሙ ውስጥ ነክሮ
በእግዚአብሔር ፊት በመቅደሱ መጋረጃ ፊት
ለፊት ሰባት ጊዜ ይረጨዋል። ፲፰በምስክሩ ድን
ኳን ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት ባለው በዕ
ጣን መሠዊያው ቀንዶች ላይ ከደሙ ያደር
ጋል፤ ደሙንም ሁሉ በምስክሩ ድንኳን ደጅ
ባለው ለሚቃጠል መሥዋዕት በሚሆነው መሠ
ዊያ በታች ያፈስሰዋል። ፲፱ስቡንም ሁሉ ከእ
ርሱ ወስዶ በመሠዊያው ላይ ያቀርበዋል።
፳እንዲህም በወይፈኑ ያደርጋል፤ ስለ ኀጢአት
መሥዋዕት በታረደው ወይፈን እንደ አደረገ
እንዲሁ በዚህ ያደርጋል፤ ካህኑም ኀጢአታቸ
ውን ያስተሰርያል፤ ኀጢአቸውም ይሰረይላቸ
ዋል። ፳፩ወይፈኑንም ሁሉ ከሰፈሩ ወደ ውጭ
ይወስዱታል፤ የፊተኛውንም ወይፈን እንዳቃ
ጠሉ ያቃጥሉታል፤ የማኅበሩ የኀጢአት መሥ
ዋዕት ነውና።

፳፪“መኰንንም ኀጢአትን ቢሠራ፥ ሳያው
ቅም እግዚአብሔር አምላኩ፦ አትሥራ ያለ
ውን ትእዛዝ ቢተላለፍ፥ እንዲህም ቢበድል፥
፳፫የሠራው ኀጢአት ቢታወቀውና ንስሓ ቢገባ፥
ከፍየሎች ነውር የሌለበትን ተባት ፍየል ለቍ
ርባኑ ያቀርባል፤ ፳፬በፍየሉም ራስ ላይ እጁን
ይጭናል፤ የሚቃጠልም መሥዋዕት በሚታረ
ድበት ስፍራ በእግዚአብሔር ፊት ያርደዋል፤
እርሱ የኀጢአት መሥዋዕት ነውና። ፳፭ካህኑም
ከኀጢአት መሥዋዕት ደም በጣቱ ወስዶ ለሚ
ቃጠል መሥዋዕት በሚሆነው መሠዊያ ቀንዶች
ላይ ያደርገዋል፤ ደሙንም ሁሉ ለሚቃጠል
መሥዋዕት ከሚሆነው መሠዊያ በታች ያፈስሰ
ዋል። ፳፮ስቡንም ሁሉ እንደ ደኅንነት መሥዋ
ዕት ስብ፥ በመሠዊያው ላይ ይጨምረዋል። ካህ
ኑም ኀጢአቱን ያስተሰርይለታል፤ ኀጢአቱም
ይቅር ይባልለታል።

፳፯“ከህገሩም ሕዝብ አንድ ሰው ኀጢአትን
ሳያውቅ ቢሠራ፥ እግዚአብሔርም፦ አትሥራ

ያለውን ትእዛዝ ቢተላለፍ፥ ቢበድልም፥ ፳፫ለእርሱም የሠራው ኀጢአት ቢታወቀውና ንስሓ ቢገባ፥[፩] ስለ ሠራው ኀጢአት ነውር የሌለባትን እንስት ፍየል ለቍርባኑ ያመጣል። ፳፬እጁንም በኀጢአት መሥዋዕት ራስ ላይ ይጭናል፤ ለሚቃጠልም መሥዋዕት እንስሳትን በሚያርዱበት ስፍራ የኀጢአት መሥዋዕት ፍየልዋን ያርዳታል። ፳፭ካህኑም ከደምዋ በጣቱ ወስዶ ለሚቃጠል መሥዋዕት በሚሆነው መሠዊያ ቀንዶች ላይ ያደርገዋል፤ ደሙንም ሁሉ ከመሠዊያው በታች ያፈስሰዋል። ፳፮ስቡም ሁሉ ከደኅንነት መሥዋዕት ላይ እንደሚወሰድ፥ ስብዋን ሁሉ ይወስዳል፤ ካህኑም ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ እንዲሆን በመሠዊያው ላይ ይጨምረዋል፤ ካህኑም ስለ እርሱ ያስተሰርያል፤ ኀጢአቱም ይሰረይለታል።

፴፪“ስለ ኀጢአትም መሥዋዕት የበግ ጠቦት ቢያቀርብ፥ ነውር የሌለባትን እንስት ያመጣል። ፴፫እጁንም በኀጢአት መሥዋዕት ራስ ላይ ይጭናል፤ የሚቃጠልም መሥዋዕት በሚታረድበት ስፍራ ለኀጢአት መሥዋዕት ያርዳታል። ፴፬ካህኑም ከኀጢአት መሥዋዕት ደም በጣቱ ወስዶ ለሚቃጠል መሥዋዕት በሚሆነው መሠዊያ ቀንዶች ላይ ያደርገዋል፤ ደሙንም ሁሉ ከመሠዊያው በታች ያፈስሰዋል። ፴፭ስቡ ሁሉ ለደኅንነት መሥዋዕት ከታረደው የበግ ጠቦት ላይ እንደሚወሰድ ስብዋን ሁሉ ይወስዳሉ፤ ካህኑም ለእግዚአብሔር በእሳት በተቃጠለው ቍርባን ላይ በመሠዊያው ላይ ይጨምረዋል። ካህኑም ስለ ሠራው ኀጢአት ያስተሰርይለታል፤ ኀጢአቱም ይሰረይለታል።

## ምዕራፍ ፭

### የኀጢአት ማስተስረያ መሥዋዕት የሚቀርብባቸው ምክንያቶች

፩“አንድ ሰው ቢበድል፥ የሚያምለውንም ቃል ቢሰማ፥ ምስክርም ሆኖ አንድ ነገር አይቶ እንደ ሆነ፥ ወይም ዐውቆ እንደ ሆነ ያነን ባይናገር በደሉን ይሸከማል፤ ፪ርኩስ ነገርን፥ የሞተውን፥ አውሬ የነከሰውን፥ ወይም የበከተ፥ ወይም የሚንቀሳቀስ የእንስሳን በድን የነካ፥ ከእርሱም ያነሣ ሰው ቢኖር፤ ፫ወይም ርኩስነቱን ሳያውቅ ርኩስን ሰው ቢነካ፥ በማናቸውም ርኵሰት ቢረክስ፥ ነገሩ በታወቀ ጊዜ በደል ይሆንበታል። ፬ሰው ሳያስብ ክፉን ወይም መልካምን ያደርግ ዘንድ ሳያስብ በከንፈሩ ተናግሮ ቢምል፥ ሳያስብ የማለውም ከዚህ ባንዱ ነገር ቢሆን፥ በታወቀው ጊዜ ከዚህ ነገር በአንዱ በደለኛ ይሆናል። ፭ከእነዚህ ነገሮች በአንዲቱ በደለኛ ቢሆን፥ የሠራውን ኀጢአት ይናዘዛል። ፮እግዚአብሔርን ስለ መበደሉና ስለ ሠራው ኀጢአት ከበጎቹ ነውር የሌለባትን እንስት በግ ወይም ከፍየሎች እንስት ፍየል ያመጣል፤ ካህኑም ስለ ኀጢአቱ ያስተሰርይለታል፤ ኀጢአቱም ይሰረይለታል።

፯“ስለ ሠራው ኀጢአት የበግ መግዣ ገንዘብ በእጁ ባይኖረው ግን፥ ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት የርግብ ግልገሎች፥ አንዱን ለኀጢአት መሥዋዕት ሁለተኛውንም ለሚቃጠል መሥዋዕት፥ ለእግዚአብሔር ያቀርባል። ወደ ካህኑም ያመጣቸዋል፤ ፰ካህኑም አስቀድሞ ለኀጢአት መሥዋዕት የሆነውን ያቀርባል፤ ራሱንም ከአንገቱ ይቈለምመዋል፤ ነገር ግን አይቈርጠውም። ፱ከኀጢአቱም መሥዋዕት ደም በመሠዊያው ግድግዳ ላይ ይረጨዋል፤ የተረፈውንም ደም ከመሠዊያው በታች ያንጠፈጥፋል፤ እርሱ የኀጢአት መሥዋዕት ነውና። ፲እንደ ሥርዐቱም ሁለተኛውን ለሚቃጠል መሥዋዕት ያዘጋጀዋል። ካህኑም ስለ ሠራው ኀጢአት ያስተሰርይለታል፤ ኀጢአቱም ይሰረይለታል።

፲፩“ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት የርግብ ግልገሎች ለማምጣት ገንዘብ በእጁ ባይኖረው፥ ስለ ሠራው ኀጢአት የኢፍ መስፈሪያ ዐሥረኛ ክፍል መልካም የስንዴ ዱቄት ለኀጢአት መሥዋዕት ያቀርባል፤ የኀጢአት መሥዋዕት ነውና ዘይት አያፈስስበትም፤ ዕጣንም አይጨምርበትም። ፲፪ወደ ካህኑም ያመጣዋል፤ ካህኑም ስለ መታሰቢያው ለእርሱ እፍኝ ሙሉ ይዘግናል፤ ለእግዚአብሔርም በእሳት በተቃጠለው ቍርባን ላይ በመሠዊያው ላይ ይጨምረዋል፤ እርሱም የኀጢአት መሥዋዕት ነው። ፲፫ካህኑም ከእነዚያ በአንዳቸው ስለ ሠራው ኀጢአት ያስተሰርይለታል፤ ኀጢአቱም ይቅር ይባልለታል። የተረፈውም እንደ እህሉ ቍርባን ለካህኑ ይሆናል።”

### ስለ በደል መሥዋዕት

፲፬እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፦ ፲፭“ሰው ቢዘነጋ፥ ሳያውቅም ለእግዚአብሔር በተቀደሰው በማናቸውም ነገር ኀጢ

፩ “ንስሓ ቢገባ” የሚለው በዕብ. እና በግሪክ ሰባ. ሊ.. የለም።

አትን ቢሠራ፥ ለበደል መሥዋዕት ለእግዚአብ
ሔር ከመንጋዉ ነውር የሌለበትን እንደ መቅ
ደሱ ሰቅል ሚዛን በብር ሰቅል የተገመተውን
አውራ በግ ለበደል መሥዋዕት ያቀርባል።
፲፮በተቀደሰ ነገር ላይ ስለ ሠራው ኀጢአት ዕዳ
ይከፍላል፤ አምስተኛውንም እጅ ይጨምርበ
ታል፤ ለካህኑም ይሰጠዋል። ካህኑም በበደል
መሥዋዕት አውራ በግ ያስተሰርይለታል፤ ኀጢ
አቱም ይቅር ይባልለታል።
፲፯“ሰው ባለማወቅ ኀጢአት ቢሠራ፥ እግዚ
አብሔርም፦ አትሥሩ ካላቸው ትእዛዛት አንዲ
ቱን ቢተላለፍ፥ ቢታወቀው፥ ኀጢአት ስለሆነ
ችበትም ንስሓ ቢገባ፥[፭] ፲፰ነውር የሌለበትን በሰ
ቅል የተገመተውን አውራ በግ ከመንጋው ለበ
ደል መሥዋዕት ወደ ካህኑ ያመጣዋል፤ ካህኑም
ሳያውቅ ስለ ሳተው ስሕተት ያስተሰርይለታል፤
ኀጢአቱም ይቅር ይባልለታል። ፲፱እርሱ በእግ
ዚአብሔር ፊት ንስሓ ገብቶአልና።”[፮]

## ምዕራፍ ፮

፩እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገ
ረው፦ ፪“ሰው ኀጢአትን ቢሠራ፥ የእግዚአብ
ሔርንም ትእዛዝ ቸል ቢል፥ ያኖረበትን አደራ
ወይም የኅብረትን ገንዘብ ወስዶ ባልንጀራውን
ቢክድ፥ ወይም ቢቀማ፥ ወይም በባልንጀራው
ላይ ግፍ ቢሠራ፥ ፫ወይም የጠፋውን ነገር ቢያ
ገኝ፥ ስለዚህም ቢዋሽ፥ ሰው ኀጢአትን ለመ
ሥራት ከሚያደርጋቸው ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ
በአንዲቱ በሐሰት ቢምል፥ ፬እርሱ ቢበድልና
ከዚህ በኋላ ንስሓ ቢገባ፥ በቅድሚያ የወሰደ
ውን፥ ወይም በዐመፅና በግፍ የተቀበለውን፥
ወይም የተሰጠውን አደራ፥ ወይም ጠፍቶ ያገ
ኘውን፥ ፭ወይም በሐሰት የማለበትን ነገር ቢመ
ልስ፥ በሙሉ ይመልስ፤ ከዚያም በላይ አምስ
ተኛውን ክፍል ጨምሮ የበደሉን መሥዋዕት
በሚያቀርብበት ቀን[፯] ለባለ ገንዘቡ ይስጠው።
፮ስለ በደል መሥዋዕትም ከመንጋው ነውር
የሌለበትን፥ ዋጋው እንደ በደሉ የተገመተውን
አውራ በግ ለእግዚአብሔር ያምጣ።[፰]። ፯ካህ
ኑም በእግዚአብሔር ፊት ያስተሰርይለታል፤
ስለዚያም ስለ አደረገው በደል ሁሉ ይቅር
ይባልለታል።”

### ስለሚቃጠል መሥዋዕት ሕግ

፰እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገ
ረው፦ ፱“አሮንንና ልጆቹን እንዲህ ብለህ እዘ
ዛቸው፦ የሚቃጠለው የመሥዋዕቱ ሕግ ይህ
ነው፤ የመሠዊያው እሳት በላዩ እየነደደች እስ
ኪነጋ ትተዉታላችሁ። ፲ካህኑም የተልባ እግር
ቀሚስና የተልባ እግር ሱሪ በሰውነቱ ላይ ይለ
ብሳል፤ በመሠዊያውም ላይ የሚቃጠለውን
መሥዋዕት እሳቱ ከበላው በኋላ አመዱን አን
ሥቶ በመሠዊያው አጠገብ ያፈስሰዋል። ፲፩ልብ
ሱንም ያወልቃል፤ ሌላም ልብስ ይለብሳል፤
አመዱንም ተሸክሞ ከሰፈሩ ንጹሕ ወደ ሆነ
ስፍራ ወደ ውጭ ያወጣዋል። ፲፪እሳቱም በመ
ሠዊያው ላይ ዘወትር ይነድዳል፤ አይጠፋም፤
ካህኑም ማለዳ ማለዳ ዕንጨት ያቃጥልበታል፤
የሚቃጠለውንም መሥዋዕት በዚያ ላይ ይረበር
ባል፤ በዚያም የደኅንነትን መሥዋዕት ስብ ያቃ
ጥላል። ፲፫ዘወትር በመሠዊያው ላይ እሳት ይነ
ድዳል፤ አይጠፋም።

### ስለ እህል ቍርባን

፲፬“የአሮን ልጆች በእግዚአብሔር ፊት በመ
ሠዊያው ፊት ለፊት የሚያቀርቡት የመሥዋ
ዕት[፱] ሥርዐት ይህ ነው። ፲፭ካህኑም ከእህሉ
ቍርባን መልካሙን የስንዴ ዱቄት ከዘይት ጋር
እፍኝ ሙሉ፥ ደግሞም በእህሉ ቍርባን ላይ
ያለውን ዕጣን ሁሉ ያነሣል፤ ለእግዚአብሔርም
በጎ መዓዛ ያለው የመታሰቢያ ቍርባን እንዲሆን
ለመታሰቢያ ነውና በመሠዊያው ላይ ይጨምረ
ዋል። ፲፮ከእርሱም የተረፈውን አሮንና ልጆቹ
ይበሉታል፤ ቂጣ ሆኖ በተቀደሰው ስፍራ ይበ
ላል፤ በምስክሩ ድንኳን ዙሪያ ባለው አደባባይ
ይበሉታል። ፲፯በእርሾ ቦክቶ አይጋገርም። ከእግ
ዚአብሔር መሥዋዕት የሰጠኋቸው ዕድል ፈንታ
ይህ ነው፤ እርሱም እንደ ኀጢአትና እንደ በደል

---

[፭] ዕብ. እና ግሪክ ሰባ. ሊ. “ቢተላለፍ ባያውቅም ያ ሰው በደለኛ ነው፤ ኀጢአቱንም ይሸከማል” ይላል።
[፮] ምዕ. ፭ ቍ. ፲፱ በዕብ. እና በግሪክ ሰባ. ሊ. “እርሱም የበደል መሥዋዕት ነው፤ በእውነት በእግዚአብሔር ፊት በደለኛ ሆኖአልና” ይላል።
[፯] ግእዙ “በዕለተ ዘለፍዎ” ይላል።
[፰] ዕብ. “ስለ በደል መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ከመንጋው ነውር የሌለበትን አውራ በግ እንደ ግምጋሜህ መጠን ስለ በደል መሥዋዕት ወደ ካህኑ ያምጣ” ይላል።
[፱] ዕብ. “የእህል ቍርባን” ይላል።

መሥዋዕት ቅዱስ ቅዱሳን ነው። ፲፰ከካህናት
ወገን ወንድ ሁሉ ይበላዋል፤ በዘመናችሁ ለዘለ
ዓለም ሕግ ነው። ከሚቃጠለው የእግዚአብሔር
መሥዋዕት የሚነካ ሁሉ ቅዱስ ይሆናል።”
፲፱እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ሲል ተና
ገረው:- ፳“እርሱን በቀባህበት ቀን ለእግዚአብ
ሔር የሚያቀርቡት የአሮንና የልጆቹ መባ ይህ
ነው። የኢፍ መስፈርያ ዐሥረኛ ክፍል መልካ
ሙን ዱቄት እኩሌታውን በጥዋት፥ እኩሌታ
ውንም በማታ ለዘወትር መሥዋዕት ያቀርባሉ።
፳፩ከዘይት ጋር በምጣድ ላይ ያደርጉታል፤ ለው
ሰውም ያገቡታል፤ ለእግዚአብሔር በጎ መዓዛ
እንዲሆን የሚፈተት መሥዋዕት ነው። ፳፪ከል
ጆቹም በእርሱ ፋንታ የተቀባው ካህን ያቀር
በዋል። ለዘለዓለም ሥርዐት ነው፤ ሁልጊዜም
ይደረጋል። ፳፫ካህናትም የሚያቀርቡት የእህል
ቍርባን ሁሉ ፈጽሞ ይቃጠላል፤ ከእርሱም
አንዳች አይበላም።”

### ስለ ኀጢአት ማስተስረያ መሥዋዕት

፳፬እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገ
ረው:- ፳፭“አሮንንና ልጆቹን እንዲህ ብለህ ንገ
ራቸው:- የኀጢአት መሥዋዕት ሕግ ይህ ነው፤
የሚቃጠል መሥዋዕት በሚታረድበት ስፍራ የኀ
ጢአቱ መሥዋዕት በእግዚአብሔር ፊት ይታረ
ዳል፤ እርሱም ቅዱሰ ቅዱሳን ነው። ፳፮የሚሠ
ዋው ካህን ይበላዋል፤ በምስክሩ ድንኳን ዙሪያ
በአለው አደባባይ በተቀደሰ ስፍራ ይበሉታል።
፳፯ሥጋውን የሚነካ ሁሉ ቅዱስ ይሆናል፤ ማና
ቸውም ልብስ ደም ቢረጭበት የተረጨበትን
በተቀደሰ ስፍራ ያጥቡታል። ፳፰የሚቀቀልበትን
ሸክላ ይሰብሩታል፤ በናስም ዕቃ ቢቀቀል ይፈ
ገፍጉታል፤ በውኃም ያጥቡታል። ፳፱ከካህናት
ወገን የሆነ ወንድ ሁሉ ከእርሱ ይበላል፤ እር
ሱም ቅዱሰ ቅዱሳን ነው። ፴ነገር ግን በመቅደሱ
ውስጥ ለማስተስረያ ይሆን ዘንድ ከደሙ ወደ
ምስክሩ ድንኳን የሚገባው የኀጢአት መሥዋዕት
ሁሉ አይበላም፤ በእሳት ይቃጠላል።[1]

## ምዕራፍ ፯

### ስለ በደል መሥዋዕት ሕግ

፩“የበደል መሥዋዕት ሕግ ይህ ነው፤ ቅዱሰ
ቅዱሳን ነው። ፪የሚቃጠለውን መሥዋዕት በሚ
ያርዱበት ስፍራ የበደሉን መሥዋዕት በግ በዚያ
ያርዱታል፤ ደሙንም በመሠዊያው ላይ በዙሪ
ያው ይረጩታል። ፫ስቡንም ሁሉ፥ ላቱንም፥
የሆድ ዕቃውንም የሚሸፍነውን ስብ ሁሉ፥ በአ
ንጀቱም ላይ ያለውን ስብ፤ ፬ሁለቱንም ኵላሊ
ቶች፥ በእነርሱም ላይና በጎድኑ አጠገብ ያለ
ውን ስብ፥ በጉበቱም ላይ ያለውን መረብ ከኵ
ላሊቶቹ ጋር ካህኑ ይለያል። ፭ካህኑም ለእግዚአ
ብሔር የእሳት ቍርባን እንዲሆን በመሠዊያው
ላይ ይጨምረዋል፤ እርሱም የበደል መሥዋዕት
ነው። ፮ከካህናት ወገን የሆነ ወንድ ሁሉ ይበ
ላዋል፤ በተቀደሰ ስፍራም ይበሉታል፤ ቅዱሰ
ቅዱሳን ነው። ፯የኀጢአት መሥዋዕት እንደ
ሆነ እንዲሁ የበደል መሥዋዕት ነው፤ ለሁለቱ
አንድ ሕግ ነው፤ በእነርሱ የሚያስተሰርይ ካህን
ይወስደዋል። ፰የሰውን የሚቃጠል መሥዋዕት
የሚያቀርብ ካህን ያቀረበው የሚቃጠለው መሥ
ዋዕት ቍርበት ለዚያው ካህን ይሆናል። ፱በእ
ቶን የተጋገረው የእህል ቍርባን ሁሉ፥ በመቀ
ቀያም ወይም በምጣድ የበሰለው ሁሉ ለሚያ
ቀርበው ካህን ይሆናል።[2] ፲በዘይትም የተለወ
ሰው ወይም የደረቀው የእህል ቍርባን ሁሉ
ለአሮን ልጆች ሁሉ ይሆናል፤ ለእያንዳንዱም
እኩል ይሆናል።

### ስለ ደኅንነት መሥዋዕት ሕግ

፲፩“ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት የደኅንነት
መሥዋዕት ሕግ ይህ ነው። ፲፪ለምስጋና ቢያቀ
ርበው፥ ከምስጋናው መሥዋዕት ጋር በዘይት
የተለወሰ የቂጣ እንጎቻ፥ በዘይትም የተቀባ ስስ
ቂጣ፥ በዘይትም የተለወሰ መልካም የስንዴ
ዱቄት ያቀርባል። ፲፫ለምስጋና የሚሆነውን የደ
ኅንነት መሥዋዕት በአቀረበ ጊዜ እርሾ ያለበ
ትን ኅብስት ያቀርባል። ፲፬ከቍርባኑም ሁሉ የእ
ግዚአብሔርን ድርሻ ከእነርሱ አንዱን ያነሣል።
እርሱም የደኅንነትን መሥዋዕት ደም ለሚረ
ጨው ካህን ይሆናል።
፲፭“ለምስጋና የሚሆነው የደኅንነት መሥዋዕት
ሥጋም ለእርሱ ነው፤ በሚቀርብበትም ቀን ይበ
ሉታል፤ ከእርሱ እስከ ነገ ምንም አያተርፉም።
፲፮የቍርባኑም መሥዋዕት የስእለት ወይም የፈ
ቃድ ቢሆን፥ መሥዋዕቱ በሚቀርብበት ቀን
ይብሉት፤ ከእርሱም የቀረውን በነጋው ይብ
ሉት፤ ፲፯ከመሥዋዕቱም ሥጋ እስከ ሦስተኛው

---

፩ በግሪክ ሰባ. ሊ. ምዕ. ፯ ከቍ. ፴፩ እስከ ፵ ያለው በዕብ. እና በግእዝ ምዕ. ፯ ከቍ. ፩ እስከ ፲ ነው።
፪ ምዕ. ፯ ቍ. ፲ በግእዙ የለም።

ቀን የሚቈየውን በእሳት ያቃጥሉታል። ፲፰በሦስ
ተኛው ቀን ከደኅንነት መሥዋዕት ሥጋ ቢበላ፥
አይሠምርም፤ ላቀረበው ሰው የተጠላ ይሆንበ
ታል እንጂ ቍርባን ሆኖ አይቈጠርለትም፤ ከእ
ርሱም የበላ ሰው ኀጢአቱን ይሸከማል።
፲፱"ርኩስ ነገር የሚነካውን ሥጋ አይብሉት፤
በእሳት ያቃጥሉት እንጂ። ንጹሕ የሆነ ሰው
ሁሉ ግን ከሥጋው ይብላ። ፳ኀጢአት ሳለባት፥
ለእግዚአብሔር ከሆነው ከደኅንነት መሥዋዕት
ሥጋ የበላች ሰውነት፥ ያች ሰውነት ከሕዝብዋ
ተለይታ ትጥፋ። ፳፩ከርኩስ ሁሉ፥ ወይም ከረ
ከሰው ሰው፥ ወይም ንጹሕ ካልሆነው እንስሳ
የነካች ሰውነት፥ ለእግዚአብሔር ከሆነው ከደ
ኅንነት መሥዋዕት ሥጋ ብትበላ፥ ያች ሰውነት
ከሕዝብዋ ተለይታ ትጥፋ።"

### ስብንና ደምን መብላት ስለማይገባ

፳፪እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተና
ገረው፦ ፳፫"የእስራኤልን ልጆች እንዲህ ብለህ
ተናገራቸው፦ የበሬ ወይም የበግ ወይም የፍ
የል ስብ ከቶ አትብሉ። ፳፬የሞተውን ስብ፥
አውሬ የሰበረውንም ስብ ለሌላ ተግባር አድር
ጉት፤ እናንተ ግን አትብሉት፤ ፳፭ለእግዚአብ
ሔር በእሳት ከሚቀርበው ከእንስሳ ስብ የሚ
በላ ሁሉ ያች የበላች ሰውነት ከሕዝብዋ ተለ
ይታ ትጥፋ። ፳፮በመኖሪያዎቻችሁ ሁሉ የወፍ
ወይም የእንስሳ ደም ቢሆን አትብሉ። ፳፯ደም
የምትበላ ሰውነት ሁሉ ያች ሰውነት ከሕዝብዋ
ተለይታ ትጥፋ።"

### ከደኅንነቱና ከሚቃጠለው መሥዋዕት የካህናት ዕድል ፈንታ

፳፰እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተና
ገረው፦ ፳፱"የእስራኤልን ልጆች እንዲህ ብለህ
ተናገራቸው፦ ለእግዚአብሔር የደኅንነት መሥ
ዋዕት የሚያቀርብ ሰው ቍርባኑን ለእግዚአብ
ሔር ከደኅንነቱ መሥዋዕት ያመጣል። ፴የእርሱ
እጆች ለእግዚአብሔር የእሳቱን ቍርባን ያመ
ጣሉ፤ ፍርምባውን በእግዚአብሔር ፊት ቍር
ባን ያቀርብ ዘንድ በጉበቱ ላይ ያለውን መረ
ብና የፍርምባውን ስብ ያመጣል። ፴፩ካህኑም
ስቡን በመሠዊያው ላይ ይጨምረው፤ ፍርምባ
ውም ለአሮንና ለልጆቹ ይሁን። ፴፪ከደኅንነት
መሥዋዕታችሁ ቀኝ ወርቹን ለማንሣት ቍርባን
እንዲሆን ለካህኑ ትሰጡታላችሁ። ፴፫ከአሮንም
ልጆች የደኅንነትን መሥዋዕት ደሙንና ስቡን
ለሚያቀርብ ለእርሱ ቀኝ ወርቹ እድል ፈንታው
ይሆናል። ፴፬ፍርምባውንና የቀኝ ወርቹን ከእስ
ራኤል ልጆች ከደኅንነት መሥዋዕታቸው ወስ
ጄአለሁ፤ ለካህኑ ለአሮንና ለልጆቹም ለዘለዓ
ለም ሕግ እንዲሆን ከእስራኤል ልጆች ዘንድ
ሰጥቼአቸዋለሁ።"
፴፭እግዚአብሔርን በክህነት ያገለግሉት ዘንድ
በተቀቡበት ቀን ለእግዚአብሔር ከሆነ ከእ
ሳት ቍርባን የአሮንና የልጆቹ ሕግ ይህ ነው።
፴፮ለልጅ ልጃቸው ለዘለዓለም ሕግ እንዲሆን
በቀባቸው ቀን የእስራኤል ልጆች ይሰጡአቸው
ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዘው ይህ ነው። ፴፯የሚ
ቃጠል መሥዋዕትና የእህል ቍርባን፥ የኀጢአ
ትና የበደል መሥዋዕት፥ የቅድስናና የደኅንነት
መሥዋዕት ሕግ ይህ ነው። ፴፰እግዚአብሔር
በሲና ምድረ በዳ ቍርባናቸውን በእግዚአብሔር
ፊት ያቀርቡ ዘንድ ለእስራኤል ልጆች ባዘዘ
ጊዜ በሲና ተራራ ለሙሴ ያዘዘው ይህ ነው።

## ምዕራፍ ፰

### ስለ አሮንና ስለ ልጆቹ ቅብዐተ ክህነት

(ዘፀ. ፳፱፥ ፩-፴፯)

፩እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተና
ገረው፦ ፪"አሮንን፥ ከእርሱም ጋር ልጆቹን፥
ልብሱንም፥ የቅብዐቱንም ዘይት፥ ለኀጢአት
መሥዋዕትም የሆነውን ወይፈን፥ ሁለቱንም
አውራ በጎች፥ የቂጣውንም እንጀራ መሶብ
ውሰድ፤ ፫ማኅበሩንም ሁሉ ወደ ምስክሩ ድን
ኳን ደጃፍ ሰብስባቸው።" ፬ሙሴም እግዚአብ
ሔር እንዳዘዘው አደረገ፤ ማኅበሩንም ሁሉ ወደ
ምስክሩ ድንኳን ደጃፍ ሰበሰበ። ፭ሙሴም ማኅ
በሩን፥ "እግዚአብሔር ታደርጉ ዘንድ ያዘዘው
ነገር ይህ ነው" አላቸው።
፮ሙሴም አሮንንና ልጆቹን አቀረበ፤ በው
ኃም አጠባቸው። ፯እጀ ጠባብም አለበሰው፤
በመታጠቂያም አስታጠቀው፤ የበፍታ ቀሚስም
አለበሰው፤ ልብሰ መትከፍም ደረበለት፤ በል
ብሰ መትከፉም አሠራር ላይ በብልሃት በተጠ
ለፈ ቋድ አስታጠቀውና በእርሱ ላይ አሰረው።
፰ልብሰ እንግድዓውንም በእርሱ ላይ አደረገ፤
በልብሰ እንግድዓውም ላይ የምልክትና የእው
ነት መገለጫዎችን፩ አኖረበት። ፱እግዚአብሔ
ርም ሙሴን እንዳዘዘው በራሱ ላይ አክሊል

---

፩ ዕብ. "ኡሪምና ቱሚም" ይላል።

አደረገለት፤ በአክሊሉም ላይ በፊቱ በኩል የተ
ቀደሰውን የወርቅ መርገፍ አደረገ።
፲ሙሴም የቅብዐቱን ዘይት ወሰደ፤ ከእርሱም
በመሠዊያው ላይ ሰባት ጊዜ ረጨ፤ ፲፩ይቀድሳ
ቸውም ዘንድ መሠዊያውንና ዕቃውን ሁሉ፥
የመታጠቢያውን ሰንና መቀመጫውን ቀባ፤
ድንኳኒቱንና ዕቃዋን ሁሉ ቀብቶ ቀደሳቸው።
፲፪ከቅብዐቱም ዘይት በአሮን ራስ ላይ አፈሰሰ፤
ቀባው፤ ቀደሰውም። ፲፫እግዚአብሔርም ሙሴን
እንዳዘዘው ሙሴ የአሮንን ልጆች አቀረበ፤ የበ
ፍታ ቀሚሶችንም አለበሳቸው፤ በመታጠቂያም
አስታጠቃቸው፤ አክሊልም ደፋላቸው።
፲፬የኀጢአትንም መሥዋዕት ወይፈን አቀረበ፤
አሮንና ልጆቹም በኀጢአቱ መሥዋዕት ወይ
ፈን ራስ ላይ እጆቻቸውን ጫኑ። ፲፭አረዱትም፤
ሙሴም ደሙን ወስዶ በጣቱ የመሠዊያውን ቀን
ዶች ዙሪያ ቀባ፤ መሠዊያውንም አነጻው፤ ደሙ
ንም ከመሠዊያው በታች አፈሰሰው፤ ያስተሰርይ
ለትም ዘንድ ቀደሰው። ፲፮ሙሴም በሆድ ዕቃው
ላይ ያለውን ስብ ሁሉ፥ የጉበቱንም መረብ፥ ሁለ
ቱንም ኵላሊቶች፥ ስባቸውንም ወሰደ፤ በመሠዊ
ያውም ላይ ጨመረው። ፲፯እግዚአብሔርም ሙሴን
እንዳዘዘው ወይፈኑን፥ ቍርበቱንም፥ ሥጋውንም፥
ፈርሱንም ከሰፈሩ ውጭ በእሳት አቃጠለ።
፲፰ሙሴም ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚሆን
አውራ በግ አቀረበ፤ አሮንና ልጆቹም በአው
ራው በግ ራስ ላይ እጆቻቸውን ጫኑ። ፲፱ሙሴም
ያን በግ አረደው፤ ደሙንም በመሠዊያው ዙሪያ
ረጨው። ፳አውራውንም በግ በየብልቱ ቈረጠ፤
ሙሴም ጭንቅላቱን፥ ብልቶቹንም፥ ስቡንም
ጨመረ። ፳፩የሆድ ዕቃውንና እግሮቹንም በውኃ
አጠበ፤ ሙሴም አውራውን በግ ሁሉ በመሠዊ
ያው ላይ ጨመረ፤ ይህ በጎ መዓዛ እንዲሆን የሚ
ቃጠል መሥዋዕት ነበረ፤ እግዚአብሔር ሙሴን
እንዳዘዘው ለእግዚአብሔር የእሳት ቍርባን ነበረ።
፳፪ሙሴም ለቅድስና የሚሆነውን ሁለተኛውን
አውራ በግ አቀረበ፤ አሮንና ልጆቹም በአውራው
በግ ራስ ላይ እጆቻቸውን ጫኑ፤ ፳፫አረዱትም።
ሙሴም ከደሙ ወስዶ የአሮንን የቀኝ ጆሮውን
ጫፍ፥ የቀኝ እጁንም አውራ ጣት፥ የቀኝ እግ
ሩንም አውራ ጣት ቀባው። ፳፬የአሮንንም ልጆች
አቀረበ፤ ሙሴም የቀኝ ጆሮአቸውን ጫፍ፥ የቀኝ
እጃቸውንም አውራ ጣት፥ የቀኝ እግራቸውንም
አውራ ጣት ከደሙ ቀባ፤ ሙሴም ደሙን በመሠ
ዊያው ዙሪያ ረጨ። ፳፭ስቡንና ላቱን፥ በሆድ ዕቃ
ውም ላይ ያለውን ስብ ሁሉ፥ የጉበቱንም መረብ፥
ሁለቱንም ኵላሊቶች፥ ስባቸውንም፥ ቀኝ ወርቹ
ንም ወሰደ፤ ፳፮በእግዚአብሔር ፊት ካለው የቅ
ድስና መሶብ አንድ የቂጣ እንጎቻ፥ አንድም የዘ
ይት እንጀራ፥ አንድም ስስ ቂጣ ወስዶ በስቡና
በቀኝ ወርቹ ላይ አኖራቸው። ፳፯ሁሉንም በአሮ
ንና በልጆቹ እጆች ላይ አደረገ፤ በእግዚአብሔ
ርም ፊት ቍርባንን አቀረበ፤ ፳፰ሙሴም ከእጃ
ቸው ተቀብሎ በመሠዊያው በሚቃጠለው መሥዋ
ዕት ላይ አኖረው። በጎ መዓዛ የቅድስና መሥዋዕት
ነበረ። እርሱም ለእግዚአብሔር የእሳት ቍርባን
ነበረ። ፳፱ሙሴም ከቅድስናው አውራ በግ ፍርምባ
ውን ወስዶ በእግዚአብሔር ፊት ያቀርበው ዘንድ
ቈራረጠ። እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው ይህ
ለቅድስና ከታረደው አውራ በግ የሙሴ እድል
ፈንታ ሆነ።
፴ሙሴም ከቅብዐቱ ዘይትና በመሠዊያው
ላይ ከአለው ከደሙ ወስዶ በአሮንና በልብሱ
ላይ፥ በልጆቹና በልጆቹ ልብስ ላይ ረጨው፤
አሮንንና ልብሱንም፥ ልጆቹንም፥ የልጆቹንም
ልብስ ቀደሰ።
፴፩ሙሴም አሮንንና ልጆቹን አላቸው፥ “ሥጋ
ውን በምስክሩ ድንኳን ደጃፍ በተቀደሰው ቦታ
ቀቅሉ፤ አሮንና ልጆቹ ይብሉት ብሎ እግዚአብ
ሔር እንዳዘዘኝ በዚያ እርሱንና በቅድስናው መሶብ
ያለውን እንጀራ ብሉ። ፴፪ከሥጋውና ከእንጀራውም
የተረፈውን በእሳት አቃጥሉት። ፴፫ሰባት ቀን ይክና
ችኋልና የክህነታችሁ ቀን እስኪፈጸም ድረስ ሰባት
ቀን ከማኅበሩ ድንኳን ደጃፍ አትውጡ። ፴፬በዚህ
ቀን እንደ ተደረገ ለእናንተ ለማስተስረያ ይደረግ
ዘንድ እንዲሁ እግዚአብሔር አዘዘ። ፴፭እግዚአብ
ሔር እንዲሁ አዝዞኛልና እንዳትሞቱ በምስክሩ
ድንኳን ደጃፍ ሌሊቱንና ቀኑን ሰባት ቀን ተቀ
መጡ፤ የእግዚአብሔርንም ሥርዐት ጠብቁ፤”
፴፮አሮንና ልጆቹም እግዚአብሔር ለሙሴ ያዘዘ
ውን ሁሉ አደረጉ።

## ምዕራፍ ፱

### አሮን መሥዋዕት ስለ ማቅረቡ

፩በስምንተኛውም ቀን እንዲህ ሆነ፤ ሙሴ አሮን
ንና ልጆቹን፥ የእስራኤልንም ሽማግሌዎች ጠራ።
፪ሙሴም አሮንን አለው፥ “ስለ ኀጢአት መሥዋ
ዕት ከመንጋው እንቦሳውን፥ ስለሚቃጠልም መሥ
ዋዕት አውራውን በግ[፩] ወስደህ በእግዚአብሔር

፩ ዕብ. “ነውር የሌለባቸውን” ይላል።

ፊት አቅርባቸው። ፫የእስራኤልንም ልጆች፡- ለኀ
ጢአት መሥዋዕት አውራ ፍየልን፥ ለሚቃጠልም
መሥዋዕት ነውር የሌለባቸውን አንድ ዓመት የሆ
ናቸውን ጥጃና ጠቦትን፥ ፬ለደኅንነትም መሥዋ
ዕት በሬንና አውራ በግን፥ በዘይትም የተለወሰ የእ
ህልን ቍርባን በእግዚአብሔር ፊት ይሠዉ ዘንድ
ውሰዱ፤ ዛሬ እግዚአብሔር ይገለጥላችኋልና ብለህ
ንገራቸው።” ፭ሙሴም ያዘዛቸውን ወደ ምስክሩ
ድንኳን ደጃፍ አመጡ፤ ማኅበሩም ሁሉ ቀርበው
በእግዚአብሔር ፊት ቆሙ። ፮ሙሴም፥ “ታደ
ርጉት ዘንድ እግዚአብሔር ያዘዛችሁ ቃል ይህ
ነው፤ የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጥላችኋል”
አለ። ፯ሙሴም አሮንን፥ “ወደ መሠዊያው ቀርበህ
የኀጢአትህን መሥዋዕትና የሚቃጠለውን መሥዋ
ዕትህን ሠዋ፤ ለራስህና ለወገንህ አስተስርይ፤ እግ
ዚአብሔርም እንዳዘዘ የሕዝቡን ቍርባን አቅርብ፤
አስተስርይላቸውም” አለው።
፰አሮንም ወደ መሠዊያው ቀርቦ ስለ ራሱ
ኀጢአት መሥዋዕት የሆነውን ጥጃ አረደ።
፱የአሮንም ልጆች ደሙን አቀረቡለት፤ ጣቱ
ንም በደሙ ውስጥ ነክሮ የመሠዊያውን ቀን
ዶች ቀባ፤ ደሙንም ከመሠዊያው በታች አፈ
ሰሰው። ፲እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው
ከኀጢአቱ መሥዋዕት ስቡንና ኵላሊቶቹን፥
የጉበቱንም መረብ በመሠዊያው ላይ ጨመረ።
፲፩ሥጋውንና ቍርበቱንም ከሰፈሩ ውጭ በእ
ሳት አቃጠሉ።
፲፪የሚቃጠለውንም መሥዋዕት አረደ፤ የአሮ
ንም ልጆች ደሙን አመጡለት፤ እርሱም በመ
ሠዊያው ላይ በዙሪያው ረጨው። ፲፫የሚቃጠለ
ውን መሥዋዕት በየብልቱ፥ ራሱንም አመጡ
ለት፤ እርሱም በመሠዊያው ላይ ጨመረው።
፲፬የሆድ ዕቃውንና እግሮቹንም በውኃ አጠበ፤
በመሠዊያውም በሚቃጠለው መሥዋዕት ላይ
ጨመረው።
፲፭ከዚህም በኋላ የሕዝቡን ቍርባን አቀረበ፤
ስለ ሕዝቡ ለኀጢአት መሥዋዕት የሆነውን
ፍየል ወስዶ አረደው፤ አነጻውም፤ እንደ ፊተ
ኛውም ለየው። ፲፮የሚቃጠለውንም መሥዋዕት
አቀረበ፤ እንደ ሥርዐቱም አደረገው። ፲፯የስን
ዴውንም መሥዋዕት አቀረበ፤ ከእርሱም እፍኝ
ሙሉ ወስዶ በጥዋት ከሚቃጠለው መሥዋዕት
ሌላ በመሠዊያው ላይ ጨመረው።
፲፰ስለ ሕዝቡ የሆነውን የደኅንነት መሥዋ
ዕት፥ በሬውንና አውራውን በግ አረደ፤ የአ
ሮንም ልጆች ደሙን አመጡለት፤ በመሠዊ
ያውም ዙሪያ ረጨው፤ ፲፱የበሬውንና የአው
ራውንም በግ ስብ፥ ላቱንም፥ የሆድ ዕቃው
ንም የሚሸፍነውን ስብ፥ ሁለቱን ኵላሊቶ
ቹንም፥ በላያቸውም ያለውን ስብ፥ የጉበቱ
ንም መረብ አመጡለት። ፳ስቡንም በፍርም
ባዎቹ ላይ አኖረ፤ ስቡንም በመሠዊያው ላይ
ጨመረ፤[፪] ፳፩እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘ
ዘው አሮን ፍርምባዎቹንና ቀኝ ወርቹን በእግ
ዚአብሔር ፊት ለየ።[፫]
፳፪አሮንም እጆቹን ወደ ሕዝቡ ዘረጋ፤ ባረ
ካቸውም፤ የኀጢአቱን፥ የሚቃጠለውንም፥
የደኅንነቱንም መሥዋዕት ከሠዋ በኋላ ወረደ።
፳፫ሙሴና አሮንም ወደ ምስክሩ ድንኳን ገቡ፤
ወጡም፤ ሕዝቡንም ባረኩ፤ የእግዚአብሔርም
ክብር ለሕዝቡ ሁሉ ተገለጠ። ፳፬እሳትም ከእ
ግዚአብሔር ዘንድ ወጣ፤ በመሠዊያውም ላይ
የሚቃጠለውን መሥዋዕት፥ ስቡንም በላ፤ ሕዝ
ቡም ሁሉ አይተው ተደነቁ፤ በግምባራቸውም
ወደቁ።

## ምዕራፍ ፲

### ስለ ናዳብና አብዩድ በደል

፩የአሮንም ልጆች ናዳብና አብዩድ[፩] በየራሳ
ቸው ጥናውን ወስደው እሳት አደረጉበት፤ በላ
ዩም ዕጣን ጨመሩበት፤ በእግዚአብሔርም ፊት
እግዚአብሔር ያላዘዛቸውን ሌላ እሳት አቀረቡ።
፪እሳትም ከእግዚአብሔር ዘንድ ወጥቶ በላ
ቸው፤ በእግዚአብሔርም ፊት ሞቱ። ፫ሙሴም
አሮንን፥ “እግዚአብሔር፡- ወደ እኔ በሚቀ
ርቡ እመሰገናለሁ፤ በሕዝቡም ሁሉ ፊት እከ
ብራለሁ ብሎ የተናገረው ይህ ነው” አለው፤
አሮንም ደነገጠ። ፬ሙሴም የአሮንን አጎት የአ
ዚሔልን ልጆች ሚሳዴንና ኤልሳፍንን ጠርቶ፥
“ሂዱ፤ ወንድሞቻችሁን ከመቅደሱ ፊት አን
ሥታችሁ ከሰፈር ወደ ውጭ ውሰዱአቸው”
አላቸው። ፭እነርሱም ገብተው አነሡአቸው፤
ሙሴም እንዳለ በልብሳቸው ከሰፈር ወደ ውጭ
ወሰዱአቸው። ፮ሙሴም አሮንን፥ ልጆቹንም
አልዓዛርንና ኢታምርን፥ “እንዳትሞቱ፥ በማኅ

፪ ዕብ. “አቃጠለ” ይላል።
፫ ግእዝ “ሙሴን እንዳዘዘው በእግዚአብሔር ፊት ዕድሉ ነውና አሮን ቀኝ ወርቹንና ፍርምባውን ለየ” ይላል።
፩ ዕብ. “አቢሁ” ይላል።

በሩም ላይ ሁሉ ቍጣ እንዳይወርድ ራሳችሁን
አትንጩ፤ ልብሳችሁንም አትቅደዱ፤ እግዚአ
ብሔር ስላቃጠላቸው ማቃጠል ግን ወንድሞቻ
ችሁ የእስራኤል ቤት ሁሉ ያልቅሱ። ፯የእግዚ
አብሔር የቅብዐት ዘይት በላያችሁ ነውና እን
ዳትሞቱ ከምስክሩ ድንኳን ደጃፍ አትውጡ”
አላቸው። ሙሴም እንዳዘዛቸው አደረገ።

### ለአሮንና ለልጆቹ የተሠሩ ሕጎች

፰እግዚአብሔርም አሮንን እንዲህ ብሎ ተና
ገረው፦ ፱“እንዳትሞቱ ወደ ምስክሩ ድንኳን
ስትገቡ ወይም ወደ መሠዊያው ስትቀርቡ አን
ተና ልጆችህ የወይን ጠጅና የሚያሰክርን ነገር
ሁሉ አትጠጡ፤ ይህም ለልጅ ልጃችሁ የዘለዓ
ለም ሥርዐት ይሆናል፤ ፲በተቀደሰውና በአልተ
ቀደሰው፥ በርኩሱና በንጹሑም መካከል ትለያ
ላችሁ፤ ፲፩እግዚአብሔርም በሙሴ እጅ የነገራ
ቸውን ሥርዐት ሁሉ ለእስራኤል ልጆች ታስ
ተምራቸዋለህ።”

፲፪ሙሴም አሮንን፥ የተረፉለትን ልጆቹን አል
ዓዛርንና ኢታምርን አላቸው፥ “ቅዱሰ ቅዱሳን
ነውና ለእግዚአብሔር ከሆነው ከእሳት ቍርባን
የቀረውን የስንዴውን ቍርባን ውሰዱ፤ ቂጣም
አድርጋችሁ በመሠዊያው አጠገብ ብሉት፤
፲፫እግዚአብሔርም እንዲህ አዝዞኛልና፥ ለእግዚ
አብሔር ከሆነው ከእሳት ቍርባን ለአንተም፥
ለልጆችህም የተሰጠ ሥርዐት ነውና በቅዱስ
ስፍራ ትበሉታላችሁ። ፲፬እነዚህም ከእስራኤል
ልጆች ከደኅንነት መሥዋዕቶች ለአንተና ለል
ጆችህ ሥርዐት እንዲሆኑ ስለ ተሰጡ፥ የመሥ
ዋዕቱን ፍርምባና ወርች አንተ፥ ከአንተ ጋርም
ልጆችህ፥ ቤተሰብህም ተለይቶ በንጹሕ ስፍራ
ትበላላችሁ። ፲፭የመሥዋዕቱን ወርችና ፍርምባ
በእግዚአብሔር ፊት ከሚቀርበው መሥዋዕት
የእሳት ቍርባን ከሆነው ስብ ጋር ያመጣሉ፤
እግዚአብሔር እንዳዘዘ ለአንተ፥ ከአንተ ጋርም
ለወንዶችና ሴቶች ልጆችህ የዘለዓለም ሥር
ዐት ይሆናል።”

፲፮ሙሴም የኀጢአቱን መሥዋዕት ፍየል
እጅግ ፈለገው፤ በፈለገውም ጊዜ እነሆ ተቃ
ጥሎ ነበር፤ ሙሴም የቀሩትን የአሮንን ልጆች
አልዓዛርንና ኢታምርን ተቈጣቸው፤ እንዲህም
አላቸው፦ ፲፯“ቅዱሰ ቅዱሳን ነውና፥ የሕዝቡ
ንም ኀጢአት እንድትሸከሙ፥ በእግዚአብሔ
ርም ፊት እንድታስተሰርዩላቸው ይህን ትበሉ
ዘንድ ለእናንተ ሰጥቶታልና ስለ ምን የኀጢአ
ትን መሥዋዕት በቅዱሱ ስፍራ አልበላችሁም?
፲፰እነሆ፥ ደሙን ወደ መቅደስ ውስጥ አላገባ
ችሁትም፤ እኔ እንደታዘዝሁ በቅዱስ ስፍራ
ውስጥ ትበሉት ዘንድ ይገባችሁ ነበር።” ፲፱አሮ
ንም ሙሴን ተናገረው እንዲህም አለው፥
“እነሆ፥ ዛሬ የኀጢአታቸውን መሥዋዕት፥
የሚቃጠለውንም መሥዋዕታቸውን በእግዚአብ
ሔር ፊት በለዩ ጊዜ፥ ይህች አገኘችኝ፤ ዛሬም
የኀጢአቱን መሥዋዕት እበላ ዘንድ በእግዚአ
ብሔር ፊት መልካም አይደለም።” ፳ሙሴም
ሰማ፤ ደስም አለው።

## ምዕራፍ ፲፩

### ስለሚበሉና ስለማይበሉ እንስሳት
(ዘዳ. ፲፬፥ ፫ - ፳፩)

፩እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን እንዲህ
ብሎ ተናገራቸው፦ ፪“ለእስራኤል ልጆች እን
ዲህ ብላችሁ ንገሩአቸው፦ በምድር ካሉት እን
ስሳት ሁሉ የምትበሉአቸው እንስሳት እነዚህ
ናቸው። ፫የተሰነጠቀ ሰኰና ያለውንና የሚያመሰ
ኳውን እንስሳ ሁሉ ብሉ። ፬ነገር ግን ከሚያመ
ሰኩት፥ ሰኰናቸውም ስንጥቅ ከሆነው ከእነዚህ
አትበሉም፤ ግመል ያመሰኳል፤ ነገር ግን ሰኰ
ናው ስላልተሰነጠቀ ለእናንተ ርኩስ ነው። ፭ጥን
ቸል ያመሰኳል፤ ነገር ግን ሰኰናው ስላልተሰነ
ጠቀ ይህ ለእናንተ ርኩስ ነው። ፮ሽኮኮ ያመሰ
ኳል፤ ነገር ግን ሰኰናው ስላልተሰነጠቀ ለእና
ንተ ርኩስ ነው። ፯እርያም ሰኰናው ተሰንጥቆ
አል፤ ነገር ግን ስለማያመሰኳ ለእናንተ ርኩስ
ነው። ፰የእነዚህን ሥጋ አትበሉም፤ በድናቸው
ንም አትንኩም፤ ለእናንተ ርኩሳን ናቸው።

፱“በውኃ ውስጥ ከሚኖሩት ሁሉ እነዚህን
ትበላላችሁ፤ በውኆች፥ በባሕሮችም፥ በወንዞ
ችም ውስጥ ከሚኖሩት ሁሉ ክንፍና ቅርፊት
ያላቸውን ትበላላችሁ። ፲በውኆች ውስጥ ከሚ
ንቀሳቀሱ፥ በውኆች ውስጥ የሕይወት ነፍስ
ከአላቸው ሁሉ፥ በባሕሮችና በወንዞች ውስጥ
ክንፍና ቅርፊት የሌላቸው ሁሉ በእናንተ ዘንድ
የተጸየፉ ናቸው። ፲፩በእናንተም ዘንድ የተጸየፉ
ይሆናሉ። ሥጋቸውንም አትበሉም፤ በድናቸው
ንም ትጸየፉላችሁ። ፲፪ክንፍና ቅርፊትም የሌላ
ቸው በውኃ ውስጥ የሚኖሩት ሁሉ ለእናንተ
ርኩሳን ናቸው።

፲፫“ከወፎችም ወገን የምትጸየፉአቸው እነዚህ
ናቸው፤ አይበሉም፤ የተጸየፉ ናቸው፤ ንስር፥
ገዴ አሞራ፥ ዓሣ አውጭ፥ ፲፬ጭላት፥ ጭል
ፊት፥ አንጭ አሞራ በየወገኑ፤ ፲፭ቁራ ሁሉ

በየወገኑ፤ ፲፮ሰጎን በየወገኑ፤ ጠለቋ፥ ዝዪ፥
በቋል በየወገኑ፤ ፲፯ጉጉት፥ እርኩም፥ ጋጋኖ፥
፲፰የውኃ ዶሮ፥ ይብራ፥ ጥምብ አንሣ አሞራ፥
፲፱ሸመላ፥ ሳቢሳ በየወገኑ፤ ጅንጅላቴ ወፍ፥
የሌሊት ወፍ።

፳"የሚበርርም፥ በአራት እግሮችም የሚ
ሄድ ተንቀሳቃሽ ሁሉ ለእናንተ ርኩስ ነው።
፳፩ነገር ግን ከሚበርሩት፥ አራትም እግሮች ካሉ
አቸው፥ ከእግሮቻቸውም በላይ በምድር ላይ
የሚዘልሉባቸው ጭኖች ካሉአቸው ተንቀሳቃ
ሾች እነዚህን ትበላላችሁ፤ ፳፪ከእነርሱም እነ
ዚህን አትበሉም፤ ኩብኩባ የሚመስለውም፥
ፌንጣ የሚመስለውም፥ አሸን የሚመስለውም፥
አንበጣ የሚመስለውም።፩ ፳፫የሚበርር፥ አራ
ትም እግሮች ያሉት ተንቀሳቃሽ ሁሉ ለእና
ንተ ርኩስ ነው።

፳፬"በእነዚህም ርኩስ ትሆናላችሁ፤ የእነርሱ
ንም በድን የሚነካ ሁሉ እስከ ማታ ርኩስ
ነው። ፳፭ከእነርሱም በድን የሚያነሣ ሁሉ ልብ
ሱን ይጠብ፤ እስከ ማታም ርኩስ ነው። ፳፮ሰኰ
ናም ያለው፥ ነገር ግን ሰኰናው ያልተሰነጠቀ፥
የማያመሰኳም እንስሳ ሁሉ ለእናንተ ርኩስ
ነው፤ እርሱን የሚነካ ሁሉ ርኩስ ነው። ፳፯በአ
ራት እግሮቹ ከሚሄድ እንስሳ ሁሉ በመዳፎቹ
ላይ የሚሄድ ለእናንተ ርኩስ ነው፤ የእርሱን
በድን የሚነካ ሁሉ እስከ ማታ ርኩስ ነው።
፳፰በድናቸውንም የሚያነሣ ልብሱን ይጠብ፤
እስከ ማታም ርኩስ ነው። እነርሱም በእናንተ
ዘንድ ርኩሳን ናቸው።

፳፱"በምድር ላይም ከሚንቀሳቀስ ተንቀሳ
ቃሽ እነዚህ ለእናንተ ርኩሳን ናቸው፤ ሙጭ
ልጭላ፥ አይጥ፥ እንሽላሊት በየወገኑ፥ ፴ኤሊ፥
አዞ፥ ገበሎ፥ አርጃኖ፥ እስስት። ፴፩ከሚንቀሳ
ቀሱት ሁሉ በእናንተ ዘንድ ርኩሳን የሚሆኑ
እነዚህ ናቸው። ከእነርሱም በድናቸውን የሚ
ነካ ሁሉ እስከ ማታ ርኩስ ነው። ፴፪ከእነርሱም
በድናቸው በምንም ላይ ቢወድቅ እርሱ ርኩስ
ነው፤ የዕንጨት ዕቃ ወይም ልብስ ወይም ቍር
በት ወይም ከረጢት ቢሆን የሚሠራበት ዕቃ
ሁሉ እርሱን በውኃ ውስጥ ይንከሩት፤ እስከ
ማታም ርኩስ ነው፤ ከዚያም በኋላ ንጹሕ
ይሆናል። ፴፫ከእነርሱም አንዳች በውስጡ የወ
ደቀበትን የሸክላውን ዕቃ ሁሉ ስበሩት፤ በው
ስጡም ያለው ሁሉ ርኩስ ነው። ፴፬በእርሱ
ውስጥ ያለው፤ ውኃም የሚፈስስበት፥ የሚ
በላ መብል ሁሉ ርኩስ ነው፤ በዚህም ዕቃ
ሁሉ ያለው የሚጠጣ መጠጥ ሁሉ ርኩስ ነው።
፴፭ከእነዚህም በድን የሚወድቅበት ሁሉ ርኩስ
ነው፤ እቶን ወይም ምድጃ ቢሆን ይሰባበራል፤
ርኩሳን ናቸውና፤ ለእናንተ ርኩሳን ይሆናሉ።
፴፮ነገር ግን ምንጩ፥ ጉድጓዱም፥ የውኃውም
ኵሬ ንጹሓን ናቸው፤ በድናቸውን ግን የሚነካ
ርኩስ ነው። ፴፯ከበድናቸውም በሚዘራ ዘር ላይ
አንዳች ቢውድቅ እርሱ ንጹሕ ነው። ፴፰ነገር
ግን በዘሩ ላይ ውኃ ቢፈስስበት፥ ከዚህ በኋላ
ከበድናቸው አንዳች ቢወድቅበት፥ ለእናንተ
ርኩስ ነው።

፴፱"ለመብል ከሚሆኑላችሁ እንስሳት የሞተ
ቢኖር፥ በድኑን የሚነካ ሁሉ እስከ ማታ ርኩስ
ነው። ፵ከበድኑም የሚበላ ልብሱን ያጥባል፤ እስከ
ማታም ርኩስ ይሆናል፤ በድኑንም የሚያነሣ፤
ልብሱን ይጠብ፥ እስከ ማታም ርኩስ ነው።

፵፩"በምድርም ላይ የሚንቀሳቀስ ተንቀሳቃሽ
አውሬ ሁሉ ለእናንተ ርኩስ ነው፤ አትብሉትም።
፵፪በሆዱ የሚሳብ፥ በአራትም እግሮች የሚሳብ፥
ብዙ እግሮችም ያሉት፥ በምድርም ላይ የሚንቀ
ሳቀሱ ተንቀሳቃሾች ሁሉ ርኩሳን ናቸውና አት
ብሉአቸው። ፵፫በምድር ላይ በሚንቀሳቀሱ ተን
ቀሳቃሾች ሁሉ ሰውነታችሁን አታርክሱ፤ በእነ
ርሱም እንዳትረክሱ ሰውነታችሁን አታርክሱባ
ቸው። ፵፬እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና፤
ሰውነታችሁን ቀድሱ፤ ቅዱሳንም ሁኑ፤ እኔ አም
ላካችሁ እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና፤ ፵፭በምድ
ርም ላይ በሚሳብ ተንቀሳቃሽ ሁሉ ሰውነታችሁን
አታሳድፉ። እኔ አምላካችሁ እሆን ዘንድ ከግብፅ
ምድር ያወጣኋችሁ እግዚአብሔር ነኝ፤ እንግዲህ
እኔ ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ።

፵፮"የእንስሳና የወፍ፥ በውኃውም ውስጥ የሚ
ንቀሳቀስ የፍጥረት ሁሉ፥ በምድርም ላይ የሚ
ንቀሳቀስ የፍጥረት ሁሉ ሕግ ይህ ነው። ፵፯በር
ኩስና በንጹሕ መካከል፥ የሕይወት ነፍስ ካላ
ቸውም በምትበሉትና በማትበሉት መካከል እን
ድትለዩ ነው።"

## ምዕራፍ ፲፪

### ሴት ከወለደች በኋላ ከሕርስ ስለምትነጻበት ጊዜ

፩እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተና
ገረው፦ ፪"ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ

፩ ምዕ. ፲፩ በቍ. ፳፪ የተገለጹት በዕብ. እና በግሪክ ሰባ. ሊ. "የሚበሉ ናቸው"

ተናገራቸው፡- ሴት ብታረግዝ ወንድ ልጅም
ብትወልድ፥ ሰባት ቀን ያህል የረከሰች ናት፤
፫እንደ ግዳጅዋ ወራት ትረክሳለች። በስምንተኛ
ውም ቀን ልጁ ከሥጋው ሸለፈት ይገረዝ። ፬ከደ
ምዋም እስክትነጻ ሠላሳ ሦስት ቀን ትቈይ፤
የመንጻቷ ቀንም እስኪፈጸም ድረስ የተቀደሰን
ነገር አትንካ፤ ወደ መቅደስም አትግባ። ፭ሴት
ልጅም ብትወልድ እንደ ግዳጅዋ ወራት ሁለት
ሳምንት ያህል የረከሰች ናት፤ ከደምዋም እስክ
ትነጻ ድረስ ስድሳ ስድስት ቀን ትቈይ።

፮"የመንጻቷ ወራትም በተፈጸመ ጊዜ፥ ለወ
ንድ ልጅ ወይም ለሴት ልጅ፥ የአንድ ዓመት
ጠቦት ለሚቃጠል መሥዋዕት፥ የርግብም ግል
ገል ወይም ዋኖስ ለኀጢአት መሥዋዕት ወደ
ምስክሩ ድንኳን ደጃፍ ወደ ካህኑ ታመጣለች።
፯ካህኑም በእግዚአብሔር ፊት ያቀርበዋል፤ ያስ
ተሰርይላትማል፤ ከደምዋም ፈሳሽ ትነጻለች።
ወንድ ወይም ሴት ለምትወልድ ሴት ሕጉ ይህ
ነው። ፰ጠቦት ለማምጣት የሚበቃ ገንዘብ በእ
ጅዋ ባይኖራት ሁለት ዋኖሶች፥ ወይም ሁለት
የርግብ ግልገሎች፥ አንዱን ለሚቃጠል መሥ
ዋዕት፥ ሌላውንም ለኀጢአት መሥዋዕት ታቀ
ርባለች፤ ካህኑም ያስተሰርይላታል፤ እርስዋም
ትነጻለች።"

## ምዕራፍ ፲፫

### የለምጽ ደዌ ሕግ

፩እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዲህ
ብሎ ተናገራቸው፡- ፪"ሰው በሥጋው ቆዳ ላይ
እባጭ ብትወጣበት፥ ብትነጣም፥ በሥጋውም
ቆዳ እንደ ለምጽ ደዌ ብትመስል፥ ወደ ካህኑ
ወደ አሮን ወይም ከካህናቱ ልጆች ወደ አንዱ
ያምጡት። ፫ካህኑም በሥጋው ቆዳ ያለችውን
ያችን ደዌ ይያት፤ ጠጕሯም ተለውጣ ብት
ነጣ በሥጋው ቆዳ ያለች የዚያች ደዌ መልክ
ቢከፋ፥ ደዌውም ወደ ሥጋው ቆዳ ቢጠልቅ፥
እርስዋ የለምጽ ደዌ ናት፤ ካህኑም አይቶ፡-
'ርኩስ ነው' ይበለው። ፬ቋቍቻውም በሥጋው
ቆዳ ላይ ቢነጣ፥ ከቆዳውም የጠለቀ ባይመ
ስል፥ ጠጕሩም ባይነጣ፥ ካህኑ የታመመውን
ሰው ሰባት ቀን ይዘጋበታል። ፭በሰባተኛውም
ቀን ካህኑ ያችን ደዌ ይያት፤ እነሆም፥ ያች
ደዌ በፊት እንደ ነበረች ብትሆን፥ በቆዳውም
ላይ ባትሰፋ፥ ካህኑ ሰባት ቀን ደግሞ ይለየ
ዋል። ፮ደግሞ በሰባተኛው ቀን ካህኑ ያየዋል፤
እነሆም፥ ያች ደዌ ብትከስም፥ በቆዳውም ላይ
ባትሰፋ፥ ካህኑ፡- 'ንጹሕ ነው' ይለዋል፤ ምል
ክት[፩] ነውና፥ ልብሱንም አጥቦ ንጹሕ ይሆ
ናል። ፯ስለ መንጻቱ በካህኑ ዘንድ ከታየ በኋላ
ምልክቱ በቆዳው ላይ ቢሰፋ፥ እንደገና ሊታይ
ወደ ካህኑ ይቀርባል። ፰ካህኑም ያያል፤ እነ
ሆም፥ ምልክቱ በቆዳው ላይ ቢሰፋ ካህኑ፡-
'ርኩስ ነው' ይለዋል፤ ለምጽ ነውና።

፱"የለምጽ ደዌ በሰው ላይ ቢወጣ እርሱ ወደ
ካህኑ ይሄዳል። ፲ካህኑም ያየዋል፤ እነሆም፥
በቆዳው ላይ ነጭ እባጭ ቢሆን፥ ጠጕሩም
ተለውጦ ቢነጣ፥ ሥጋውም በእባጩ ውስጥ
ቢያዥ፥ ፲፩እርሱ በሥጋው ቆዳ ላይ አሮጌ
ለምጽ ነው፤ ካህኑም፡- 'ርኩስ ነው' ይለዋል፤
እርሱ ርኩስ ነውና ይለየዋል። ፲፪ለምጹም በቆ
ዳው ላይ ሰፍቶ ቢወጣ፥ ለምጹም የታመመ
ውን ሰው ቆዳውን ሁሉ ከራሱ እስከ እግሮቹ
ድረስ እንደ ከደነው ለካህኑ ቢመስለው፤ ፲፫ካህኑ
ያየዋል፤ እነሆም፥ ለምጹ ቆዳውን ሁሉ ቢከ
ድን የታመመውን ሰው፡- ካህኑ 'ንጹሕ ነህ'
ይለዋል፤ ሁለመናው ተለውጦ ነጭ ሆኖአልና
ንጹሕ ነው። ፲፬ደዌው በታየበት ቀን ጤነኛው
ቆዳ ርኩስ ይሆናል። ፲፭ካህኑም ጤነኛውን ቆዳ
አይቶ፡- 'ርኩስ ነው' ይለዋል፤ ስለዚህ ለምጽ
ነውና ርኩስ ነው። ፲፮ጤነኛው ቆዳ ተመልሶ
ቢነጣ እንደገና ወደ ካህኑ ይመጣል። ፲፯ካህኑም
ያየዋል፤ እነሆም፥ ደዌው ቢነጣ ካህኑ የታመመ
ውን፡- 'ንጹሕ ነው' ይለዋል፤ ንጹሕ ነውና።

፲፰"በሥጋውም ቆዳ ላይ ቍስል ቢሆንና
ቢሽር፥ ፲፱በቍስሉም ስፍራ ነጭ እባጭ ወይም
ቀላ ያለ ቋቍቻ ቢወጣ፥ በካህኑ ዘንድ ይታያል።
፳ካህኑም ያያል፤ እነሆም፥ ወደ ቆዳው ውስጥ
ጠልቆ ቢታይ፥ ጠጕሩም ተለውጦ ቢነጣ፥
ካህኑ፡- 'ርኩስ ነው' ይለዋል፤ የለምጽ ደዌ ነው፤
ከቍስሉ ውስጥ ወጥቶአል። ፳፩ካህኑም ቢያየው፥
ነጭም ጠጕር ባይኖርበት፥ ወደ ቆዳውም ውስጥ
ባይጠልቅ ነገር ግን ቢከስም፥ ካህኑ ሰባት ቀን
ይለየዋል። ፳፪በቆዳውም ላይ ቢሰፋ፥ ካህኑ፡-
'ርኩስ ነው' ይለዋል፤ የለምጽ ደዌ ነው፤ በእት
ራቱ ላይ ወጥቶአልና። ፳፫ያች ደዌ ግን በስፍራዋ
ብትቆም፥ ባትሰፋም፥ የቍስል እትራት ናት፤
ካህኑም፡- 'ንጹሕ ነው' ይለዋል።

፳፬"በሥጋውም ቆዳ የእሳት ትኩሳት ቢኖር
በት፥ በተቃጠለውም ስፍራ ነጭ፥ ወይም ቀላ

---

፩ ዕብ. "እከክ" ይላል።

ያለ ቋቍቻ ቢታይ፥ ፳፭ካህኑ ያየዋል፤ እነሆም፥
በቋቁቻው ጠጕሩ ተለውጦ ቢነጣ፥ ወደ ቆዳ
ውም ውስጥ ቢጠልቅ፥ ለምጽ ነው፤ ከተቃጠለ
ውም ስፍራ ወጥቶአል፤ ካህኑም፦ ‘ርኩስ ነው’
ይለዋል፤ የለምጽ ደዌ ነውና። ፳፮ካህኑም ቢያ
የው፥ በቋቍቻውም ነጭ ጠጕር ባይኖር፥ ወደ
ቆዳውም ባይጠልቅ፥ ነገር ግን ቢከስም፥ ካህኑ
ሰባት ቀን ይለየዋል። ፳፯ካህኑም በሰባተኛው ቀን
ያየዋል፤ በቆዳውም ላይ ቢሰፋ ካህኑ፦ ‘ርኩስ
ነው’ ይለዋል፤ የለምጽ ደዌ ነውና በእትራቱ
ላይ ወጥቶአል። ፳፰ቋቍቻውም በስፍራው ላይ
ቢቆም፥ በቆዳውም ላይ ባይሰፋ፥ ነገር ግን ቢከ
ስም፥ የትኩሳት እባጭ ነው፤ የትኩሳትም ጠባሳ
ነውና ካህኑ፦ ‘ንጹሕ ነው’ ይለዋል።

፳፱“ማናቸውም ወንድ ወይም ሴት በራሱ
ወይም በአገጩ የለምጽ ደዌ ቢኖርበት፥ ካህኑ
የለምጹን ደዌ ያያል፤ ፴እነሆም፥ ወደ ቆዳው
ቢጠልቅ፥ በውስጡም ቀጭን ብጫ ጠጕር ቢኖ
ርበት፥ ካህኑ፦ ‘ርኩስ ነው’ ይለዋል፤ ቈረ
ቈር ነው፤ የራስ ወይም የአገጭ ለምጽ ነው።
፴፩ካህኑም የቈረቈሩን ደዌ ቢያይ፥ ወደ ቆዳ
ውም ባይጠልቅ፥ ጥቁርም ጠጕር ባይኖርበት፥
ካህኑ የቈረቈር ደዌ ያለበትን ሰው ሰባት ቀን
ይለየዋል። ፴፪ካህኑም በሰባተኛው ቀን ደዌውን
ያያል፤ እነሆም፥ ቈረቈሩ ባይሰፋ፥ በውስጡም
ብጫ ጠጕር ባይኖር፥ የቈረቈሩም መልክ ወደ
ቆዳው ባይጠልቅ፤ ይላጫል፤ ፴፫ቈረቈሩ ግን
አይላጭም፤ ካህኑም ቈርቈር ያለበትን ሰው
ሰባት ቀን ደግሞ ይለየዋል። ፴፬ካህኑም በሰባተ
ኛው ቀን ቈረቈሩን ያያል፤ እነሆም፥ ከተላጨ
በኋላ ቈረቈሩ በቆዳው ላይ ባይሰፋ፥ መል
ኩም ወደ ቆዳው ባይጠልቅ፥ ካህኑ፦ ‘ንጹሕ
ነው’ ይለዋል፤ ልብሱን አጥቦ ንጹሕ ይሆናል።
፴፭ከነጻ በኋላ ግን ቈረቈሩ በቆዳው ላይ ቢሰፋ፥
ካህኑ ያየዋል፤ ፴፮እነሆም፥ ቈረቈሩ በቆዳው
ላይ ቢሰፋ ካህኑ ብጫውን ጠጕር አይፈል
ግም፤ ርኩስ ነውና። ፴፯ቈረቈሩ ግን ፊት እንደ
ነበረ በቦታው ቢኖር፥ ጥቁርም ጠጕር ቢበቅል
በት፥ ቈረቈሩ ሸሮአል፤ እርሱም ንጹሕ ነው፤
ካህኑም፦ ‘ንጹሕ ነው’ ይለዋል።

፴፰“ማናቸውም ወንድ ወይም ሴት በሥጋው
ቆዳ ላይ ነጭ ቋቍቻ ቢኖርበት፥ ፴፱ካህኑ ያያል፤
እነሆም፥ በሥጋቸው ቆዳ ላይ ያለው ቋቍቻ
ፈገግ ቢል አጓጉት ነው፤ ከቆዳው ውስጥ ወጥ
ቶአል፤ ንጹሕ ነው።

፵“የሰውም ጠጕር ከራሱ ቢመለጥ እርሱ
በራ ነው፤ ነገር ግን ንጹሕ ነው። ፵፩ጠጕሩ
ከግንባሩ ቢመለጥ እርሱ ራሰ በራ ነው፤ ነገር
ግን ንጹሕ ነው። ፵፪በቡሀነቱ ወይም በራሰ በራ
ነቱ ነጭ፥ ወይም ቀላ ያለ ደዌ ቢኖርበት፥
እርሱ ከቡሀነቱ ወይም ከራሰ በራነቱ የወጣ
ለምጽ ነው። ፵፫ካህኑም ያየዋል፤ እነሆም፥ የደ
ዌው እብጠት በሥጋው ቆዳ ላይ የሆነ ለምጽ
መስሎ፥ በቡሀነቱ ወይም በራሰ በራነቱ ነጭ
ወይም ቀላ ያለ ቢሆን፥ ፵፬ለምጻም ሰው ነው፤
ርኩስ ነው፤ ካህኑ፦ በርግጥ ‘ርኩስ ነው’ ይለ
ዋል፤ ደዌው በራሱ ነው።

፵፭“የለምጽ ደዌ ያለበት ሰው ልብሱ የተቀ
ደደ ይሁን፤ ራሱም የተገለጠ ይሁን፤ ከንፈሩ
ንም ይሸፍን፤ ርኩስ ይባላል። ፵፮ደዌው ባለ
በት ዘመን ሁሉ ርኩስ ይሆናል፤ እርሱ ርኩስ
ነው፤ ብቻውን ይቀመጣል፤ መኖሪያውም ከሰ
ፈር በውጭ ይሆናል።

## በልብስ ላይ ስለሚታይ
## የለምጽ ደዌ ምልክት ሕግ

፵፯“የለምጽም ደዌ በልብስ ላይ ቢሆን፥
ልብሱም የበግ ጠጕር ወይም የተልባ እግር
ቢሆን፥ ፵፰በድሩ ወይም በማጉ ላይ ቢሆን፥
የበግ ጠጕር ወይም የተልባ እግር ቢሆን፥ ቆዳ
ወይም ከቆዳ የሚደረግ ነገር ቢሆን፥ ፵፱ደዌው
በልብሱ ወይም በቆዳው ወይም በድሩ ወይም
በማጉ ወይም ከቆዳ በሚደረገው ነገር አረንጓዴ
ወይም ቀይ ቢሆን፥ የለምጽ ደዌ ነው፤ ለካህኑ
ያሳያል። ፶ካህኑም ደዌውን አይቶ ደዌው ያለ
በትን ነገር ሰባት ቀን ይለየዋል። ፶፩በሰባተኛ
ውም ቀን ደዌውን ያያል፤ ደዌውም በልብስ
ላይ ወይም በድሩ ወይም በማጉ ወይም በቆ
ዳው ወይም ከቆዳው በሚደረግ ነገር ቢሰፋ፥
ደዌው እየፋገ የሚሄድ ለምጽ ነው፤ ርኩስ
ነው። ፶፪ልብሱን ያቃጥላል፤ ድሩ ወይም ማጉ
የበግ ጠጕር ወይም የተልባ እግር ቢሆን ወይም
ከቆዳ የተደረገ ቢሆን፥ ደዌ ያለበት ሁሉ እየፋገ
የሚሄድ ለምጽ ነውና በእሳት ይቃጠላል።

፶፫“ካህኑ ቢያይ፥ እነሆም፥ ደዌው በድሩ
ወይም በማጉ ወይም ከቆዳ በተደረገ ነገር ቢሆን
በልብሱ ላይ ባይሰፋ፥ ፶፬ካህኑ ደዌ ያለበቱ ነገር
እንዲታጠብ ያዝዛል፤ ሌላም ሰባት ቀን ይለየ
ዋል። ፶፭ደዌውም ከታጠበ በኋላ ካህኑ ያየዋል፤
እነሆም፥ ደዌው መልኩን ባይለውጥ፥ ባይሰ
ፋም፥ ርኩስ ነው፤ በእሳት ያቃጥሉታል፤ በልብ
ሱም ውስጥ በማጉም፥ በድሩም ወጥቶአልና።

፶፮“ካህኑም ቢያይ፥ እነሆ፥ ደዌው ከታጠበ
በኋላ ቢከስም፥ ከልብሱ ወይም ከድሩ ወይም

ከማጉ ወይም ከቆዳው ይቅደደው። ፶፯በል
ብሱም ወይም በድሩ ወይም በማጉ ወይም
ከቆዳ በተደረገ ነገር ላይ ደግሞ ቢታይ፥ የወጣ
ለምጽ ነው፤ ደዌው ያለበትን ነገር ያቃጥሉት።
፶፰ልብሱ ወይም ድሩ ወይም ማጉ ወይም ከቆዳ
የተደረገው ነገር ከታጠበ በኋላ ደዌው ቢለቅ
ቀው ሁለተኛ ጊዜ ይታጠባል፤ ንጹሕም ይሆ
ናል።

፶፱"በበግ ጠጉር ልብስ፥ ወይም በተልባ እግር
ወይም በድሩ ወይም በማጉ ወይም ከቆዳ በተ
ደረገ ነገር ላይ ቢሆን፥ ንጹሕ ወይም ርኩስ
ያሰኝ ዘንድ የለምጽ ደዌ ሕግ ይህ ነው።"

## ምዕራፍ ፲፬

### ከለምጽ ደዌ የመንጻት ሕግ

፩እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገ
ረው፡- ፪"ለምጽ ለያዘው ሰው ሕጉ ይህ ነው፤
ከለምጽ በነጻበት ቀን ወደ ካህኑ ይወስዱታል።
፫ካህኑም ከሰፈር ወደ ውጭ ይወጣል፤ ካህ
ኑም ያየዋል፤ ፬እነሆም፥ የለምጹ ደዌ ከለም
ጻሙ ላይ ቢጠፋ፥ ካህኑ ስለሚነጻው ሰው
ሁለት ንጹሓን ዶሮዎች በሕይወታቸው፥ የዝ
ግባም ዕንጨት፥ ቀይ ግምጃም፥ ሂሶጵም[፩]
ያመጣ ዘንድ ያዝዛል። ፭ካህኑም ከሁለቱ ዶሮ
ዎች አንደኛዋን በሸክላ ዕቃ ውስጥ በምንጭ
ውኃ ላይ ያርድ ዘንድ ያዝዛል። ፮ያልታረደች
ውንም ዶሮ፥ ዝግባውንም ዕንጨት፥ ቀዩንም
ግምጃ፥ ሂሶጱንም ወስዶ በምንጭ ውኃ ላይ
በታረደችው ዶሮ ደም ውስጥ ይነክራቸዋል።
፯ከለምጹም በሚነጻው ሰው ላይ ሰባት ጊዜ
ይረጫል፤ ንጹሕም ይሆናል፤ ያልታረደችውን
ዶሮ ወደ ሜዳ ይለቅቃታል። ፰የነጻውም ሰው
ልብሱን ያጥባል፤ ጠጕሩንም ሁሉ ይላጫል፤
በውኃም ይታጠባል፤ ንጹሕም ይሆናል። ከዚ
ያም በኋላ ወደ ሰፈር ይገባል፤ ነገር ግን ከቤቱ
በውጭ ሆኖ ሰባት ቀን ይቀመጣል። ፱በሰባተኛ
ውም ቀን ጠጕሩን ሁሉ ይላጫል፤ ራሱንም፥
ጢሙንም፥ ቅንድቡንም፥ የገላውንም ጠጕር
ሁሉ ይላጫል፤ ልብሱንም፥ ገላውንም በውኃ
ያጥባል፤ ንጹሕም ይሆናል።

፲"በስምንተኛው ቀን ነውር የሌለባቸውን፥
ዓመት የሞላቸውን ሁለት ተባት የበግ ጠቦ
ቶች፥ ነውር የሌለባትንም አንዲት የዓመት እን
ስት የበግ ጠቦት፥ ስለ እህልም ቍርባን ከመ
ስፈሪያው ከዐሥር እጅ ሦስት እጅ የሆነ፥ በዘ
ይት የተለወሰ መልካም የስንዴ ዱቄት፥ አንድ
ማሰሮ ዘይትም ይወስዳል። ፲፩የሚያነጻውም
ካህን እነዚህን ነገሮች፥ የሚነጻውንም ሰው በም
ስክሩ ድንኳን ደጃፍ አጠገብ በእግዚአብሔር
ፊት ያቀርባቸዋል። ፲፪ካህኑም አንዱን ጠቦት
ወስዶ ስለ በደል መሥዋዕት ያቀርባል፤ ያንም
አንድ ማሰሮ ዘይት ስለ ልዩ ቍርባን በእግዚአ
ብሔር ፊት ይለየዋል። ፲፫የኀጢአትን መሥዋዕ
ትና የሚቃጠለውን መሥዋዕት በሚያርዱበት
በተቀደሰው ስፍራ ጠቦቱን ያርዱታል፤ የበደሉ
መሥዋዕት ለካህኑ እንደሚሆን፥ እንዲሁ የኀጢ
አቱ መሥዋዕት ነውና፤[፪] ቅዱስ ቅዱሳን ነው።
፲፬ካህኑም ከበደል መሥዋዕት ደም ወስዶ የሚ
ነጻውን ሰው የቀኝ ጆሮውን ጫፍ፥ የቀኝ እጁ
ንም አውራ ጣት፥ የቀኝ እግሩንም አውራ ጣት
ይቀባዋል። ፲፭ካህኑም ከማሰሮው ዘይት ወስዶ
በግራ እጁ ውስጥ ያፈስሰዋል። ፲፮ካህኑም በግራ
እጁ ውስጥ ባለው ዘይት ቀኝ ጣቱን ነክሮ ከዘ
ይቱ በእግዚአብሔር ፊት ሰባት ጊዜ በጣቱ
ይረጫል። ፲፯ካህኑም በእጁ ውስጥ ከቀረው
ዘይት የሚነጻውን ሰው የቀኝ ጆሮውን ጫፍ፥
የቀኝ እጁንም አውራ ጣት፥ የቀኝ እግሩንም
አውራ ጣት የበደል መሥዋዕት ደም ባረፈበት
ላይ ይቀባዋል። ፲፰በካህኑም እጅ ውስጥ የቀረ
ውን ዘይት ካህኑ በሚነጻው ሰው ራስ ላይ ያደ
ርግበታል፤ ካህኑም በእግዚአብሔር ፊት ያስተ
ሰርይለታል። ፲፱ካህኑም የኀጢአቱን መሥዋዕት
ያቀርባል፤ ካህኑም ከኀጢአቱ ለማንጻት ለሚ
ነጻው ሰው ያስተሰርይለታል፤ ከዚህም በኋላ
ካህኑ የሚቃጠለውን መሥዋዕት ያርዳል። ፳ካህ
ኑም የሚቃጠለውን መሥዋዕትና የእህሉን ቍር
ባን በመሠዊያው ላይ በእግዚአብሔር ፊት ያቀ
ርባል፤ ካህኑም ያስተሰርይለታል፤ እርሱም
ንጹሕ ይሆናል።

፳፩"ድሃም ቢሆን፥ በእጁም ገንዘብ ባይኖ
ረው፥ ማስተስረያ ይሆንለት ዘንድ አንድ
ጠቦት ስለ በደል የመለየት መሥዋዕት፥ ከመስ
ፈሪያውም ከዐሥር እጅ አንድ እጅ የሆነ በዘ
ይት የተለወሰ የስንዴ ዱቄት ለቍርባን፥ አንድ
ማሰሮ ዘይትም ያመጣል። ፳፪ሁለት ዋኖሶች፥
ወይም ሁለት የርግብ ግልገሎች በእጁ እንዳገኘ
አንዲቱን ለኀጢአት መሥዋዕት፥ አንዲቱንም

---

፩ ስሚዛ

፪ ዕብ. "የኀጢአቱ መሥዋዕት ለካህኑ እንደሚሆን እንዲሁ የበደል መሥዋዕት ነውና" ይላል።

ለሚቃጠል መሥዋዕት ይወስዳል። ፳፫በስምንተ
ኛውም ቀን ያነጹት ዘንድ ወደ ካህኑ ወደ ምስ
ክሩ ድንኳን ደጃፍ በእግዚአብሔር ፊት ያመ
ጣቸዋል። ፳፬ካህኑም የበደሉን መሥዋዕት የበግ
ጠቦት የማሰሮውንም ዘይት ይወስዳል፤ በእግ
ዚአብሔርም ፊት ለቍርባን ያቀርበዋል። ፳፭የበ
ደሉንም መሥዋዕት የበግ ጠቦት ያርዳል፤ ካህ
ኑም ከበደሉ መሥዋዕት ደም ወስዶ የሚነጻ
ውን ሰው የቀኝ ጆሮውን ጫፍ፥ የቀኝ እጁንም
አውራ ጣት፥ የቀኝ እግሩንም አውራ ጣት ይቀ
ባዋል። ፳፮ካህኑም ከዘይቱ በግራ እጁ ውስጥ
ያፈስሰዋል። ፳፯ካህኑም በግራ እጁ ውስጥ ከአ
ለው ዘይት በቀኝ ጣቱ ሰባት ጊዜ በእግዚአብ
ሔር ፊት ይረጨዋል። ፳፰ካህኑም በእጁ ውስጥ
ከአለው ዘይት የሚነጻውን ሰው የቀኝ ጆሮውን
ጫፍ፥ የቀኝ እጁንም አውራ ጣት፥ የቀኝ እግ
ሩንም አውራ ጣት የበደል መሥዋዕት ደም
ባረፈበት ላይ ይቀባዋል። ፳፱በካህኑ እጅ ውስጥ
የቀረውን ዘይት በሚነጻው ሰው ራስ ላይ ያደ
ርገዋል፤ ካህኑም በእግዚአብሔር ፊት ያስተሰ
ርይለታል። ፴በእጁ ከአለው ከዋኖሶች ወይም
ከርግብ ግልገሎች አንዱን ያቀርባል። ፴፩አንዲ
ቱን ለኀጢአት መሥዋዕት፥ ሌላዪቱንም ከእ
ህል ቍርባን ጋር ለሚቃጠል መሥዋዕት ያቀር
ባል፤ ካህኑም ለሚነጻው ሰው በእግዚአብሔር
ፊት ያስተሰርይለታል። ፴፪ለመንጻቱ የሚያስፈል
ገውን ነገር ለማያገኝ የለምጽ ደዌ ላለበት ሰው
ሕጉ ይህ ነው።”

## በቤት ላይ ስለሚታይ
## የለምጽ ደዌ ምልክት ሕግ

፴፫እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን እንዲህ
ብሎ ተናገራቸው፦ ፴፬“ትወርሱአት ዘንድ እኔ
ወደምሰጣችሁ ርስት ወደ ከነዓን ምድር በገባ
ችሁ ጊዜ፥ እኔም የለምጽ ደዌ ምልክት በርስ
ታችሁ ምድር ቤቶች ባደረግሁ ጊዜ፥ ፴፭ባለ
ቤቱ መጥቶ ካህኑን፦ ‘ደዌ በቤቴ ውስጥ እን
ዳለ አይቻለሁ’ ብሎ ይንገረው። ፴፮ካህኑም
በቤቱ ውስጥ ያለው ዕቃ ሁሉ እንዳይረክስ፥
እርሱ የለምጹን ምልክት ለማየት ወደ ቤት ሳይ
ገባ፥ ቤቱን ባዶ እንዲያደርጉት ያዝዛል፤ በኋ
ላም ካህኑ ቤቱን ለማየት ይገባል። ፴፯የለምጹ
ንም ምልክት ያያል፤ እነሆም፥ የለምጹ ምል
ክት በግንቡ ላይ በአረንጓዴና በቀይ ቢዥጐረ
ጐር፥ መልኩም ወደ ግንቡ ውስጥ ቢጠልቅ፥
፴፰ካህኑ ከቤቱ ውስጥ ወደ ቤቱ በር ወጥቶ
ሰባት ቀን ቤቱን ይዘጋዋል። ፴፱ካህኑም በሰባ
ተኛው ቀን ተመልሶ ቤቱን ያያል፤ ፵እነሆም፥
ደዌው በቤቱ ግንብ ላይ ቢሰፋ፥ ካህኑ ደዌ
ያለባቸውን ድንጋዮች እንዲያወጡ፥ ከከተማ
ውም ወደ ውጭ ወደ ረከሰው ስፍራ እንዲጥሉ
አቸው ያዝዛል። ፵፩ቤቱንም በውስጡ በዙሪያው
ያስፍቀዋል፤ የፋቁትንም የምርጊቱን አፈር ከከ
ተማው ወደ ውጭ ወደ ረከሰ ስፍራ ያፈስሱ
ታል። ፵፪በእነዚያም ድንጋዮች ስፍራ ሌሎች
ድንጋዮችን ያገባሉ፤ ሌላም ጭቃ ወስደው
ቤቱን ይመርጉታል።

፵፫“ደዌውም ዳግም ቢመለስ፥ ድንጋዮቹም
ከወጡ፥ ቤቱም ከተፋቀና ከተመረገ በኋላ
በቤቱ ውስጥ ቢሰፋ፥ ፵፬ካህኑ ገብቶ ያያል፤
እነሆም፥ ደዌው በቤቱ ውስጥ ቢሰፋ፥ በቤቱ
ውስጥ ያለው እየፋገ የሚሄድ ለምጽ ነው፤
ርኩስ ነው። ፵፭ቤቱንም፥ ድንጋዮቹንም፥ ዕን
ጨቱንም፥ የቤቱንም ምርጊት ሁሉ ያፈርሳል፤
እነርሱንም ከከተማው ወደ ውጭ ወደ ርኩስ
ስፍራ ያወጣል። ፵፮በተዘጋበትም ጊዜ ሁሉ ወደ
ቤቱ የሚገባ እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ይሆናል።
፵፯በቤቱም የሚተኛ ልብሱን ያጥባል፤ እስከ
ማታም ርኩስ ነው፤ በቤቱም የሚበላ ልብሱን
ያጥባል፤ እስከ ማታም ርኩስ ነው።

፵፰“ካህኑም ገብቶ ቢያየው፥ እነሆም፥ ቤቱ ከተ
መረገ በኋላ ደዌው በቤቱ ውስጥ ባይሰፋ፥ ደዌው
ስለ ሻረ ካህኑ ቤቱን፦ ንጹሕ ነው ይለዋል። ፵፱ካህ
ኑም ቤቱን ለማንጻት ሁለት ዶሮዎች፥ የዝግባ ዕን
ጨት፥ ቀይ ግምጃ፥ ሂሶጵም[፫] ይወስዳል። ፶አንደ
ኛዪቱንም ዶሮ በሸክላ ዕቃ ውስጥ ከምንጩ ውኃ
በላይ ያርዳል። ፶፩የዝግባውን ዕንጨት፥ ሂሶጱንም፥
ቀዩንም ግምጃ፥ ደኅነኛዪቱንም ዶሮ ወስዶ በታ
ረደችው ዶሮ ደምና በምንጩ ውኃ ውስጥ ይነክ
ራቸዋል፥ ቤቱንም ሰባት ጊዜ ይረጨዋል። ፶፪ቤቱ
ንም በዶሮዪቱ ደም በምንጩም ውኃ፥ በደኅነኛ
ዪቱም ዶሮ፥ በዝግባውም ዕንጨት፥ በሂሶጱም፥
በቀዩም ግምጃ ያነጻዋል። ፶፫ደኅነኛዪቱንም ዶሮ
ከከተማ ወደ ሜዳ ይሰድዳታል፤ ለቤቱም ያስተሰ
ርይለታል፤ ንጹሕም ይሆናል።

፶፬“ይህም ሕግ ነው፤ ለሁሉ ዓይነት ለምጽና
የቈረቈር ደዌ ሕጉ ይህ ነው፤ ፶፭በልብስና በቤ
ትም ላለ ለምጽ፥ ፶፮ለዕባጭም፥ ለብጕርም፥
ለቋቍቻም፤ ፶፯በሚረክስና በሚነጻ ጊዜ እንዲ
ያስታውቅ ይህ የለምጽ ሕግ ነው።”

---

፫ ሰሚዛ

## ምዕራፍ ፲፭

### ከሰውነቱ ፈሳሽ ስለሚፈስ ሰው ሰው የመንጻት ሕግ

፩እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን እንዲህ
ብሎ ተናገራቸው፥ ፪"ለእስራኤል ልጆች እን
ዲህ ብላችሁ ንገሩአቸው፦ ከሰውነቱ ዘር የሚ
ፈስሰው ሰው ቢኖር ስለሚፈስሰው ነገር ርኩስ
ነው። ፫ከሰውነቱ ፈሳሽ ለሚፈስሰው ሰው የር
ኵሰቱ ሕግ ይህ ነው፤ ፈሳሽ የሚፈስሰው ሰው
ፈሳሹ እየፈሰሰው በሚኖርበት ጊዜ ሁሉ ርኩስ
ነው፤ ፈሳሹ ያረክሰዋል። ፬ፈሳሽ ነገር ያለበት
ሰው የሚተኛበት መኝታ ሁሉ ርኩስ ነው፤
የሚቀመጥበትም ነገር ሁሉ ርኩስ ነው። ፭መኝ
ታውንም የሚነካ ሰው ሁሉ ልብሱን ይጠብ፤
በውኃም ሰውነቱን ይታጠብ፤ እስከ ማታም
ድረስ ርኩስ ነው። ፮ፈሳሽ ነገር ያለበት ሰው
በተቀመጠበት ነገር ላይ የሚቀመጥበት ሰው
ልብሱን ይጠብ፤ በውኃም ይታጠብ፤ እስከ
ማታም ድረስ ርኩስ ነው። ፯ፈሳሽ ነገር ያለ
በትን የሰውን ሥጋ የሚነካ ልብሱን ይጠብ፤
በውኃም ይታጠብ፤ እስከ ማታም ድረስ ርኩስ
ነው። ፰ፈሳሽ ነገር ያለበት ሰው በንጹሕ ሰው
ላይ ቢተፋ ልብሱን ይጠብ፤ በውኃም ይታ
ጠብ፤ እስከ ማታም ድረስ ርኩስ ነው። ፱ፈሳሽ
ነገር ያለበት ሰው የተቀመጠበት ኮርቻ ሁሉ
ርኩስ ነው። ፲ከበታቹም ያለውን ነገር የሚ
ነካ ሁሉ እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው፤ እነዚ
ህንም ነገሮች የሚያነሣ ሁሉ ልብሱን ይጠብ፤
በውኃም ይታጠብ፤ እስከ ማታም ድረስ ርኩስ
ነው። ፲፩ፈሳሽ ነገር ያለበት ሰው እጁን በውኃ
ሳይታጠብ የሚነካው ሁሉ ልብሶቹን ይጠብ፤
በውኃም ይታጠብ፤ እስከ ማታም ርኩስ ነው።
፲፪ፈሳሽ ነገር ያለበት ሰው የሚነካውን የሸክላ
ዕቃ ይስበሩት፤ የዕንጨቱንም ዕቃ ሁሉ በውኃ
ይጠቡት፤ ንጹሕም ይሆናል።

፲፫"ፈሳሽ ነገር ያለበት ሰው ከፈሳሹ ነገር
ሲነጻ ስለ መንጻቱ ሰባት ቀን ይቈጥራል፤ ልብ
ሶቹንም ያጥባል፤ ገላውንም በምንጭ ውኃ
ይታጠባል፤ ንጹሕም ይሆናል። ፲፬በስምንተኛ
ውም ቀን ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት የርግብ
ግልገሎች ይዞ ወደ ምስክሩ ድንኳን ደጃፍ በእ
ግዚአብሔር ፊት ያመጣል፤ ለካህኑም ይሰጠ
ዋል። ፲፭ካህኑም አንዲቱን ለኀጢአት መሥዋ
ዕት፥ አንዲቱንም ለሚቃጠል መሥዋዕት ያቀ
ርባል፤ ካህኑም በእግዚአብሔር ፊት ስለ ፈሳሹ
ነገር ሁሉ ያስተሰርይለታል።

፲፮"ማንም ሰው ዘር ከእርሱ ቢወጣ፥[፩] ገላ
ውን ሁሉ በውኃ ይታጠባል፤ እስከ ማታም
ርኩስ ነው። ፲፯ዘር የነካው ልብስ ሁሉ፥ ቍር
በትም ሁሉ በውኃ ይታጠባል፤ እስከ ማታም
ድረስ ርኩስ ነው። ፲፰ሴት ፈሳሽ ከአለበት
ወንድ ጋር ብትገናኝ ሁለቱም በውኃ ይታጠ
ባሉ፤ እስከ ማታም ድረስ ርኩሳን ናቸው።

፲፱"ሴት ፈሳሽ ነገር ቢኖርባት፥ በሥጋዋም
ያለው ፈሳሽ ነገር ደም ቢሆን፥ በግዳጅዋ ሰባት
ቀን ትቀመጣለች፤ የሚነካትም ሁሉ እስከ ማታ
ድረስ ርኩስ ነው። ፳በግዳጅም ሳለች የምትተኛ
በት ነገር ሁሉ ርኩስ ነው፤ የምትቀመጥበትም
ነገር ሁሉ ርኩስ ነው። ፳፩መኝታዋንም የሚነካ
ሁሉ ልብሶቹን ያጥባል፤ በውኃም ሰውነቱን
ይታጠባል፤ እስከ ማታም ድረስ ርኩስ ነው።
፳፪የምትቀመጥበትንም ነገር ሁሉ የሚነካ ሁሉ
ልብሶቹን ያጥባል፤ በውኃም ሰውነቱን ይታ
ጠባል፤ እስከ ማታም ርኩስ ነው። ፳፫በመኝ
ታዋም ላይ ወይም በምትቀመጥበት ነገር ላይ
ቢሆን ሲነካው እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው።
፳፬ማንም ከእርስዋ ጋር ቢተኛ፥ ግዳጅዋም ቢነ
ካው፥ ሰባት ቀን ርኩስ ነው፤ የሚተኛበትም
መኝታ ሁሉ ርኩስ ነው።

፳፭"ሴትም ከግዳጅዋ ቀን ሌላ ደምዋ ብዙ
ቀን ቢፈስስ፥ ወይም ደምዋ ከግዳጅዋ ወራት
በኋላ ቢፈስስ፥ በግዳጅዋ ወራት እንደ ሆነች
እንዲሁ በፈሳሽዋ ርኩስነት ወራት ትሆናለች፤
ርኵስት ናት። ፳፮ደምዋም በሚፈስስበት ወራት
ሁሉ የምትተኛበት መኝታ ሁሉ በግዳጅዋ ጊዜ
እንደ ነበረው መኝታ ያለ ይሆንባታል፤ የምት
ቀመጥበት ነገር ሁሉ እንደ ግዳጅዋ ርኩስነት
ርኩስ ነው። ፳፯እነዚህንም ነገሮች የሚነካ ሁሉ
ርኩስ ነው፤ ልብሱንም ያጥባል፤ በውኃም ይታ
ጠባል፤ እስከ ማታም ርኩስ ነው። ፳፰ከፈሳሽ
ዋም ብትነጻ ሰባት ቀን ትቈጥራለች፤ ከዚያም
በኋላ ንጽሕት ትሆናለች። ፳፱በስምንተኛውም
ቀን ሁለት ዋኖሶች ወይም ሁለት የርግብ ግልገ
ሎች ይዛ ወደ ካህኑ ወደ ምስክሩ ድንኳን ደጃፍ
ታመጣቸዋለች። ፴ካህኑም አንዲቱን ለኀጢአት
መሥዋዕት፥ አንዲቱንም ለሚቃጠል መሥዋዕት
ያቀርባል፤ ካህኑም ስለ ፈሳሽዋ ርኩስነት በእግ
ዚአብሔር ፊት ያስተሰርይላታል።

---

፩ ግእዙ "እመቦ ብእሲ ዘሰከበ ምስለ ብእሲት" ይላል።

፴፩"እንዲሁም በእነርሱ መካከል ያለችውን
ድንኳኔን ባረከሱ ጊዜ፥ በርኩስነታቸው እን
ዳይሞቱ የእስራኤልን ልጆች ከርኩስነታቸው
አንጹአቸው።
፴፪"ፈሳሽ ነገር ላለበት ሰው፥ ይረክስም
ዘንድ ዘሩ ለሚወጣበት ሰው፥ ፴፫በግዳጅዋም
ደም ለሚፈስሳት፥ ፈሳሽም ነገር ላለባቸው ለወ
ንድም ለሴትም፥ ከረከሰችም ሴት ጋር ለሚተኛ
ሰው ሕጉ ይህ ነው።"

## ምዕራፍ ፲፮

### የስርየት ቀን

፩በእግዚአብሔር ፊት ሌላ እሳትን ስላመጡ
የሞቱ ሁለቱ የአሮን ልጆች ከሞቱ በኋላ እግዚ
አብሔር ሙሴን ተናገረው። ፪እግዚአብሔርም
ሙሴን አለው፥ "እኔ በስርየቱ መክደኛ ላይ
በደመናው ውስጥ እታያለሁና እንዳይሞት በመ
ጋረጃው ውስጥ በምስክሩ ታቦት ላይ ወዳለው
ወደ ስርየቱ መክደኛ ወደ ተቀደሰው ስፍራ
ሁልጊዜ እንዳይገባ ለወንድምህ ለአሮን ንገ
ረው። ፫እንዲሁ አሮን ለኀጢአት መሥዋዕት ከላ
ሞች ወይፈን፥ ለሚቃጠል መሥዋዕትም አውራ
በግ ይዞ ወደ ተቀደሰው ስፍራ ይግባ። ፬የተቀ
ደሰውንም የተልባ እግር ቀሚስ ይልበስ፤ የተ
ልባ እግርም ሱሪ በገላው ላይ ይሁን፤ የተልባ
እግር መታጠቂያ ይታጠቅ፤ የተልባ እግር አክ
ሊልም በራሱ ላይ ያድርግ፤ እነዚህ የተቀደሱ
ልብሶች ናቸው፤ ገላውንም በውኃ ታጥቦ ይል
በሳቸው። ፭ከእስራኤልም ልጆች ማኅበር ለኀጢ
አት መሥዋዕት ሁለት የፍየል ጠቦቶች፥ ለሚቃ
ጠል መሥዋዕት አንድ አውራ በግ ይውሰድ።
፮"አሮንም የኀጢአቱን መሥዋዕት ወይፈን
ያቀርባል፤ ለራሱም፥ ለቤተሰቡም ያስተሰር
ያል። ፯ሁለቱንም የፍየል ጠቦቶች ወስዶ በም
ስክሩ ድንኳን ደጃፍ አጠገብ በእግዚአብሔር
ፊት ያቆማቸዋል። ፰አሮንም በሁለቱ የፍየል
ጠቦቶች ላይ ዕጣ ይጥልባቸዋል፤ አንዱን ዕጣ
ለእግዚአብሔር፥ ሌላውንም ዕጣ ለሚለቀቅ።
፱አሮንም የእግዚአባሔር ዕጣ የሆነበትን ፍየል
ያቀርባል፤ ስለ ኀጢአትም መሥዋዕት ያደርገ
ዋል። ፲የመለቀቅም ዕጣ የሆነበትን ፍየል ያስተ
ስርይበት ዘንድ፥ ለመለቀቅም ወደ ምድረ በዳ
ይሰድደው ዘንድ በሕይወቱ በእግዚአብሔር
ፊት ያቆመዋል።
፲፩"አሮንም ስለ ራሱ ኀጢአት የሚሠዋውን
መሥዋዕት ወይፈኑን ያቀርባል፤ ለራሱም ለቤ
ተሰቡም ያስተሰርያል፤ ስለ ኀጢአቱ የእርሱን
መሥዋዕት ወይፈኑን ያርዳል። ፲፪በእግዚአብሔ
ርም ፊት ከአለው መሠዊያ ላይ የእሳት ፍም
አምጥቶ ጥናውን ይሞላል፤ ከተወቀጠውም
ልቅምና ደቃቅ ዕጣን እጁን ሙሉ ይወስዳል፤
ወደ መጋረጃውም ውስጥ ያመጣዋል። ፲፫እንዳ
ይሞትም የጢሱ ደመና በምስክሩ ታቦት ላይ
ያለውን መክደኛ ይሸፍን ዘንድ በእግዚአብሔር
ፊት ዕጣኑን በእሳቱ ላይ ያደርጋል። ፲፬ከወይፈ
ኑም ደም ወስዶ በስርየቱ መክደኛ ላይ ወደ
ምሥራቅ በጣቱ ይረጨዋል፤ ከደሙም በመክደ
ኛው ፊት በጣቱ ሰባት ጊዜ ይረጫል።
፲፭"ስለ ሕዝቡም ኀጢአት የሚሠዋውን
መሥዋዕት ፍየል ያርዳል፤ ደሙንም ወደ መጋ
ረጃው ውስጥ ያመጣዋል፤ በወይፈኑም ደም
እንዳደረገ በፍየሉ ደም ያደርጋል፤ በመክደኛው
ላይና በመክደኛው ፊት ይረጨዋል። ፲፮ከእስራ
ኤል ልጆች ርኩስነት፥ ከመተላለፋቸውም፥
ከኀጢአታቸውም የተነሣ ለመቅደሱ ያስተሰር
ይለታል፤ እንዲሁም በርኩስነታቸው መካከል
ከእነርሱ ጋር ለኖረች ለምስክሩ ድንኳን ያደር
ጋል። ፲፯እርሱ ለማስተስረይ ወደ መቅደሱ በገባ
ጊዜ ለራሱ፥ ለቤተሰቡም፥ ለእስራኤል ጉባኤ
ሁሉ አስተስርዮ እስኪወጣ ድረስ በምስክሩ
ድንኳን ውስጥ ማንም አይኖርም። ፲፰በእግዚአ
ብሔርም ፊት ወዳለው ወደ መሠዊያው ወጥቶ
ያስተሰርይለታል፤ ከወይፈኑም ደም፥ ከፍየሉም
ደም ወስዶ በመሠዊያው ዙሪያ ያሉትን ቀን
ዶች ያስነካል። ፲፱ከደሙም በእርሱ ላይ ሰባት
ጊዜ በጣቱ ይረጫል፤ ከእስራኤልም ልጆች
ርኩስነት ያነጻዋል፤ ይቀድሰውማል።

### የሕዝቡን ኀጢአት ተሸክሞ ወደ በረሃ ስለሚለቀቀው የፍየል ጠቦት

፳"ስለመቅደሱ፥ስለ ምስክሩም ድንኳን፥ ስለ
መሠዊያውም ማስተስረያና ስለ ካህናትም ማን
ጻት ከፈጸመ በኋላ ደኅነኛውን ፍየል ያቀርባል።
፳፩አሮንም ሁለቱን እጆቹን በደኅነኛው ፍየል
ራስ ላይ ይጭናል፤ በላዩም የእስራኤልን ልጆች
በደል ሁሉ፥ መተላለፋቸውን ሁሉ፥ ኀጢአታ
ቸውንም ሁሉ ያስተሰርያል፤ በፍየሉም ራስ
ላይ ያሸክመዋል፤ በተዘጋጀው ሰውም እጅ ወደ
ምድረ በዳ ይሰድደዋል። ፳፪ፍየሉም ኀጢአታቸ
ውን ሁሉ ወደ በረሃ ይሸከማል፤ ፍየሉንም ዛፍ
በሌለበት በምድረ በዳ ውስጥ ይለቅቀዋል።
፳፫"አሮንም ወደ ምስክሩ ድንኳን ይገባል፤
ወደ መቅደሱም በገባ ጊዜ የለበሰውን የተልባ

እግር ልብስ ያወልቃል፤ በዚያም ይተወዋል።
፳፬በተቀደሰውም ስፍራ ገላውን በውኃ ይታጠ
ባል፤ ሌላውንም ልብስ ለብሶ ይወጣል፤ የእር
ሱንም የሚቃጠል መሥዋዕት ያቀርባል፤ ለካህ
ናቱ እንዳስተሰረየ ለራሱም፥ ለሕዝቡም ያስተ
ሰርያል። ፳፭የኀጢአቱንም መሥዋዕት ስብ በመ
ሠዊያው ላይ ያቃጥለዋል። ፳፮ለመለቀቅ የሚሆ
ነውን ፍየል የወሰደ ሰው ልብሱን ያጥባል፤ ገላ
ውንም በውኃ ይታጠባል፤ ከዚያም በኋላ ወደ
ሰፈሩ ይገባል። ፳፯ለማስተስረያም እንዲሆን ደማ
ቸው ወደ መቅደስ የገባውን የኀጢአቱን መሥ
ዋዕት ወይፈንና የኀጢአቱን መሥዋዕት ፍየል
ከሰፈሩ ወደ ውጭ ያወጡአቸዋል፤ ቍርበታቸ
ውንም፥ ሥጋቸውንም፥ ፈርሳቸውንም በእሳት
ያቃጥላሉ። ፳፰ያቃጠላቸውም ሰው ልብሱን ያጥ
ባል፤ ገላውንም በውኃ ይታጠባል፤ ከዚያም
በኋላ ወደ ሰፈር ይገባል።

፳፱"ይህም የዘለዓለም ሥርዐት ይሁንላችሁ።
፴በዚህ ቀን ትነጹ ዘንድ ማስተስረያ ይሆንላችኋ
ልና በሰባተኛው ወር ከወሩም በዐሥረኛው ቀን
ራሳችሁን አስጨንቋት፤ የሀገር ልጅም፥ በእና
ንተም መካከል የተቀመጠ እንግዳ ሥራን ሁሉ
አትሥሩበት፤ በእግዚአብሔርም ፊት ከኀጢአ
ታችሁ ሁሉ ትነጻላችሁ። ፴፩ታላቅ ሰንበት ይሆ
ንላችኋል፤ ራሳችሁንም ታዋርዳላችሁ፤ የዘለዓ
ለም ሥርዐት ነው። ፴፪የሚቀባውም፥ በአባቱም
ፋንታ ካህን ሊሆን የሚካነው ካህን ያስተስ
ርይ፤ የተቀደሰውንም የተልባ እግር ልብስ ይል
በስ። ፴፫ለቅድስተ ቅዱሳንም ያስተስርይ፤ ለም
ስክሩ ድንኳን፥ ለመሠዊያውም ያስተስርይ፤
ለካህናቱም፥ ለጉባኤውም ሕዝብ ሁሉ ያስተ
ስርይ። ፴፬ይህም አንድ ጊዜ በዓመት ለእስራ
ኤል ልጆች ስለ ኀጢአታቸው ሁሉ ያስተሰርይ
ዘንድ የዘለዓለም ሥርዐት ይሁንላችሁ።" እግ
ዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው እንዲሁ አደ
ረገ።

## ምዕራፍ ፲፯

### ደም መብላት ስለ መከልከሉ

፩እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተና
ገረው- ፪"ለአሮንና ለልጆቹ፥ ለእስራኤልም
ልጆች ሁሉ እንዲህ ብለህ ንገር፡- እግዚአብ
ሔር ያዘዘው ይህ ነው፤ እንዲህም አለ፡- ፫ከእ
ስራኤል ቤት ከመካከላቸውም ከሚኖሩ እን
ግዶች ማናቸውም ሰው በሬ፥ ወይም በግ፥
ወይም ፍየል ቢያርድ፥ በሰፈሩ ውስጥ ወይም
ከሰፈሩ ውጭ ቢያርደው፥ ፬ለእግዚአብሔር በጎ
መዓዛ ያለው የተመረጠ የሚቃጠል መሥዋ
ዕት፥ ወይም የድኅነት መሥዋዕት ያደርገው
ዘንድ ወደ ምስክሩ ድንኳን ደጃፍ ባያመጣው፥
በሌላም ቦታ ቢያርደው፥ በእግዚአብሔር ማደ
ሪያ ፊት ለእግዚአብሔር ቍርባን ያቀርብ ዘንድ
ወደ ምስክሩ ድንኳን ባያመጣው፥ ደሙ በዚያ
ሰው ላይ ይቈጠርበታል፤ ደም አፍስሶአልና፤
ያም ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ። ፭ስለዚህ የእስ
ራኤል ልጆች በሜዳ የሚያርዱትን መሥዋዕ
ታቸውን ወደ እግዚአብሔር ወደ ምስክሩ ድን
ኳን ደጃፍ ያመጡታል፤ ወደ ካህኑም አም
ጥተው ለእግዚአብሔር ለድኅነት መሥዋዕት
ይሠዉታል። ፮ካህኑም በምስክሩ ድንኳን ደጃፍ
ባለው በመሠዊያው ላይ በእግዚአብሔር ፊት
ደሙን ይረጨዋል፤ ስቡንም ለእግዚአብሔር
በጎ መዓዛ እንዲሆን ያቃጥለዋል። ፯መሥዋዕታ
ቸውንም ደግሞ ተከትለው ላመነዘሩባቸው ለሰ
ይጣናት አይሠዉ። ይህ ለእነርሱ ለልጅ ልጃ
ቸው ለዘለዓለም ሥርዐት ይሁን።"

፰ለእነርሱ እንዲህ በላቸው፥ "ከእስራኤል
ቤት ከመካከላቸው ከሚኖሩ እንግዶች ማናቸ
ውም ሰው የሚቃጠል መሥዋዕት ወይም ሌላ
መሥዋዕት ቢያቀርብ፥ ፱ለእግዚአብሔር ይሠዋ
ዘንድ ወደ ምስክሩ ድንኳን ደጃፍ ባያመጣው፥
ያ ሰው ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ።

፲"ከእስራኤልም ልጆች፥ ወይም በመካከላ
ቸው ከሚኖሩ እንግዶች ማናቸውም ሰው ደም
ቢበላ፥ ደም በሚበላው በዚያ ሰው ላይ ፊቴን
አከብድበታለሁ፤ ያንም ሰው ከሕዝቡ ለይቼ
አጠፋዋለሁ። ፲፩የሥጋ ሁሉ ሕይወት ደሙ
ነው፤ ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያ
ልና በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተስረያ
ይሆን ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት። ፲፪ስለዚህ
የእስራኤልን ልጆች፡- 'ከእናንተ ማንም ደምን
አይበላም፤ በመካከላችሁም ከሚኖሩ እንግዶች
ማንም ደምን አይበላም' አልሁ።

፲፫"ከእስራኤልም ልጆች፥ ወይም በመካከላ
ቸው ከሚኖሩ እንግዶች ማናቸውም ሰው የሚ
በላ እንስሳ ወይም ወፍ እያደነ ቢይዝ፥ ደሙን
ያፈስሳል፤ በአፈርም ይከድነዋል። ፲፬የሥጋ ሁሉ
ሕይወት ደሙ ነውና፤ ስለዚህ ለእስራኤል
ልጆች፡- የሥጋ ሁሉ ሕይወት ደሙ ነውና
የሥጋውን ሁሉ ደም አትብሉ፤ የሚበላውም
ሁሉ ተለይቶ ይጥፋ አልኋቸው። ፲፭የሞተውን
ወይም አውሬ የሰበረውን የሚበላ ሰው ሁሉ፥
የሀገር ልጅ ወይም እንግዳ ቢሆን፥ ልብሱን

ያጥባል፤ በውኃም ይታጠባል፤ እስከ ማታም
ርኩስ ይሆናል፤ ከዚያም በኋላ ንጹሕ ይሆ
ናል። ፲፮ልብሱንና ገላውን ባያጥብ ግን ኃጢአ
ቱን ይሸከማል።”

## ምዕራፍ ፲፰

### የተከለከለ ሩካቤ

፩እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገ
ረው:- ፪“ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገ
ራቸው:- እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ።
፫እንደ ተቀመጣችሁባት እንደ ግብፅ ምድር
ሥራ አትሥሩ፤ እኔም ወደ እርስዋ እንደማገባ
ችሁ እንደ ከነዓን ምድር ሥራ አትሥሩ፤ በሥ
ርዐታቸውም አትሂዱ። ፬ፍርዴን አድርጉ፤ በእ
ርስዋም ትሄዱ ዘንድ ሥርዐቴን ጠብቁ፤ እኔ
እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ። ፭የሚሠራቸው
ሰው በእነርሱ በሕይወት ይኖራልና ሥርዐቴ
ንና ፍርዴን ጠብቁ፤ እኔ እግዚአብሔር አም
ላካችሁ ነኝ።
፮“ከእናንተም ማንም ሰው ኀፍረተ ሥጋውን
ይገልጥ ዘንድ ወደ ሥጋ ዘመዱ ሁሉ አይቅ
ረብ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ። ፯የአ
ባትህን ኀፍረተ ሥጋና የእናትህን ኀፍረተ ሥጋ
አትግለጥ፤ እናትህ ናትና ኀፍረተ ሥጋዋን አት
ግለጥ። ፰የአባትህን ሚስት ኀፍረተ ሥጋ አትግ
ለጥ፤ የአባትህ ኀፍረተ ሥጋ ነው። ፱የእኅትህን
ኀፍረተ ሥጋ አትግለጥ፤ የአባትህ ልጅ ወይም
የእናትህ ልጅ በቤት ወይም በውጭ የተወለደች
ብትሆን፥ ኀፍረተ ሥጋዋን አትግለጥ። ፲የወ
ንድ ልጅህን ሴት ልጅ ኀፍረተ ሥጋ ወይም
የሴት ልጅህን ሴት ልጅ ኀፍረተ ሥጋ አትግ
ለጥ፤ የአንተ ኀፍረተ ሥጋ ነውና። ፲፩ከአባትህ
የተወለደችውን የአባትህን ሚስት ልጅ ኀፍረተ
ሥጋ አትግለጥ፤ ከአባትህ የተወለደች እኅትህ
ናት፤ ኀፍረተ ሥጋዋን አትግለጥ። ፲፪የአባትህን
እኅት ኀፍረተ ሥጋ አትግለጥ፤ የአባትህ ዘመድ
ናትና። ፲፫የእናትህን እኅት ኀፍረተ ሥጋ አትግ
ለጥ፤ የእናትህ ዘመድ ናትና። ፲፬የአባትህን ወን
ድም ሚስት ኀፍረተ ሥጋ አትግለጥ፤ ዘመድህ
ናትና። ፲፭የምራትህን ኀፍረተ ሥጋ አትግለጥ፤
የልጅህ ሚስት ናት፤ ኀፍረተ ሥጋዋን አትግ
ለጥ። ፲፮የወንድምህን ሚስት ኀፍረተ ሥጋ አት
ግለጥ፤ የወንድምህ ኀፍረተ ሥጋ ነውና። ፲፯የሴ
ትንና የሴት ልጅዋን ኀፍረተ ሥጋ አትግለጥ፤
የወንድ ልጅዋን ሴት ልጅ ወይም የሴት ልጅ
ዋን ሴት ልጅ ኀፍረተ ሥጋዋን ትገልጥ ዘንድ
አታግባ፤ ዘመዶች ናቸው፤ ኀጢአት ነውና።
፲፰በእኅቷ ላይ እንዳትቀና ሚስትህ በሕይወት
ሳለች የእኅቷን ኀፍረተ ሥጋ አትግለጥ።
፲፱“እርስዋም በግዳጅዋ ርኵሰት ሳለች ኀፍ
ረተ ሥጋዋን ትገልጥ ዘንድ ሳትነጻ በግዳ
ጅዋ ወደ አለች ሴት አትቅረብ። ፳ከባልንጀ
ራህ ሚስት ጋር አትተኛ፤ ዘርህንም አትዝራ
ባት። ፳፩ከዘርህም ለሞሎክ አትስጥ[፩] የአምላክህ
ንም ስም አታርክስ፤ እኔ አምላክህ እግዚአብ
ሔር ነኝ። ፳፪ከሴትም ጋር እንደምትተኛ ከወ
ንድ ጋር አትተኛ፤ ጸያፍ ነገር ነውና። ፳፫ዘር
ህን በእርስዋ ላይ እንዳትዘራና እንዳትረክስባት
ወደ እንስሳ አትሂድ፤ ሴት ከእርሱ ጋር ትተኛ
ዘንድ በእንስሳ ፊት አትቁም፤ የተጠላ ነገር
ነውና።
፳፬“ከፊታችሁ የማሳድዳቸው አሕዛብ በእነ
ዚህ ሁሉ ረክሰዋልና በእነዚህ ነገሮች ሁሉ አት
ርከሱ። ፳፭ምድሪቱም ረከሰች፤ ስለዚህ ኀጢአ
ቷን በእርስዋ ላይ እመልሳለሁ፤ ምድሪቱም
የሚኖሩባትን ሰዎች ትተፋለች። ፳፮ሥርዐቴንና
ፍርዴን ጠብቁ፤ እናንተም የሀገሩ ልጆች፥ በእ
ናንተም መካከል የሚኖሩት እንግዶች ከዚህ
ርኵሰት ምንም አትሥሩ፤ ፳፯ከእናንተ በፊት
የነበሩት የሀገሩ ልጆች ይህን ርኵሰት ሁሉ ሠር
ተዋልና፥ ምድሪቱንም አርክሰዋታልና፤ ፳፰ምድ
ሪቱም ከእናንተ በፊት የነበረውን ሕዝብ እንደ
ተፋች ባረከሳችኋት ጊዜ እናንተንም እንዳት
ተፋችሁ ተጠንቀቁ። ፳፱ከዚህ ርኵሰት ሁሉ
ማናቸውን የሚያደርግ ያ ሰው ከሕዝቡ መካ
ከል ተለይቶ ይጠፋልና። ፴ስለዚህ ከእናንተ
በፊት የነበሩ ሰዎች የሠሩትን ጸያፍ የሆነውን
ወግ ሁሉ እንዳትሠሩ፥ በእርሱም እንዳትረክሱ
ሥርዐቴን ጠብቁ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካ
ችሁ ነኝና።”

## ምዕራፍ ፲፱

### የቅድስናና የፍትሕ ሕግ

፩እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገ
ረው:- ፪“ለእስራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ እን
ዲህ በላቸው:- እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ
ቅዱስ ነኝና እናንተ ቅዱሳን ሁኑ። ፫ከእናንተ
እያንዳንዱ አባቱንና እናቱን ይፍራ፤ ሰንበታ

---

[፩] ግእዙ እና ግሪክ ሰባ. ሊ. “ኢታስተፃምድ ወልደከ ለመልአክ” ይላል።

ቴንም ጠብቁ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ
ነኝ። ፬ጣዖታትንም አትከተሉ፤ ቀልጠው የተሠ
ሩትንም የአማልክት ምስሎች ለእናንተ አታድ
ርጉ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ።
፭"የድኅነትን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ስት
ሠዉ ንጹሕ አድርጋችሁ ሠዉት። ፮በምትሠዉ
በት ቀንና በነጋው ይበላል፤ እስከ ሦስተኛውም
ቀን ድረስ ቢተርፍ በእሳት ይቃጠላል። ፯በሦ
ስተኛውም ቀን ቢበላ ጸያፍ ነው፤ ተቀባይነት
የለውም፤ ፰የበላውም ለእግዚአብሔር የተቀደሰ
ውን ነገር አርክሶአልና ኀጢአቱን ይሸከማል፤
ያም ሰው ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ።
፱"የምድራችሁንም መከር በሰበሰባችሁ ጊዜ
የእርሻችሁን አጨዳ አታጥሩ፤ ስታጭዱም የወ
ደቀውን ቃርሚያ አትልቀሙ። ፲የወይንህን ቃር
ሚያ አጥርተህ አትቃርም፤ የወደቀውንም የወ
ይንህን ፍሬ አትሰብስብ፤ ለድሆችና ለእንግ
ዶች ተወው፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ
ነኝና።
፲፩"አትስረቁ፤ አትዋሹም፤ ባልንጀራውንም
የሚቀማ አይኑር።[፩] ፲፪በስሜም በሐሰት አት
ማሉ፤ የአምላካችሁን ቅዱስ ስም አታርክሱ፤
እኔ አምላካችሁ እግዚአብሔር ነኝና።
፲፫"በባልንጀራህ ግፍ አታድርግ፤ አትቀማ
ውም። የሞያተኛው ዋጋ እስከ ነገ ድረስ በአ
ንተ ዘንድ አይደርብህ። ፲፬ደንቆሮውን አትስ
ደብ፤ በዕውርም ፊት ዕንቅፋት አታድርግ፤
ነገር ግን አምላክህን እግዚአብሔርን ፍራ፤ እኔ
አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።
፲፭"በፍርድ ዐመፃ አታድርጉ፤ ለድሃ አታ
ድላ፤ ባለጠጋውንም አታክብር፤ ነገር ግን ለባ
ልንጀራህ በእውነት ፍረድ። ፲፮በሕዝብህ መካ
ከል በሸንጋይነት አትዙር፤ በባልንጀራህም ደም
ላይ[፪] አትቁም፤ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ
ነኝ።
፲፯"ወንድምህን አትበድለው፤ በልብህም አት
ጥላው፤ በእርሱ ምክንያት ኀጢአት እንዳይሆ
ንብህ ባልንጀራህን የምትነቅፍበትን ንገረው፤
ገሥጸውም። ፲፰አትበቀል፤ በሕዝብህም ልጆች
ቂም አትያዝ፤ ነገር ግን ባልንጀራህን እንደ
ራስህ ውደድ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ
ነኝና።

፲፱"ሥርዐቴን ጠብቁ፤ በበሬህ በባዕድ ቀን
በር አትረስ፤ በወይን ቦታህ የተለያየ ዘር አት
ዝራ፤ ከሁለት ዐይነት ነገር የተሠራ ልብስ ኀፍ
ረት ነውና አትልበስ።
፳"ማናቸውም ሰው ከሴት ባሪያ ጋር ቢተኛ፥
እርስዋም ለባል የተሰጠች፥ ዋጋዋም ያልተከ
ፈለ፥ አርነት ያልወጣች ብትሆን፥ ቅጣት አለ
ባቸው፤ አርነት አልወጣችምና አይገደሉም።
፳፩እርሱም የበደሉን መሥዋዕት አውራ በግ ወደ
እግዚአብሔር ወደ ምስክሩ ድንኳን ደጃፍ ያመ
ጣል። ፳፪ካህኑም ስለ ሠራው ኀጢአት በእግዚአ
ብሔር ፊት በበደል መሥዋዕት በግ ያስተሰርይ
ለታል፤ የሠራውም ኀጢአት ይቀርለታል።
፳፫"አምላካችሁ እግዚአብሔር ወደሚሰጣችሁ
ምድር በገባችሁ ጊዜ፥ የሚበላ የፍሬ ዛፍ ሁሉ
በተከላችሁም ጊዜ ከርኵሰቱ ሁሉ ታጠሩታላ
ችሁ፤ የሦስቱ ዓመት ፍሬም ርኩስ ነው፤ አይ
በላም። ፳፬በአራተኛውም ዓመት ፍሬ ሁሉ ለእ
ግዚአብሔር ምስጋና ቅዱስ ይሁን። ፳፭በአም
ስተኛውም ዓመት ፍሬውን ብሉ፤ ፍሬውም
ይበዛላችኋል፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ
ነኝ።
፳፮"በተራራ ላይ አትብሉ፤ አትርከሱ፥[፫] በወ
ፍም አታሟርቱ። ፳፯የራስ ጠጕራችሁንም ዙሪያ
ውን አትከርክሙት፤ ጢማችሁንም አትላጩ።
፳፰ሰው ቢሞት ምላጭ ወደ ሥጋችሁ አታቅ
ርቡ፤ ገላችሁንም አትንቀሱት፤ እኔ እግዚአብ
ሔር አምላካችሁ ነኝ።
፳፱"ምድሪቱ ከግልሙትና፥ ከርኵሰትም እን
ዳትሞላ ሴት ልጅህን ታመነዝር ዘንድ አታር
ክሳት። ፴ሰንበታቴን ጠብቁ፤ መቅደሴንም አክ
ብሩ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና።
፴፩"ወደ መናፍስት ጠሪዎችና ወደ ጠንቋዮች
አትሂዱ፤ እንዳትረክሱባቸውም አትፈልጉአ
ቸው፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና።
፴፪"በሽበታሙ ፊት ተነሣ፤ ሽማግሌውንም
አክብር፤ አምላክህን እግዚአብሔርንም ፍራ፤
እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና።
፴፫"በሀገራችሁ ውስጥ እንግዳ ከእናንተ ጋር
ቢቀመጥ ግፍ አታድርጉበት። ፴፬እናንተ በግ
ብፅ ምድር እንግዶች ነበራችሁና፤ ወደ እናንተ
የመጣ እንግዳ እንደ ሀገር ልጅ ይሁንላችሁ፤

---

፩ ዕብ. "ከእናንተም እርስ በእርሳችሁ አትነቃቀፉ" ሲል ግሪክ ሰባ. ሊ. "ባልንጀራውን በመቃወም የሐሰት ምስክር
አይሁን" ይላል።

፪ ግእዙ "በባልንጀራህ ነፍስ ላይ" ይላል።

፫ ዕብ. "ከደሙ ጋር ምንም አትብሉ፤ አስማትም አታድርጉ" ይላል።

እርሱን እንደ ራሳችሁ ውደዱት፤ እኔ እግዚአ
ብሔር አምላካችሁ ነኝና።
፴፭"በፍርድ፥ በመለካትም፥ በመመዘንም፥
በመስፈርም ዐመፃ አታድርጉ። ፴፮የእውነትም
ሚዛን፥ የእውነትም መመዘኛ፥[፬] የእውነትም
የፈሳሽ መስፈሪያ ይሁንላችሁ፤ ከግብፅ ምድር
ያወጣኋችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ እኔ
ነኝ። ፴፯ሕጌን ሁሉ፥ ትእዛዜንም ሁሉ ጠብቁ፤
አድርጉትም፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ
ነኝና።"

## ምዕራፍ ፳

### የሕግ መተላለፍ ቅጣት

፩እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተና
ገረው፦ ፪"ደግሞ የእስራኤልን ልጆች እንዲህ
በላቸው፦ ከእስራኤል ልጆች ወይም በእስራ
ኤል ዘንድ ከሚቀመጡ እንግዶች ማናቸውም
ሰው ዘሩን ለሞሎክ[፭] አገልግሎት ቢሰጥ ፈጽሞ
ይገደል፤ የሀገሩ ሕዝብ በድንጋይ ይውገሩት።
፫መቅደሴን ያረክስ ዘንድ፥ የቅዱሳኔንም ስም[፮]
ያጐስቍል ዘንድ ዘሩን ለሞሎክ አገልግሎት
ሰጥቶአልና እኔ በዚያ ሰው ላይ ፊቴን አከብዳ
ለሁ፤ ከሕዝቡም መካከል ለይች አጠፋዋለሁ።
፬ዘሩንም ለሞሎክ ሲሰጥ፥ የሀገሩ ሕዝብ ያን
ሰው ቸል ቢሉት፥ አይተው እንዳላዩ ቢሆኑ፥
ባይገድሉትም፥ እኔ በዚያ ሰውና በቤተ ሰቡ
ላይ ፊቴን አከብዳለሁ። ፭እርሱንና ከሞሎክ[፯]
ጋር ያመነዘሩ ዘንድ የሚከተሉትን ሁሉ ከሕዝ
ባቸው መካከል ለይች አጠፋለሁ።
፮"እነርሱን ተከትሎ ያመነዝር ዘንድ መና
ፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን የሚከተል
ሰው ቢኖር፥ በዚያ ሰው ላይ ፊቴን አከብ
ዳለሁ፤ ከሕዝቡም መካከል ለይች አጠፋዋ
ለሁ። ፯እንግዲህ እኔ እግዚአብሔር አምላካ
ችሁ ቅዱስ ነኝና[፰] ቅዱሳን ሁኑ። ፰ሕጌንና ትእ
ዛዜን ጠብቁ፤ አድርጉትም፤ እኔ የምቀድሳ
ችሁ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና። ፱ማና
ቸውም ሰው አባቱን ወይም እናቱን ቢሰድብ
ፈጽሞ ይገደል፤ አባቱንና እናቱን ሰድቦአልና
በደለኛ ነው።[፱]
፲"ማናቸውም ሰው ከሌላ ሰው ሚስት ወይም
ከባልንጀራው ሚስት ጋር ቢያመነዝር አመንዝራ
ውና አመንዝራዪቱ ፈጽመው ይገደሉ። ፲፩ማና
ቸውም ሰው ከአባቱ ሚስት ጋር ቢተኛ የአባ
ቱን ኀፍረት ሥጋ ገልጦአል፤ ሁለቱም ፈጽ
መው ይገደሉ፤ በደለኞች ናቸው።[፲] ፲፪ማናቸ
ውም ሰው ከምራቱ ጋር ቢተኛ ሁለቱ ፈጽ
መው ይገደሉ፤ ጸያፍ ነገር አድርገዋል፤ በደ
ለኞች ናቸው። ፲፫ማናቸውም ሰው ከሴት ጋር
እንደሚተኛ ከወንድ ጋር ቢተኛ ሁለቱ ጸያፍ
ነገር አድርገዋል፤ ፈጽመው ይገደሉ፤ በደለኞች
ናቸው። ፲፬ማናቸውም ሰው እናቲቱንና ልጂቱን
ቢያገባ ኀጢአት ነው፤ በመካከላቸው ኀጢአት
እንዳይሆን እርሱንና እነርሱን[፲፩] በእሳት ያቃጥሉ
አቸው። ፲፭ማናቸውም ሰው ከእንስሳ ጋር ቢገ
ናኝ ፈጽሞ ይገደል፤ እንስሳዪቱንም ግደሉአት።
፲፮ማንኛዪቱም ሴት ወደ እንስሳ ብትቀርብ፥ ከእ
ርሱም ጋር ብትገናኝ፥ ሴቲቱንና እንስሳውን
ግደሉ፤ ፈጽመው ይገደሉ፤ በደለኞች ናቸው።
፲፯"ማናቸውም ሰው የአባቱን ልጅ ወይም
የእናቱን ልጅ እኅቱን ቢያገባ፥ ኀፍረተ ሥጋ
ዋንም ቢያይ፥ እርስዋም ኀፍረተ ሥጋውን
ብታይ፥ ይህ ጸያፍ ነገር ነው፤ በሕዝባቸውም
ልጆች ፊት ይገደሉ፤ የእኅቱን ኀፍረተ ሥጋ
ገልጦአልና ኀጢአቱን ይሸከማል። ፲፰ማናቸ
ውም ሰው ከባለ ግዳጅ ሴት ጋር ቢተኛ ኀፍ
ረተ ሥጋዋንም ቢገልጥ፥ ፈሳሽዋን ገልጦአልና፥
እርስዋም የደምዋን ፈሳሽ ገልጣለችና ሁለቱ
ከሕዝባቸው መካከል ተለይተው ይጥፉ። ፲፱የአ
ባትህን ወይም የእናትህን እኅት ኀፍረተ ሥጋ
አትግለጥ፤ ይህን የሚያደርግ የዘመድን ኀፍረተ
ሥጋ ገልጦአል፤ ኀጢአታቸውን ይሸከማሉ።
፳ሰውም ከቅርብ ዘመዱ[፲፪] ሚስት ጋር ቢተኛ

---

[፬] ዕብ. "የኢፍ መስፈሪያ" የሚል ይጨምራል።
[፭] ግዕዝ እና ግሪክ ሰባ. ሊ. "ለመልአክ" ይላል።
[፮] ዕብ. "የተቀደሰውን ስሜን" ሲል ግሪክ ሰባ. ሊ. "ለእኔ የተቀደሱትን ስም" ይላል።
[፯] ግዕዙ "ከመላእክት ጋር" ይላል።
[፰] ዕብ. "ሰውነታችሁን ቀድሱ" የሚል ይጨምራል።
[፱] ዕብ. "ደሙ በራሱ ላይ ነው" ይላል።
[፲] ዕብ. "ደማቸው በላያቸው ነው" ይላል።
[፲፩] ግእዙ "እርሱንና እርስዋን" ይላል።
[፲፪] ዕብ. "ከአጎቱ" ይላል።

የቅርብ ዘመዱን ኀፍረተ ሥጋ ገልጦአል፤ ያለ
ልጅ ይሞታሉ። ፳፩ሰውም የወንድሙን ሚስት
ቢያገባ ርኵሰት ነው፤ የወንድሙን ኀፍረተ
ሥጋ ገልጦአል፤ ያለ ልጅም ይሙቱ።
፳፪"እንግዲህ ትቀመጡባት ዘንድ የማገባችሁ
ምድር እንዳትተፋችሁ ትእዛዜን ሁሉ፥ ፍር
ዴንም ሁሉ ጠብቁ፤ አድርጉትም። ፳፫ከፊታ
ችሁ በማወጣቸው ሕዝብ ሕግ አትሂዱ፤ ይህን
ሁሉ አድርገዋልና ተጸየፍኋቸው ፳፬ነገር ግን
እናንተ፡- ምድራቸውን ትወርሳላችሁ፤ ትወር
ሱአትም ዘንድ ወተትና ማር የምታፈስሰውን
ምድር እሰጣችኋለሁ አልኋችሁ፤ እኔ ከአሕ
ዛብ የለየኋችሁ አምላካችሁ እግዚአብሔር ነኝ።
፳፭እንግዲህ በንጹሕና በርኩስ እንስሳ መካ
ከል፥ በንጹሕና በርኩስም ወፍ መካከል ለየሁ
ላችሁ፤ ርኩሳን ናቸው ብዬ በለየኋቸው በእን
ስሳና በወፍ፥ በምድርም ተንቀሳቃሽ ሁሉ ነፍ
ሳችሁን አታርክሱ። ፳፮እኔ እግዚአብሔር ቅዱስ
ነኝና፥ ለእኔም ትሆኑ ዘንድ ከአሕዛብ ለይቻች
ኋለሁና ቅዱሳን ትሆኑልኛላችሁ።
፳፯"ወንድ ወይም ሴት መናፍስትን ቢጠሩ፥
ወይም ጠንቋዮች ቢሆኑ ፈጽመው ይገደሉ፤
በድንጋይም ይውገሩአቸው፤ ፱ በደለኞች ናቸ
ውና።"

## ምዕራፍ ፳፩

### ስለ ካህናት ቅድስና

፩እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገ
ረው፥ "ከወገናቸው በሞተ ሰው ራሳቸውን እን
ዳያረክሱ ለካህናቱ ለአሮን ልጆች ንገራቸው።
፪ከቅርብ ዘመዶቻቸው፥ ከአባቶቻቸው፥ ወይም
ከእናቶቻቸው፥ ወይም ከወንዶች ልጆቻቸው፥
ወይም ከሴቶች ልጆቻቸው፥ ወይም ከወንድ
ሞቻቸው፥ ፫ወይም ከቀረበች ያላገባች ድን
ግል እኅት በቀር ራሳቸውን አያርክሱ። ፬ራሱን
ያጕሰቍል ዘንድ ከሕዝቡ በማንም አይርከስ።፲
፭ስለ ሞተው ሰው ራሳቸውን አይላጩ፤ ጢማ
ቸውንም አይላጩ፤ ሥጋቸውንም አይንጩ።
፮ለአምላካቸው ቅዱሳን ይሁኑ፤ የአምላካቸው
ንም ስም አያርክሱ፤ የእግዚአብሔርን፲፩ መሥ
ዋዕትና የአምላካቸውን መባ ያቀርባሉና ቅዱ
ሳን ይሁኑ። ፯ለአምላኩ ለእግዚአብሔር የተ
ቀደሰ ነውና ጋለሞታን ሴት ወይም የረከሰች
ውን አያግባ፤ ወይም ከባልዋ የተፋታችውን
አያግባ። ፰የአምላክህን መባ ያቀርባልና ስለዚህ
ትቀድሰዋለህ፤ እኔም የምቀድሳችሁ እግዚአብ
ሔር ቅዱስ ነኝና እርሱ ቅዱስ ይሁንልህ። ፱የካ
ህንም ሰው ልጅ በግልሙትና ራስዋን ብታረ
ክስ በግልሙትና አባቷን ታረክሰዋለች፤ በእ
ሳት ትቃጠል።
፲"በራሱም ላይ የቅባት ዘይት የፈሰሰበት፥
የክህነትም ልብስ ይለብስ ዘንድ የተቀደሰ፥ ከወ
ንድሞቹ የተለየው ካህን ራሱን አይላጭ፤ ልብ
ሱንም አይቀደድ። ፲፩ወደ ሞተ ሰው ሁሉ አይ
ግባ፤ በአባቱም ወይም በእናቱ አይርከስ። ፲፪የአ
ምላኩም ቅባት ዘይት ቅዱስነት በላዩ ነውና
ከመቅደስ አይውጣ፤ የአምላኩንም ቅዱስ ስም
አያርክስ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ። ፲፫እርሱም
ከወገኑ ድንግል ሴትን ያግባ። ፲፬ባልዋ የሞተ
ባትን፥ ወይም የተፋታችውን፥ የተጠላችውን
ወይም ጋለሞታዪቱን አያግባ፤ ነገር ግን ከወ
ገኑ ድንግሊቱን ያግባ፤ ፲፭እኔም የምቀድሰው
እግዚአብሔር ነኝና በሕዝቡ መካከል ዘሩን አያ
ጕስቍል።"
፲፮እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተና
ገረው፡- ፲፯"ለአሮን እንዲህ ብለህ ንገረው፡-
ከወገንህ በትውልዳቸው ነውር ያለበት ሰው
ሁሉ የአምላኩን መባ ያቀርብ ዘንድ አይቅረብ።
፲፰ንጹሕ ያልሆነ ሰው ሁሉ አይቅረብ፤ ዕውር፥
ወይም አንካሳ፥ ወይም አፍንጫ ደፍጣጣ፥
ወይም ጆሮ ቈራጣ፥ ፲፱ወይም እጅ ሰባራ፥
ወይም እግረ ሰባራ፥ ፳ወይም ጎባጣ፥ ወይም
ድንክ፥ ወይም ዐይነ መጭማጫ፥ ወይም ቅን
ድብ መላጣ፥ ወይም እከካም፥ ወይም ቋቍ
ቻም፥ ወይም የአባለዘሩ ፍሬ አንድ የሆነ ነው
ረኛ ሁሉ አይቅረብ። ፳፩ከካህኑ ከአሮን ዘር
ነውር ያለበት ሰው የእግዚአብሔርን መሥዋዕት
ያቀርብ ዘንድ አይቅረብ፤ ነውረኛ ነው፤ የአምላ
ኩን መባ ያቀርብ ዘንድ አይቅረብ። ፳፪የቅዱሱ
ንና የቅዱስ ቅዱሳኑን የአምላኩን መባ ይብላ፤
፳፫ነገር ግን ነውረኛ ነውና መቅደሶችን እንዳያ
ረክስ ወደ መጋረጃው አይግባ፤ ወደ መሠዊያ
ውም አይቅረብ፤ የምቀድሳቸው እኔ እግዚአብ
ሔር ነኝና።" ፳፬ሙሴም ይህን ለአሮን፥ ለልጆ
ቹም፥ ለእስራኤልም ልጆች ሁሉ ነገራቸው።

---

፱ ዕብ. "ደማቸው በላያቸው ነው" ይላል።

፲ ዕብ. "የሕዝቡ አለቃ ራሱን ያጕሰቍል ዘንድ አይርከስ" ይላል።

፲፩ ዕብ. "የእሳት ቍርባን" ይላል።

## ምዕራፍ ፳፪

### የመሥዋዕት ቅድስና

፩እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገ
ረው:- ፪"የእስራኤል ልጆች ለእኔ ከሚቀድሱ
አቸው ከቅዱሳን ነገሮች ራሳቸውን እንዲለዩ፥
የተቀደሰውንም ስሜን እንዳያረክሱ ለአሮንና
ለልጆቹ ንገራቸው፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።
፫እንዲህ በላቸው:- ማናቸውም ሰው ከዘራችሁ
በትውልዳችሁ ርኵሰት እያለበት የእስራኤል
ልጆች ለእግዚአብሔር ወደሚቀድሱት ወደ
ቅዱስ ነገር ቢቀርብ፥ ያ ሰው ከፊቴ ተለይቶ
ይጥፋ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ። ፬ከአሮን ዘር
ለምጽ ወይም ፈሳሽ ነገር ያለበት ሁሉ ንጹሕ
እስኪሆን ድረስ ከተቀደሰው አይብላ። ከበድ
ንም የተነሣ ርኩስ የሆነውን፥ ወይም ዘሩ ከእ
ርሱ የሚፈስስበትን የሚነካ፥ ፭ወይም የሚያረ
ክሰውን ተንቀሳቃሽ፥ ወይም በሁሉ ዐይነት የረ
ከሰውን ሰው የሚነካ፥ ፮እነዚህን ሁሉ የሚነካ
ሰው እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ይሆናል፤ ገላውን
በውኃ ካልታጠበ ከተቀደሰው አይብላ። ፯ፀሐ
ይም በገባች ጊዜ ንጹሕ ይሆናል፤ ከዚያም
በኋላ ምግቡ ነውና ከተቀደሰው ይብላ። ፰በእር
ሱም እንዳይረክስ፥ የሞተውን፥ አውሬም የሰበ
ረውን አይብላ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝና። ፱ቢያ
ረክሱአት እንዳይሞቱ፥ ስለ እርስዋም ኀጢአ
ትን እንዳይሸከሙ፥ ሕግን ይጠብቁ፤ የምቀድ
ሳቸው እኔ እግዚአብሔር ነኝና።

፲"ከባዕድ ወገን የሆነ ሰው ከተቀደሰው አይ
ብላ፤ የካህኑም እንግዳ፥ ደመወዘኛውም ከተ
ቀደሰው አይብላ። ፲፩ካህኑ ግን በገንዘቡ አገል
ጋይ ቢገዛ እርሱ ከምግቡ ይብላ፤ በቤቱም የተ
ወለዱት ከእንጀራው ይብሉ። ፲፪የካህንም ልጅ
ከሌላ ወገን ጋር ብትጋባ፥ እርስዋ ከተቀደሰው
ዐሥራት አትብላ። ፲፫የካህን ልጅ ግን ባልዋ
ቢሞት፥ ወይም ብትፋታ፥ ልጅም ባይኖራት፥
በብላቴንነቷ እንደ ነበረች ወደ አባቷ ቤት ብት
መለስ፥ ከአባቷ እንጀራ ትብላ፤ ከሌላ ወገን
የሆነ ባዕድ ሰው ግን ከእርሱ አይብላ። ፲፬ማና
ቸውም ሰው ሳያውቅ ከተቀደሰው ቢበላ አምስ
ተኛ እጅ ጨምሮ የተቀደሰውን ለካህኑ ይስጥ።
፲፭ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡትን፥ በእስራ
ኤል ልጆች ዘንድ የተቀደሰውን ነገር አያር
ክሱ። ፲፮በኀጢአት ሳሉ ከተቀደሰው መሥዋዕት
ከበሉ ግን ኀጢአትና በደል ይሆንባቸዋል፤
የማነጻቸው እኔ እግዚአብሔር ነኝና።"

፲፯እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተና
ገረው:- ፲፰"ለአሮንና ለልጆቹ፥ ለእስራኤልም
ልጆች ሁሉ እንዲህ ብለህ ንገራቸው:- ከእስ
ራኤል ቤት ወይም ከእናንተ መካከል ከሚቀ
መጡት እንግዶች ማናቸውም ሰው ስእለቱን
ሁሉ፥ በፈቃዱም የሚያቀርበውን ሁሉ፥ ለእ
ግዚአብሔር ለሚቃጠል መሥዋዕት የሚያቀ
ርበውን ቍርባን ቢያቀርብ፥ ፲፱ይሠምርላችሁ
ዘንድ ከበሬ፥ ወይም ከበግ፥ ወይም ከፍየል
ነውር የሌለበትን ተባቱን አቅርቡ። ፳ነገር ግን
አይሠምርላችሁምና ነውር ያለበትን ለእግዚአ
ብሔር አታቅርቡ። ፳፩ማናቸውም ሰው ስእለ
ቱን ለመፈጸም ወይም በፈቃዱ ለማቅረብ[፩] የደ
ኅንነትን መሥዋዕት፥ ወይም በሬን፥ ወይም
በግን፥ ለእግዚአብሔር ቢያቀርብ፥ ይሰምርለት
ዘንድ ፍጹም ይሁን፤ ነውርም አይሁንበት።
፳፪ዕውር፥ ወይም ሰባራ፥ ወይም ምላሱ የተ
ቈረጠ፥ ወይም የሚመግል ቍስል ያለበት፥
ወይም እከካም፥ ወይም ቋቍቻም ቢሆን፥ እነ
ዚህን ሁሉ ለእግዚአብሔር አታቅርቡ፤ እነዚ
ህንም ለእሳት ቍርባን በመሠዊያው ላይ ለእ
ግዚአሔር አታሳርጉ። ፳፫በሬው፥ ወይም በጉ
ጆሮው፥ ወይም ጅራቱ የተቈረጠ ቢሆን፥ ቈጥ
ረህ የራስህ ገንዘብ አድርገው እንጂ ለስእለት
አይቀበልህም። ፳፬የተቀጠቀጠውን፥ ወይም የተ
ሰበረውን፥ ወይም የተቈረጠውን ወይም የተሰነ
ጋውን ለእግዚአብሔር አታቅርቡ፤ በምድራች
ሁም እነዚህን አትሠዉ። ፳፭ከእነዚህም ከባዕድ
ወገን ከሆነ ሰው እጅ ለአምላካችሁ መባ አታ
ቅርቡ፤ ርኵሰትም፥ ነውርም አለባቸውና አይ
ቀበላችሁም።"

፳፮እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተና
ገረው:- ፳፯"ላም፥ ወይም በግ፥ ወይም ፍየል
ሲወለድ ሰባት ቀን ከእናቱ ጋር ይቀመጥ፤
በስምንተኛውም ቀን፥ ከዚያም በላይ ለእግ
ዚአብሔር የእሳት ቍርባን የሠመረ ይሆናል።
፳፰ላም፥ ወይም በግ፥ ወይም ፍየል ብትሆን
እርስዋንና ልጅዋን በአንድ ቀን አትረዱ።
፳፱የምስጋናንም መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ስት
ሠዉ እንዲቀበላችሁ ሠዉለት። ፴በዚያው ቀን
ይብሉት፤ ከእርሱ እስከ ነገ ምንም አትተዉ፤
እኔ እግዚአብሔር ነኝና። ፴፩ትእዛዛቴን ጠብቁ፤
አድርጉትም፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝና። ፴፪የተ

፩ ግሪክ ሰባ. ሊ. "በበዓላት ቀን" ይላል።

ቀደሰውንም ስሜን አታርክሱ፤ እኔ ግን በእስ
ራኤል ልጆች መካከል እቀደሳለሁ፤ ፴፫የምቀድ
ሳችሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝና። አምላካችሁም
እሆን ዘንድ ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ እኔ
እግዚአብሔር ነኝና።”

## ምዕራፍ ፳፫

### የሃይማኖት በዓላት

፩እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተና
ገረው፡- ፪“ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ
ንገራቸው፡- ቅዱሳት ጉባኤያት ብላችሁ የም
ትጠሩአቸው በዓላቴ፥ የእግዚአብሔር በዓላት
እነዚህ ናቸው። ፫ስድስት ቀን ሥራህን ትሠ
ራለህ፤ በሰባተኛው ቀን ግን የዕረፍት ሰንበት
ነው፤ ለእግዚአብሔር ቅዱስ ጉባኤ ይሆንበ
ታል፤ ምንም ሥራ አትሠሩም፤ በምትኖሩበት
ሁሉ ለእግዚአብሔር ሰንበት ነው። ፬እነዚህ የእ
ግዚአብሔር በዓላት፥ በየዘመናቸው የምታውጁ
አቸው፥ የተቀደሱ ጉባኤያት ናቸው።

### በዓለ ፋሲካና በዓለ ናዕት
(ዘኍ. ፳፰፥ ፲፮-፳፭)

፭“በመጀመሪያው ወር በዐሥራ አራተኛው
ቀን ሲመሽ የእግዚአብሔር ፋሲካ ነው። ፮በዚ
ህም ወር በዐሥራ አምስተኛው ቀን ለእግዚ
አብሔር የቂጣ በዓል ነው፤ ሰባት ቀን ቂጣ
ብሉ። ፯መጀመሪያይቱ ቀን ቅድስት ጉባኤ
ትሁንላችሁ፤ የተግባር ሥራ ሁሉ አትሥሩ
ባት። ፰ሰባት ቀንም ለእግዚአብሔር የሚቃ
ጠል መሥዋዕት አቅርቡ፤ ሰባተኛዋ ቀን ቅድ
ስት ጉባኤ ትሁንላችሁ፤ የተግባር ሥራ ሁሉ
አትሥሩባት።”
፱እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተና
ገረው፡- ፲“ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ
ንገራቸው፡- ወደምሰጣችሁ ምድር በገባችሁ
ጊዜ፥ መከሩንም ባጨዳችሁ ጊዜ፥ የእናንተን
መከር በኵራት ነዶ ወደ ካህኑ አምጡ፤ ፲፩እር
ሱም ነዶውን በእግዚአብሔር ፊት እንዲሠም
ርላችሁ ያቀርበዋል፤ በማግስቱ ከሰንበት በኋላ
ካህኑ ያቅርበው፤ ፲፪ነዶውንም ባቀረባችሁበት
ቀን ነውር የሌለበትን የአንድ ዓመት ተባት
ጠቦት ለሚቃጠል መሥዋዕት ለእግዚአብሔር
አቅርቡ። ፲፫የስንዴም ቍርባን ከመስፈሪያው
ከዐሥር እጅ ሁለት እጅ የሆነ በዘይት የተለ
ወሰ መልካም የስንዴ ዱቄት ለእግዚአብሔር
በጎ መዓዛ ያለው ቍርባን ይሁን፤ የመጠጡም
ቍርባን የወይን ጠጅ የኢን መስፈሪያ አራ
ተኛ እጅ ይሁን። ፲፬እንጀራውንም፥ የተጠበ
ሰውንም እሸት፥ ለምለሙንም እሸት የአምላ
ካችሁን ቍርባን እስከምታቀርቡበት እስከዚህ
ቀን ድረስ አትብሉ። ይህ በምትቀመጡበት
ሀገር ሁሉ ለልጅ ልጃችሁ የዘለዓለም ሥር
ዐት ነው።

### በዓለ ሠዊት
(ዘኍ. ፳፰፥ ፳፮-፴፩)

፲፭“ያቀረባችሁትን ነዶ ከምታመጡበት ቀን
በኋላ ከሰንበት ማግስት ፍጹም ሰባት ሱባዔ
ቍጠሩ፤ ፲፮እስከ መጨረሻዋ ሰባተኛ ሰንበት
ማግስት ድረስ አምሳ ቀን ቍጠሩ፤ አዲሱንም
መሥዋዕት ለእግዚአብሔር አቅርቡ። ፲፯ከየማ
ደሪያችሁ ከመስፈሪያው ከዐሥር እጅ ሁለት
እጅ ከሆነ መልካም የስንዴ ዱቄት የተሠራ
ሁለት የቍርባን እንጀራ ታመጣላችሁ፤ ከእህ
ላችሁ ቀዳምያት ለእግዚአብሔር በእርሾ ይጋ
ገራል። ፲፰ከኅብስቱም ጋር ነውር የሌለባቸውን
የአንድ ዓመት ሰባት ጠቦቶች፥ ከመንጋውም
አንድ ወይፈን፥ ሁለትም ነውር የሌለባቸው
አውራ በጎች ታቀርባላችሁ፤ ለእግዚአብሔር
በጎ መዓዛ ያለው መሥዋዕት እንዲሆን መሥዋ
ዕታቸውና ቍርባናቸው፥ ወይናቸውም ለእግዚ
አብሔር ይሁን። ፲፱አንድም አውራ ፍየል ለኀ
ጢአት መሥዋዕት፥ ሁለትም የአንድ ዓመት
ተባት ጠቦቶች ከመጀመሪያው የእህል ቍርባን
ጋር ለደኅንነት መሥዋዕት አቅርቡ። ፳ካህኑም
ከበኵራቱ ኅብስት፥ ከሁለቱም ጠቦቶች ጋር
በእግዚአብሔር ፊት ለቍርባን ያቅርበው፤ ለእ
ግዚአብሔር የተቀደሰ ፈንታ ነው፤ ላቀረበው
ለካህኑ ይሁን። ፳፩ያችንም ቀን ቅድስት ጉባኤ
ብላችሁ ታውጃላችሁ፤ የተግባር ሥራ ሁሉ
አታድርጉባት፤ በምትቀመጡበት ሀገር ሁሉ
ለልጅ ልጃችሁ የዘለዓለም ሥርዐት ነው።
፳፪“የምድራችሁን መከር በሰበሰባችሁ ጊዜ
በእርሻችሁ የቀረውን አጥርታችሁ አትጨዱ፤
የመከሩንም ቃርሚያ አትልቀሙ፤ ለድሆችና
ለእንግዶች ተዉት፤ እኔ እግዚአብሔር አምላ
ካችሁ ነኝና።”

### በዓለ መጥቅዕ
(ዘኍ. ፳፱፥ ፩-፮)

፳፫እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተና
ገረው፡- ፳፬“ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ
ንገራቸው፡- በሰባተኛው ወር ከወሩም በመጀመ

በት ቀን ሁሉ ያድርጉት፤ በእስራኤል ልጆች
ዘንድ የዘለዓለም ቃል ኪዳን ነው። ፱ለአሮንና
ለልጆቹም ይሁን፤ በእሳት ከተደረገው ከእግ
ዚአብሔር ቍርባን ለዘለዓለም ሥርዐት ለእ
ርሱ ቅዱስ ቅዱሳን ነውና በተቀደሰ ስፍራ
ይብሉት።”

### በእግዚአብሔር ላይ ስለሚደረግ ዕርፈት ቅጣት

፲አባቱ ግብፃዊ የነበረ የእስራኤላዊት ሴት ልጅ
በእስራኤል ልጆች መካከል ወጣ፤ የእስራኤላዊቱ
ሴት ልጅና አንድ እስራኤላዊ ሰው በሰፈር ውስጥ
ተጣሉ፤ ፲፩የእስራኤላዊቱም ሴት ልጅ የእግዚአ
ብሔርን ስም ጠርቶ ሰደበ፤ ወደ ሙሴም አመ
ጡት። እናቱም ከዳን ነገድ የዳቤር ልጅ ነበረች፤
ስምዋም ሰሎሚት ነበረ። ፲፪በእግዚአብሔርም ትእ
ዛዝ እስኪፈርዱበት ድረስ በግዞት አኖሩት።
፲፫እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገ
ረው፦ ፲፬“ተሳዳቢውን ከሰፈር ወደ ውጭ አው
ጣው፤ የሰሙትም ሁሉ እጃቸውን በራሱ ላይ
ይጫኑበት፤ ማኅበሩም ሁሉ በድንጋይ ይው
ገሩት።” ፲፭ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ
ትነግራለህ፥ “ማናቸውም ሰው አምላኩን ቢሰ
ድብ ኀጢአቱን ይሸከማል። ፲፮የእግዚአብሔር
ንም ስም ጠርቶ የሚሰድብ ሁሉ ፈጽሞ ይገ
ደል፤ ማኅበሩም ሁሉ በድንጋይ ይውገሩት፤
መጻተኛ ወይም የሀገር ልጅ ቢሆን፥ የእግዚአ
ብሔርን ስም ጠርቶ ቢሳደብ ይገደል። ፲፯ሰውን
የገደለ ሰው ሁሉ ፈጽሞ ይገደል። ፲፰እንስሳንም
ቢገድል በነፍስ ፋንታ ነፍስ ይክፈል። ፲፱ሰውም
ባልንጀራውን ቢጎዳ፥ እርሱ እንዳደረገ እንዲሁ
ይደረግበት። ፳ስብራት በስብራት ፋንታ፥ ዐይን
በዐይን ፋንታ፥ ጥርስ በጥርስ ፋንታ፥ ሰውን
እንደ ጎዳ እንዲሁ ይደረግበት። ፳፩ሰውንም የመ
ታና የገደለ ፈጽሞ ይገደል። ፳፪እኔ እግዚአብ
ሔር አምላካችሁ ነኝና ለመጻተኛና ለሀገር ልጅ
አንድ ዐይነት ሕግ ይሁንላችሁ።” ፳፫ሙሴም
ለእስራኤል ልጆች ተናገራቸው፤ ተሳዳቢው
ንም ከሰፈር ወደ ውጭ አወጡት፤ በድንጋይም
ወገሩት። የእስራኤልም ልጆች እግዚአብሔር
ሙሴን እንዳዘዘው አደረጉ።

## ምዕራፍ ፳፭

### ስለ ሰባተኛ ዓመት ዕረፍት

(ዘዳ. ፲፭፥ ፩-፲፩)

፩እግዚአብሔርም ሙሴን በሲና ተራራ ላይ
እንዲህ ብሎ ተናገረው፦ ፪“ለእስራኤል ልጆች
እንዲህ ብለህ ንገራቸው፦ እኔ ወደምሰጣችሁ
ምድር በገባችሁ ጊዜ እኔ የምሰጣችሁ ምድር
ታርፋለች፤ ለእግዚአብሔርም ሰንበት ታደር
ጋለች። ፫ስድስት ዓመት እርሻህን ትዘራለህ፤
ስድስት ዓመትም ወይንህን ትቈርጣለህ፤ ፍሬ
ዋንም ትሰበስባለህ። ፬በሰባተኛው ዓመት ግን
ሰንበት ነው፤ የምድር ዕረፍት ነው፤ ለእግዚአ
ብሔር ሰንበት ነው፤ እርሻህን አትዝራ፤ ወይ
ንህንም አትቍረጥ። ፭የምድራችሁን ገቦ አት
ጨደው፤ የተቀደሰውንም የወይንህን ፍሬ አታ
ከማች፤ ለምድሪቱ የዕረፍት ዓመት ይሆናል።
፮የምድርም ሰንበት ለአንተ፥ ለወንድ ባሪያ
ህም፥ ለሴት ባሪያህም፥ ለምንደኛም፥ ከአንተ
ጋር ለሚኖር ለመጻተኛም ምግብ ይሁን። ፯ለእ
ንስሶችህም፥ በምድርህም ላሉት አራዊት ፍሬዋ
ሁሉ ምግብ ይሁን።

### ዐመተ ኢዮቤልዩ

፰“የዓመታትን ሰባት ሰንበቶች ሰባት ጊዜ
ሰባት ለራስህ ትቈጥራለህ፤ እነዚህም ሰባት የዓ
መታት ሱባዔያት አርባ ዘጠኝ ዓመታት ይሆ
ናሉ። ፱ከዚያም በኋላ በሰባተኛው ወር ከወሩ
በዐሥረኛው ቀን በምድራችሁ ሁሉ በቀንደ መለ
ከት ታውጃለህ፤ በማስተስረያ ቀን በምድራችሁ
ሁሉ በቀንደ መለከት ታውጃላችሁ። ፲አምሳኛው
ንም ዓመት ትቀድሳላችሁ፤ በምድሪቱም ለሚ
ኖሩት ሁሉ ነጻነትን ታውጃላችሁ፤ እርሱ ለእ
ናንተ ኢዮቤልዩ ነው፤ ሰው ሁሉ ወደ ርስቱና
ወደ ወገኑ ይመለስ። ፲፩ያ አምሳኛው ዓመት ለእ
ናንተ ኢዮቤልዩ ይሆናል፤ በእርሱም አትዝሩ፤
የገቦውንም አትጨዱ፤ የተቀደሰውንም በእርሱ
አትልቀሙ። ፲፪ኢዮቤልዩ ነውና የተቀደሰ ይሁ
ንላችሁ፤ በሜዳ ላይ የበቀለውን ብሉ።
፲፫“በዚች ኢዮቤልዩ ዓመት ሰው ሁሉ ወደ
ርስቱ ይመለሳል። ፲፬ለባልንጀራህም አንዳች
ብትሸጥለት፥ ወይም ከባልንጀራህ እጅ ብት
ገዛ፥ ሰው ባልንጀራውን አያስጨንቀው። ፲፭ከኢ
ዮቤልዩ ዓመት በኋላ እንደ ዓመታቱ ቍጥር
ከባልንጀራህ ትገዛለህ፤ እርሱም እንደ መከሩ
ዓመታት ቍጥር ይከፍልሃል። ፲፮እንደ ዓመታቱ
ብዛት ዋጋውን ያበዛል፤ እንደ ዓመታቱም ማነስ
ዋጋውን ያሳንሳል፤ እንደ መከሩ ቍጥር ይሸ
ጥልሃል። ፲፯እኔም እግዚአብሔር አምላካችሁ
ነኝና ሰው ባልንጀራውን አያስጨንቅ፤ ነገር ግን
አምላክህን እግዚአብሔርን ፍራ።
፲፰“ሥርዐቴንም አድርጉ፤ ፍርዴንም ጠብቁ፤
አድርጉትም፤ በምድሪቱም ውስጥ ተዘልላችሁ

በት ቀን ሁሉ ያድርጉት፤ በእስራኤል ልጆች
ዘንድ የዘለዓለም ቃል ኪዳን ነው። ፱ለአሮንና
ለልጆቹም ይሁን፤ በእሳት ከተደረገው ከእግ
ዚአብሔር ቍርባን ለዘለዓለም ሥርዐት ለእ
ርሱ ቅዱስ ቅዱሳን ነውና በተቀደሰ ስፍራ
ይብሉት።”

### በእግዚአብሔር ላይ ስለሚደረግ ዕርፈት ቅጣት

፲አባቱ ግብፃዊ የነበረ የእስራኤላዊት ሴት ልጅ
በእስራኤል ልጆች መካከል ወጣ፤ የእስራኤላዊቱ
ሴት ልጅና አንድ እስራኤላዊ ሰው በሰፈር ውስጥ
ተጣሉ፤ ፲፩የእስራኤላዊቱም ሴት ልጅ የእግዚአ
ብሔርን ስም ጠርቶ ሰደበ፤ ወደ ሙሴም አመ
ጡት። እናቱም ከዳን ነገድ የዳቤር ልጅ ነበረች፤
ስምዋም ሰሎሚት ነበረ። ፲፪በእግዚአብሔርም ትእ
ዛዝ እስኪፈርዱበት ድረስ በግዞት አኖሩት።
፲፫እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገ
ረው፦ ፲፬“ተሳዳቢውን ከሰፈር ወደ ውጭ አው
ጣው፤ የሰሙትም ሁሉ እጃቸውን በራሱ ላይ
ይጫኑበት፤ ማኅበሩም ሁሉ በድንጋይ ይው
ገሩት።” ፲፭ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ
ትነግራለህ፥ “ማናቸውም ሰው አምላኩን ቢሰ
ድብ ኀጢአቱን ይሸከማል። ፲፮የእግዚአብሔር
ንም ስም ጠርቶ የሚሰድብ ሁሉ ፈጽሞ ይገ
ደል፤ ማኅበሩም ሁሉ በድንጋይ ይውገሩት፤
መጻተኛ ወይም የሀገር ልጅ ቢሆን፥ የእግዚአ
ብሔርን ስም ጠርቶ ቢሳደብ ይገደል። ፲፯ሰውን
የገደለ ሰው ሁሉ ፈጽሞ ይገደል። ፲፰እንስሳንም
ቢገድል በነፍስ ፋንታ ነፍስ ይክፈል። ፲፱ሰውም
ባልንጀራውን ቢጎዳ፥ እርሱ እንዳደረገ እንዲሁ
ይደረግበት። ፳ስብራት በስብራት ፋንታ፥ ዐይን
በዐይን ፋንታ፥ ጥርስ በጥርስ ፋንታ፥ ሰውን
እንደ ጎዳ እንዲሁ ይደረግበት። ፳፩ሰውንም የመ
ታና የገደለ ፈጽሞ ይገደል። ፳፪እኔ እግዚአብ
ሔር አምላካችሁ ነኝና ለመጻተኛና ለሀገር ልጅ
አንድ ዐይነት ሕግ ይሁንላችሁ።” ፳፫ሙሴም
ለእስራኤል ልጆች ተናገራቸው፤ ተሳዳቢው
ንም ከሰፈር ወደ ውጭ አወጡት፤ በድንጋይም
ወገሩት። የእስራኤልም ልጆች እግዚአብሔር
ሙሴን እንዳዘዘው አደረጉ።

## ምዕራፍ ፳፭

### ስለ ሰባተኛ ዓመት ዕረፍት

(ዘዳ. ፲፭፥ ፩-፲፩)

፩እግዚአብሔርም ሙሴን በሲና ተራራ ላይ
እንዲህ ብሎ ተናገረው፦ ፪“ለእስራኤል ልጆች
እንዲህ ብለህ ንገራቸው፦ እኔ ወደምሰጣችሁ
ምድር በገባችሁ ጊዜ እኔ የምሰጣችሁ ምድር
ታርፋለች፤ ለእግዚአብሔርም ሰንበት ታደር
ጋለች። ፫ስድስት ዓመት እርሻህን ትዘራለህ፤
ስድስት ዓመትም ወይንህን ትቈርጣለህ፤ ፍሬ
ዋንም ትሰበስባለህ። ፬በሰባተኛው ዓመት ግን
ሰንበት ነው፤ የምድር ዕረፍት ነው፤ ለእግዚአ
ብሔር ሰንበት ነው፤ እርሻህን አትዝራ፤ ወይ
ንህንም አትቍረጥ። ፭የምድራችሁን ገቦ አት
ጨደው፤ የተቀደሰውንም የወይንህን ፍሬ አታ
ከማች፤ ለምድሪቱ የዕረፍት ዓመት ይሆናል።
፮የምድርም ሰንበት ለአንተ፥ ለወንድ ባሪያ
ህም፥ ለሴት ባሪያህም፥ ለምንደኛም፥ ከአንተ
ጋር ለሚኖር ለመጻተኛም ምግብ ይሁን። ፯ለእ
ንስሶችህም፥ በምድርህም ላሉት አራዊት ፍሬዋ
ሁሉ ምግብ ይሁን።

### ዐመተ ኢዮቤልዩ

፰“የዓመታትን ሰባት ሰንበቶች ሰባት ጊዜ
ሰባት ለራስህ ትቈጥራለህ፤ እነዚህም ሰባት የዓ
መታት ሱባዔያት አርባ ዘጠኝ ዓመታት ይሆ
ናሉ። ፱ከዚያም በኋላ በሰባተኛው ወር ከወሩ
በዐሥረኛው ቀን በምድራችሁ ሁሉ በቀንደ መለ
ከት ታውጃለህ፤ በማስተስረያ ቀን በምድራችሁ
ሁሉ በቀንደ መለከት ታውጃላችሁ። ፲አምሳኛው
ንም ዓመት ትቀድሳላችሁ፤ በምድሪቱም ለሚ
ኖሩት ሁሉ ነጻነትን ታውጃላችሁ፤ እርሱ ለእ
ናንተ ኢዮቤልዩ ነው፤ ሰው ሁሉ ወደ ርስቱና
ወደ ወገኑ ይመለስ። ፲፩ያ አምሳኛው ዓመት ለእ
ናንተ ኢዮቤልዩ ይሆናል፤ በእርሱም አትዝሩ፤
የገቦውንም አትጨዱ፤ የተቀደሰውንም በእርሱ
አትልቀሙ። ፲፪ኢዮቤልዩ ነውና የተቀደሰ ይሁ
ንላችሁ፤ በሜዳ ላይ የበቀለውን ብሉ።
፲፫“በዚች ኢዮቤልዩ ዓመት ሰው ሁሉ ወደ
ርስቱ ይመለሳል። ፲፬ለባልንጀራህም አንዳች
ብትሸጥለት፥ ወይም ከባልንጀራህ እጅ ብት
ገዛ፥ ሰው ባልንጀራውን አያስጨንቀው። ፲፭ከኢ
ዮቤልዩ ዓመት በኋላ እንደ ዓመታቱ ቍጥር
ከባልንጀራህ ትገዛለህ፤ እርሱም እንደ መከሩ
ዓመታት ቍጥር ይከፍልሃል። ፲፮እንደ ዓመታቱ
ብዛት ዋጋውን ያበዛል፤ እንደ ዓመታቱም ማነስ
ዋጋውን ያሳንሳል፤ እንደ መከሩ ቍጥር ይሸ
ጥልሃል። ፲፯እኔም እግዚአብሔር አምላካችሁ
ነኝና ሰው ባልንጀራውን አያስጨንቅ፤ ነገር ግን
አምላክህን እግዚአብሔርን ፍራ።
፲፰“ሥርዐቴንም አድርጉ፤ ፍርዴንም ጠብቁ፤
አድርጉትም፤ በምድሪቱም ውስጥ ተዘልላችሁ

ትኖራላችሁ። ፲፱ምድሪቱም ፍሬዋን ትሰጣለች፤
እስክትጠግቡም ድረስ ትበላላችሁ፤ በእርስዋም
ውስጥ ተዘልላችሁ ትኖራላችሁ። ፳እናንተም፦
‹ካልዘራን፥ እህላችንንም ካላከማቸን በሰባተ
ኛው ዓመት ምን እንበላለን?› ብትሉ፥ ፳፩እኔ
በስድስተኛው ዓመት በረከቴን በላያችሁ እሰ
ጣለሁ፤ ምድሪቱም የሦስት ዓመት ፍሬ ታፈራ
ለች። ፳፪በስምንተኛውም ዓመት ትዘራላችሁ፤
ከከረመውም እህል ትበላላችሁ፤ ፍሬዋ እስኪ
ገባ፥ እስከ ዘጠነኛው ዓመት ድረስ፥ ከከረመው
እህል ትበላላችሁ።

### የዕዳ ምሕረት ዐመት

፳፫“ምድርም ለእኔ ናትና፥ እናንተም በእኔ
ፊት እንግዶችና መጻተኞች ናችሁና ምድርን
ለዘለዓለም አትሽጡ። ፳፬በርስታችሁም ምድር
ሁሉ መቤዠትን ለምድሪቱ አድርጉ። ፳፭ወንድ
ምህም ቢደኸይ፥ ከርስቱም ቢሸጥ፥ ለእርሱ
የቀረበ ዘመዱ መጥቶ ወንድሙ የሸጠውን ይቤ
ዠዋል። ፳፮የሚቤዠውም ሰው ቢያጣ፥ እርሱም
እጁ ቢረጥብ፥ ለመቤዠትም የሚበቃ ቢያገኝ፥
፳፯የሸያጩን ዘመን ቈጥሮ የቀረውን ወደ ገዛው
ሰው ይመልስ፤ እርሱም ወደ ርስቱ ይመለስ።
፳፰ለራሱም ዕዳውን መክፈል ባይችል፥ ሽያጩ
በገዛው ሰው እጅ እስከ ኢዮቤልዩ ዓመት ድረስ
ይቀመጥ፤ በኢዮቤልዩም ዓመት ይውጣ፤ እር
ሱም ወደ ርስቱ ይመለስ።
፳፱“ሰውም ቅጥር ባለበት ከተማ መኖርያ
ቤትን ቢሸጥ፥ ከተሸጠ በኋላ አንድ ዓመት
እስኪፈጸም ድረስ ለመቤዠት ይችላል፤ ለአ
ንድ ሙሉ ዓመት መቤዠት ይችላል። ፴አንድ
ዓመት እስኪጨረስ ባይቤዠው ቤቱ ለገዡ
ይሆናል፤ ቅጥር ባለበት ከተማ ያለውን ያን
ቤት ይመረምሩለታል፤ ለገዛው ሰው ለልጅ
ልጁ ለዘለዓለም ይጸናለታል፤ በኢዮቤልዩ ዓመ
ትም አይወስዱበትም። ፴፩ቅጥር በሌለበት መን
ደር ያሉ ቤቶች ግን እንደ እርሻ ይቈጠራሉ፤
ይቤዣሉ፤ በኢዮቤልዩ ዓመትም ይመለሳሉ።
፴፪የሌዋውያንን ከተሞች፥ በከተሞቻቸውም
ያሉ ቤቶቻቸውን ሌዋውያን ለዘለዓለም መቤ
ዠት ይችላሉ። ፴፫ማናቸውም ሰው ከሌዋውያን
ቢገዛ፥ በእስራኤል ልጆች መካከል የሌዋውያን
ከተሞች ቤቶች ርስቶቻቸው ናቸውና በርስቱ
ከተማ ያለ የተሸጠው ቤት በኢዮቤልዩ ዓመት
ይመለሳል። ፴፬በከተማዎቻቸው ዙሪያ ያሉ እር
ሻዎቻቸውም የዘለዓለም ርስቶቻቸው ናቸውና
አይሸጡም።

### ለድኃ በወለድ አለማበደር

፴፭“ከአንተ ጋር ያለው ወንድምህ ቢደኸይ፥
እጁም በአንተ ዘንድ ቢደክም እንደ እንግዳና
እንደ መጻተኛ ትረዳዋለህ፤ ከአንተም ጋር
ይኑር። ፴፮ወንድምህ ከአንተ ጋር ይኖር ዘንድ
ከእርሱ ምንም ወለድ ወይም ትርፍ አትው
ሰድ፤ ነገር ግን አምላክህን ፍራ፤ እኔ እግዚ
አብሔር ነኝና። ፴፯ብርህን በወለድ አታበድ
ረው፤ እህልህንም በትርፍ አትስጠው። ፴፰የከነ
ዓንን ምድር እሰጥህ ዘንድ፥ አምላክም እሆንህ
ዘንድ ከግብፅ ምድር ያወጣሁህ እኔ እግዚአብ
ሔር አምላክህ ነኝና።

### ስለ ባሪያ ነጻነት

፴፱“ወንድምህ ቢቸገር፥ ራሱንም ለአንተ
ቢሸጥ፥ እንደ ባሪያ አድርገህ አትግዛው።
፵እንደ ምንደኛና እንደ ስደተኛ ከአንተ ጋር
ይሁን፤ እስከ ኢዮቤልዩ ዓመትም ያገልግልህ።
፵፩በኢዮቤልዩ ዓመትም እርሱ ከልጆቹ ጋር
ከአንተ ይወጣል፤ ወደ ወገኖቹም፥ ወደ አባ
ቱም ርስት ይመለሳል። ፵፪ከግብፅ ምድር ያወ
ጣኋቸው ባሪያዎች ናቸውና ባሪያ እንደሚሸጥ
አይሸጡ። ፵፫በሥራ አታስጨንቀው፤ ነገር ግን
አምላክህን እግዚአብሔርን ፍራ። ፵፬ምን ያህል
ወንድ ባሪያና ሴት ባሪያ እንዲኖሩህ ብትፈ
ልግ ግን በዙሪያችሁ ካሉት ከእነርሱ ከአሕ
ዛብ ወንድና ሴት ባያሪያዎችን ግዙ። ፵፭በእና
ንተ መካከል ከሚቀመጡት ስደተኞች ልጆች
ለራሳችሁ ትገዛላችሁ፤ ከዘመዶቻቸውም በም
ድራችሁ የሚኖሩት ሁሉ ለርስታችሁ ይሁኑአ
ችሁ። ፵፮ከእናንተም በኋላ ለልጆቻችሁ ታወር
ሱአቸዋላችሁ፤ እነርሱም ለእናንተ ለዘለዓለም
ውርስ ይሆናሉ፤ ነገር ግን ከወንድሞቻችሁ ከእ
ስራኤል ልጆች ማናቸውም ሰው ወንድሙን
በሥራ አያስጨንቀው።
፵፯“በአንተም ዘንድ የሚኖር መጻተኛ ወይም
እንግዳ ሀብታም ቢሆን፥ ወንድምህም በእ
ርሱ አጠገብ ቢደኸይ፥ ራሱንም ለመጻተ
ኛው፥ ወይም ለእንግዳው ወይም ለወገኖቹ ዘር
ቢሸጥ፥ ፵፰ከተሸጠ በኋላ መቤዠት ይችላል፤
ከወንድሞቹ አንዱ ይቤዠው፤ ፵፱ወይም አጎቱ
ወይም የአጎቱ ልጅ ይቤዠው፤ ወይም ከወ
ገኑ ለእርሱ የቀረበ ዘመድ ይቤዠው፤ ወይም
እርሱ እጁ ቢረጥብ ራሱን ይቤዠው። ፶ከገዛ
ውም ሰው ጋር ከገዛበት ዓመት ጀምሮ እስከ
ኢዮቤልዩ ዓመት ድረስ ይቍጠር፤ የሽያጩም

ብር እንደ ዓመታቱ ቍጥር ይሁን፤ እንደ ምን
ደኛውም ዘመን ከእርሱ ጋር ይሁን። ፶፩ብዙ
ዓመታትም[፩] ቢቀሩ እንደ እነርሱ ቍጥር ከሸ
ያጩ ብር የመቤዠቱን ዋጋ ይመልስ። ፶፪እስከ
ኢዮቤልዩ ዓመት ድረስ ጥቂት ዓመታት ቢቀሩ
እንደ ዓመቱ ይቍጠሩለት፤ እንደ አመታቱም
መጠን የመቤዠቱን ዋጋ ይመልስ። ፶፫በየዓመቱ
እንደ ምንደኛ ከእርሱ ጋር ይኑር፤ በፊትህ
እንደ ቀደመው አያስጨንቀው። ፶፬በዚህ ዘመን
ሁሉ ግን ባይቤዥ በኢዮቤልዩ ዓመት እርሱ
ከልጆቹ ጋር ይውጣ። ፶፭የእስራኤል ልጆች
ለእኔ ባሪያዎች ናቸውና፤ ከግብፅ ምድር ያወ
ጣኋቸው ባሪያዎች ናቸው፤ እኔ እግዚአብሔር
አምላካችሁ ነኝ።[፪]

## ምዕራፍ ፳፮

### በመታዘዝ የሚገኝ በረከት

(ዘዳ. ፯፥ ፲፪-፳፬፤ ፳፰፥ ፩-፲፬)

፩"ለእናንተ በእጅ የተሠራ ጣዖት አታድርጉ፤
የተቀረጸም ምስል ወይም ሐውልት አታቁሙ፤
ትሰግዱለትም ዘንድ በምድራችሁ ላይ የተቀረጸ
ድንጋይ አታኑሩ፤ እኔ እግዚአብሔር አምላካ
ችሁ ነኝና። ፪ሰንበታቴንም ጠብቁ፤ የቀደስኋቸ
ውንም ፍሩ፤[፫] እኔ እግዚአብሔር ነኝና።
፫"በሥርዐቴ ብትሄዱ፥ ትእዛዛቴንም ብትጠ
ብቁ፥ ብታደርጉትም፥ ፬ዝናሙን በወቅቱ አዘ
ንማለሁ፤ ምድሪቱም እህልዋን ትሰጣለች፤ የሜ
ዳው ዛፎችም ፍሬያቸውን ይሰጣሉ። ፭የእህ
ሉም ማበራየት በእናንተ ዘንድ እስከ ወይኑ
መቈረጥ ይደርሳል፤ የወይኑም መቈረጥ እስከ
እህሉ መዝራት ይደርሳል፤ እስክትጠግቡም
ድረስ እንጀራችሁን ትበላላችሁ፤ በምድራች
ሁም ላይ ተዘልላችሁ ትኖራላችሁ። ፮በምድራ
ችሁም ላይ ሰላምን እሰጣለሁ፤ ትተኛላችሁ፤
የሚያስፈራችሁም የለም፤ ክፉዎችንም አራ
ዊት ከምድራችሁ አጠፋለሁ።[፬] ፯ጠላቶቻችሁ
ንም ታሳድዳላችሁ፤ በፊታችሁም በሰይፍ ይወ
ድቃሉ። ፰ከእናንተም አምስቱ መቶውን ያሳ
ድዳሉ፤ መቶውም ዐሥሩን ሺህ ያሳድዳሉ፤
ጠላቶቻችሁም በፊታችሁ በሰይፍ ይወድቃሉ።
፱ወደ እናንተም እመለከታለሁ፤ አባዛችኋለሁ፤
ከፍ ከፍም አደርጋችኋለሁ፤ ቃል ኪዳኔንም
ከእናንተ ጋር አጸናለሁ። ፲ብዙ ጊዜ የተቀመጠ
ውን፥ የከረመውንም እህል ትበላላችሁ፤ አዲሱ
ንም ታስገቡ ዘንድ የከረመውን ታወጣላችሁ።
፲፩ማደሪያዬንም በእናንተ መካከል አደርጋለሁ፤
ነፍሴም አትጸየፋችሁም። ፲፪በመካከላችሁም
እመላለሳለሁ፤ እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ፤
እናንተም ሕዝብ ትሆኑልኛላችሁ። ፲፫ባሪያዎች
ከነበራችሁበት ከግብፅ ምድር ያወጣኋችሁ እኔ
እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ፤ የባርነታችሁን
ቀንበር ሰብሬአለሁ፤ በግልጽም አወጣኋችሁ።

### ባለመታዘዝ የሚመጣ ቅጣት

(ዘዳ. ፳፰፥ ፲፭-፷፰)

፲፬"ነገር ግን ባትሰሙኝ፥ እነዚህንም ትእዛ
ዛት ሁሉ ባታደርጉ፥ ፲፭ሥርዐቴንም ብትንቁ፥
ትእዛዛቴንም ሁሉ እንዳታደርጉ፥ ቃል ኪዳኔ
ንም እንድታፈርሱ ሰውነታችሁ ፍርዴን ብትሰ
ለች፥ ፲፮እኔም እንዲህ አደርግባችኋለሁ፤ ፍርሀ
ትን፥ ክሳትንም፥ ዐይናችሁንም የሚያፈዝዝ፥
ሰውነታችሁንም የሚያጠፋ ትኩሳት አወርድባች
ኋለሁ፤ ዘራችሁንም በከንቱ ትዘራላችሁ፤ ጠላ
ቶቻችሁ ይበሉታልና። ፲፯ፊቴንም አከብድባች
ኋለሁ፤ በጠላቶቻችሁም ፊት ትወድቃላችሁ፤
የሚጠሏችሁም ያሸንፉአችኋል። ማንም ሳያሳ
ድዳችሁ ትሸሻላችሁ። ፲፰እስከዚህም ድረስ ባት
ሰሙኝ፥ ስለ ኀጢአታችሁ በቅጣታችሁ ላይ
ሰባት እጥፍ መቅሠፍትን እጨምራለሁ። ፲፱የት
ዕቢታችሁን ስድብ አጠፋለሁ፤[፭] ሰማያችሁንም
እንደ ብረት፥ ምድራችሁንም እንደ ናስ አደርጋ
ለሁ። ፳ጕልበታችሁም በከንቱ ያልቃል፤ ምድ
ራችሁም እህልዋን አትሰጥም፤ የዱር ዛፎችም
ፍሬያቸውን አይሰጡም።
፳፩"ከዚያም በኋላ በእንቢተኝነት ብትሄዱ
ብኝ፥ ልትሰሙኝም ባትፈቅዱ እንደ ኀጢአ
ታችሁ መጠን በመቅሠፍት ላይ ሰባት እጥፍ
እጨምራለሁ። ፳፪በእናንተ ላይ ክፉዎች የምድ
ርን አራዊት እሰድዳለሁ፤ ይበሉአችኋል፤[፮] እን

---

፩ ግእዙ "ስምንት ዓመት" ይላል።
፪ "እኔ እግዚአብሔር አምላክ ነኝ" የሚለው በግሪክ ሰባ. ሊ. የምዕ. ፳፮ መጀመሪያ ነው።
፫ ዕብ. "መቅደሴንም" ይላል።
፬ ዕብ. "ሰይፍም በምድራችሁ ላይ አያልፍም" የሚል ይጨምራል።
፭ ዕብ. "የኀይላችሁን ትዕቢት እሰብራለሁ" ይላል።
፮ ዕብ. "ልጆቻችሁን ይነጥቃሉ" ይላል።

ስሶቻችሁንም ያጠፉሉ፤ እናንተንም ያሳንሳሉ፤
መንገዶቻችሁም በረሃ ይሆናሉ።
፳፫“እስከዚህም ድረስ ባትቀጡ፥ አግድማች
ሁም ብትሄዱ፥ ፳፬እኔ ደግሞ አግድሜ በቊጣ
እሄድባችኋለሁ፤ ስለ ኀጢአታችሁም ሰባት
እጥፍ እበቀላችኋለሁ። ፳፭የቃል ኪዳኔንም
በቀል ይበቀልባችሁ ዘንድ ሰይፍ አመጣባችኋ
ለሁ፤ ወደ ከተማችሁም ትሸሻላችሁ፤ ቸነፈር
ንም እሰድድባችኋለሁ። በጠላቶቻችሁም እጅ
ተላልፋችሁ ትሰጣላችሁ፤ ፳፮በእህል ረሃብ ባስ
ጨነክኋችሁ ጊዜ ዐሥር ሴቶች እንጀራ በአንድ
ምጣድ ይጋግራሉ፤ በሚዛንም መዝነው እን
ጀራችሁን ይመልሱላችኋል፤ በበላችሁም ጊዜ
አትጠግቡም። ፳፯እስከዚህም ድረስ ባትሰሙኝ፥
አግድማችሁም ብትሄዱብኝ፥ ፳፰እኔ ደግሞ አግ
ድሜ በቊጣ እሄድባችኋለሁ፤ እንደ ኀጢአታ
ችሁም ሰባት እጥፍ እቀጣችኋለሁ። ፳፱የወንዶች
ልጆቻችሁንም ሥጋ ትበላላችሁ፤ የሴቶች ልጆ
ቻችሁንም ሥጋ ትበላላችሁ። ፴የኮረብታ መስ
ገጃዎቻችሁን አፈርሳለሁ፤ በእጅ የተሠሩ የዕ
ንጨት ምስሎቻችሁንም አጠፋለሁ፤ ሬሳችሁ
ንም በጣዖቶቻችሁ ሬሳዎች ላይ እጥላለሁ፤
ነፍሴም ትጸየፋችኋለች። ፴፩ከተሞቻችሁንም
ባድማ አደርጋለሁ፤ መቅደሶቻችሁንም አፈርሳ
ለሁ፤ የመሥዋዕታችሁንም መዓዛ አላሸትትም።
፴፪ምድሪቱንም የተፈታች አደርጋለሁ፤ የሚቀ
መጡባት ጠላቶቻችሁም ከእርስዋ የተነሣ ይደ
ነቃሉ። ፴፫እናንተንም በአሕዛብ መካከል እበት
ናችኋለሁ፤ በሄዳችሁበትም ሁሉ ሰይፍ ታጠፋ
ችኋለች፤ ምድራችሁም የተፈታች ትሆናለች፤
ከተሞቻችሁም ባድማ ይሆናሉ።
፴፬“በዚያም በተፈታችበት ዘመን ሁሉ እና
ንተም በጠላቶቻችሁ ምድር ሳላችሁ፥ ምድ
ሪቱ ሰንበት በማድረግዋ ደስ ይላታል፤ በዚያም
ጊዜ ምድሪቱ ታርፋለች፤ ሰንበትንም በማድረ
ግዋ ደስ ይላታል። ፴፭እናንተ ተቀምጣችሁባት
በነበረ ጊዜ በሰንበቶቻችሁ አላረፈችም ነበርና
በተፈታችበት ዘመን ሁሉ ታርፋለች። ፴፮በጠ
ላቶቻቸውም ምድሮች ሳሉ ከእናንተ ተለይ
ተው በቀሩት ላይ በልባቸው ድንጋጤን እሰ
ድድባቸዋለሁ፤ በነፋስም የምትንቀሳቀስ የቅ
ጠል ድምፅ ታሸብራቸዋለች፤ ከሰይፍ እንደ
ሚሸሹ ይሸሻሉ፤ ፴፯ማንም ሳያሳድዳቸው ከሰ
ይፍ እንዲሸሹ እርስ በርሳቸው ይሰነካከላሉ፤
እናንተም በጠላቶቻችሁ ፊት መቆም አትች
ሉም። ፴፰በአሕዛብም መካከል ትጠፋላችሁ፤
የጠላቶቻችሁም ምድር ትውጣችኋለች። ፴፱ከእ
ናንተም ተለይተው የቀሩት ስለ ኀጢአታቸው
ይጠፋሉ፤ በአባቶቻቸውም ኀጢአት ደግሞ
በጠላቶቻቸው ምድር ይቀልጣሉ።
፵“እንደ ከዱኝ፥ ቸልም እንዳሉኝ፥ በፊቴም
አግድመው እንደ ሄዱ፥ ኀጢአታቸውንና፥
የአባቶቻቸውን ኀጢአት ይናዘዛሉ። ፵፩እኔም
ደግሞ አግድሜ ከእነርሱ ጋር በቊጣ ሄድሁ፤
በጠላቶቻቸውም ምድር አጠፋቸዋለሁ። ነገር
ግን በዚያን ጊዜ ያልተገረዘው ልባቸው ያፍ
ራል፤ ስለ ኀጢአታቸውም ይናዘዛሉ፤ ፵፪ያን
ጊዜ እኔ ከያዕቆብ ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳ
ኔን አስባለሁ፤ ደግሞም ከይስሐቅ ጋር የገባሁ
ትን ቃል ኪዳኔን፥ ከአብርሃምም ጋር የገባሁ
ትን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ፤ ምድሪቱንም አስ
ባለሁ። ፵፫ምድርም ከእነርሱ መጥፋት የተነሣ
ባዶ ትቀራለች፤ እነርሱም ሳይኖሩ በተፈታች
በት ዘመን ዕረፍት ታደርጋለች፤ ፍርዴንም ስለ
ናቁ፥ ነፍሳቸውም ሥርዐቴን ስለ ተጸየፈች የኀ
ጢአታቸውን ቅጣት ይሸከማሉ። ፵፬ነገር ግን
እኔ እግዚአብሔር አምላካቸው ነኝና እነርሱ
በጠላቶቻቸው ምድር ሳሉ፥ እስካጠፋቸው
ድረስ ከእነርሱም ጋር ያለኝን ቃል ኪዳን እስ
ካፈርስ ድረስ አልጥላቸውም፤ አልጸየፋቸው
ምም። ፵፭እኔ አምላካቸው እሆን ዘንድ አሕዛብ
እያዩ ከግብፅ ምድር ከግዞት ቤት እንዳወጣኋ
ቸው የቀድሞ ቃል ኪዳናቸውን ስለ እነርሱ
አስባለሁ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝና።”
፵፮እግዚአብሔርም በእርሱና በእስራኤል
ልጆች መካከል በሲና ተራራ ላይ በሙሴ እጅ
የሰጣቸው ሥርዐቶችና ፍርዶች፥ ሕግጋትም
እነዚህ ናቸው።

## ምዕራፍ ፳፯

### ለእግዚአብሔር ስለሚቀርበው መባእ የተሰጠ ሕግ

፩እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገ
ረው፦ ፪“ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገ
ራቸው፦ ማናቸውም ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ለእ
ግዚአብሔር ስእለት ቢሳል አንተ እንደምትገ
ምተው መጠን ስለ ሰውነቱ ዋጋውን ይስጥ።
፫ለወንድ ከሃያ ዓመት ጀምሮ እስከ ስድሳ
ዓመት ድረስ እንደ መቅደሱ ሚዛን ግምቱ
አምሳ የብር ዲድርክም ይሁን። ፬ሴትም ብት
ሆን ግምቷ ሠላሳ የብር ዲድርክም ይሁን።
፭ከአምስት ዓመትም ጀምሮ እስከ ሃያ ዓመት
ድረስ ግምቱ ለወንድ ሃያ የብር ዲድርክም፥

ለሴትም ዐሥር የብር ዲድርክም ይሁን። ፮ከአ
ንድ ወርም እስከ አምስት ዓመት ድረስ ለወ
ንድ ግምቱ አምስት የብር ዲድርክም፥ ለሴ
ትም ግምቷ ሦስት የብር ዲድርክም ይሁን።
፯ከስድሳ ዓመትም ጀምሮ ከዚያም በላይ ወንድ
ቢሆን ግምቱ ዐሥራ አምስት ዲድርክም፥ ለሴ
ትም ዐሥር ዲድርክም ይሁን። ፰ለግምቱ የሚ
ከፍለውን ቢያጣ ግን በካህኑ ፊት ይቁም፤
ካህኑም የተሳለውን ሰው ከእጁ ባለው ገንዘብ
መጠን ይገምትለት፤ ካህኑም የተሳለው ሰው
እንደሚችል መጠን ይገምትለት።

፱"ለእግዚአብሔርም መሥዋዕት አድርጎ የሚ
ያቀርበው እንስሳ ቢሆን፥ ሰው ከእነዚህ ለእግ
ዚአብሔር የሚሰጠው ሁሉ ቅዱስ ይሆናል።
፲መልካሙን በክፉ፥ ክፉውንም በመልካም አይ
ለውጥ፤ እንስሳንም በእንስሳ ቢለውጥ እርሱና
ልዋጩ የተቀደሱ ይሆናሉ። ፲፩እንስሳው ለእግዚ
አብሔር መሥዋዕት መሆን የማይገባው ርኩስ
ቢሆን፥ እንስሳውን በካህኑ ፊት ያቁመው።
፲፪መልካምም ቢሆን ክፉም ቢሆን ካህኑ ይገም
ተው፤ ካህኑም እንደሚገምተው መጠን እንዲሁ
ይሁን። ፲፫ይቤዠው ዘንድ ቢወድድ ግን ከግ
ምቱ በላይ አምስተኛ እጅ ይጨምር።

፲፬"ሰውም ለእግዚአብሔር ቅዱስ ይሆን
ዘንድ ቤቱን ቢቀድስ፥ ካህኑ መልካም ወይም
ክፉ እንደ ሆነ ይገምተዋል፤ ካህኑም እንደሚ
ገምተው መጠን እንዲሁ ይቆማል። ፲፭የተሳለ
ውም ሰው ቤቱን ይቤዠው ዘንድ ቢወድድ
ከግምቱ ገንዘብ በላይ አምስተኛ እጅ ይጨ
ምር፤ ቤቱም ለእርሱ ይሆናል።

፲፮"ሰውም ከርስቱ እርሻ ለእግዚአብሔር
ቢሳል፥ እንደ መዘራቱ መጠን ይገመት፤
አንድ የቆሮስ መስፈሪያ ገብስ የሚዘራበት
እርሻ አምሳ ወቄት ብር ይገመታል። ፲፯እር
ሻውንም ከኢዮቤልዩ ዓመት ጀምሮ ቢሳል፥
እንደ ግምቱ መጠን ይቆማል። ፲፰እርሻው
ንም ከኢዮቤልዩ ዓመት በኋላ ቢሳል፥ ካህኑ
እስከ ኢዮቤልዩ ዓመት ድረስ እንደ ቀሩት
ዓመታት ገንዘቡን ይቈጥርለታል፤ ከግምቱም
ይጐድላል። ፲፱እርሻውንም የተሳለ ሰው ይቤ
ዠው ዘንድ ቢወድድ፥ ከግምቱ ገንዘብ በላይ
አምስተኛ እጅ ይጨምር፤ ለእርሱም ይሆ
ናል። ፳እርሻውንም ባይቤዠው፥ ወይም ለሌላ
ሰው ቢሸጥ እንደ ገና ይቤዠው ዘንድ አይቻ
ለውም። ፳፩እርሻው ግን በኢዮቤልዩ ዓመት
ሲወጣ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ እርሻ ይሆ
ናል፤ ርስቱም ለካህኑ ይሆናል። ፳፪ከርስቱ
እርሻ ያልሆነውን የገዛውን እርሻ ለእግዚአብ
ሔር ቢሳል፥ ፳፫ካህኑ እስከ ኢዮቤልዩ ዓመት
ድረስ የግምቱን ዋጋ ይቈጥርለታል፤ በዚያም
ቀን ግምቱን እንደ ተቀደሰ ነገር ለእግዚአብ
ሔር ይሰጣል። ፳፬በኢዮቤልዩ ዓመት እርሻው
የምድሪቱ ባለ ርስት ወደ ነበረው ወደ ሸጠው
ሰው ይመለሳል፤ የራሱ ወሰን ምድር ነውና።፩
፳፭ግምቱም ሁሉ እንደ መቅደሱ ሚዛን ይሆ
ናል፤ አንዱ ዲድርክም ሃያ አቦሊ ይሆናል።

፳፮"ከእንስሳህ የሚወለድ በኵር ሁሉ ለእግዚ
አብሔር ነው፤ ማንም ይለውጠው ዘንድ አይ
ቻለውም፤ በሬ ቢሆን ወይም በግ ለእግዚአ
ብሔር ነው። ፳፯የረከሰም እንስሳ ቢሆን እንደ
ግምቱ ይቤዠው፤ በእርሱም የዋጋውን አምስ
ተኛ እጅ ይጨምርበታል፤ ባይቤዥም እንደ
ግምቱ ይሸጣል።

፳፰"ለእግዚአብሔርም የተለየ እርም የሆነ
ነገር ሁሉ፥ ሰው ቢሆን ወይም እንስሳ ወይም
የርስቱ እርሻ ቢሆን፥ አይሸጥም፤ አይቤዥም፤
እርም የሆነ ነገር ሁሉ ለእግዚአብሔር ቅዱሰ
ቅዱሳን ነው። ፳፱ከሰዎችም መባ ሆኖ የቀረበ
ሁሉ እስኪሞት ድረስ አይቤዥም።፪

፴"የምድርም ዐሥራት፥ ወይም የምድር
ዘር፥ ወይም የዛፍ ፍሬ ቢሆን፥ የእግዚአብ
ሔር ነው፤ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው።
፴፩ሰውም ዐሥራቱን ሊቤዥ ቢወድድ፥ አም
ስተኛ እጅ ይጨመርበታል። ፴፪ከበሬም
ሁሉ ከዐሥር አንድ፥ ከበግም ሁሉ ከዐሥር
አንድ፥ ከእረኛውም በትር በታች ከሚያልፍ
ሁሉ ከዐሥር አንድ ለእግዚአብሔር የተቀ
ደሰ ይሆናል። ፴፫መልካሙን በክፉ፥ ክፉው
ንም በመልካም አይለውጥ፤ ቢለውጠውም
እርሱና ልዋጩ የተቀደሱ ይሆናሉ፤ አይቤ
ዠውም።"

፴፬እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ ለእስራ
ኤል ልጆች ያስተምራቸው ዘንድ ሙሴን ያዘ
ዘው ትእዛዛት እነዚህ ናቸው።

---

፩ በግእዙ "እስመ ደወለ ዚአሁ ውእቱ ወምድሩ" የሚል ይገኛል።

፪ ግሪክ ሰባ. ሊ. "አይቤዥም ፈጽሞ ይገደል" የሚል ይጨምራል።